

ከሚሊየነርነት ወደ ጎዳና ሕይወት

ገጽ 16



‹‹የጀሎ ደቀዬ›› የሕዝብ መዝናኛ ፓርክ - ቀጣዩ የሆሳእና ከተማ ፈርጥ

ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

አኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 182 መጋቢት 2 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







ፎቶ፡- ገበበ ገብሬ

# የአገልግሎት አሰጣጥን የሚያዘምኑ ፕሮጀክቶች ለነዋሪው አስፈላጊ ናቸው

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- የከተማዋን አገልግሎት አሰጣጥ በዲጂታል አሰራር የሚቀይሩ ፕሮጀክቶች ለነዋሪው አስፈላጊ ናቸው ሲሉ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ፡፡

በ90 ቀናት ፕሮጀክቶች የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማን አገልግሎት ወደ ዲጂታል አሰራር የሚቀይር ማዕከል ተመርቋል።

በምርቃት ሥነሥርዓቱ የተገኙት የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፤ ማዕከሉን ወደ ስራ ለማስገባት የተለያዩ እንቅፋቶችና አደጋዎች አጋጥመውን ነበር፤ ይሁንና ችግሮቹን አልፈን የሕዝቡን ኑሮ የሚያዘምን ፕሮጀክት ወደ ስራ ማስገባት ችለናል ብለዋል።

ሕዝቡን በሙስና ያስመረሩትን አካላት በሕግ ቁጥጥር ስር ከማዋል ባለፈ የክፍለ ከተማውን አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን በሚመጥን መልኩ ለማድረግ የሚረዳ የዲጂታል አገልግሎት የሚሰጥ የአስተዳደር ህንፃ ወደ ስራ መግባቱን ይፋ አድርገዋል።

የለሚኩራ ክፍለከተማ እንዲመሰረት የተደገረበት ዋነኛው ምክንያት ለኅብረተሰቡ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ለማድረግ ነው፡፡ የክፍለ ከተማውን

የአገልግሎት አሰጣጥን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## በሰባት ወራት የ2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ ተችሏል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሰባት ወራት የ2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ መቻሉን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

በሰባት ወራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከአቮካዶ ምርት ከ 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ባለፉት ሰባት ወራት የአቮካዶ ምርትን ወደ ውጭ በመላክ ከ 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቷን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የፍራፍሬ ልማት ዴስክ ኃላፊ አቶ አጥላው አንበሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ 161 ሺ 471 ሄክታር የሚጠጋ መሬት በፍራፍሬ የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ30ሺ 587 ነጥብ 74 ሄክታር በላይ የሚሆነው በአቮካዶ የተሸፈነ ነው።

ኃላፊው እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ የሚመረቱ የአቮካዶ ዝርያዎች ‹‹ሃስ፣ ኢቲንግር፣ ፍራፍሬ፣ ባኮን፣ ፒንከርተንና ናባል›› የሚባሉ ናቸው። በአገሪቱ ያለው ተስማሚ የአየር ንብረት አቮካዶን ለማልማት ምቹ አጋጣሚ ፈጥሯል። የመንግሥት ፖሊሲና ተቋማዊ ድጋፍ፣ የገበያ ፍላጎት መጨመር፣ የተቀናጁ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ማሳደግና ማቋቋም፣ ክላስተርን መሰረት ያደረጉ ተከላና

ከአቮካዶ ምርት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ - ሃይማኖት አብርሃ

## በኦሮሚያ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች 2 ነጥብ 1 ሚሊዮን ኩንታል የሰብዓዊ ድጋፍ ቀርቧል

- 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል

ገጽ 4







# ክልሉ በሌማት ትሩፋት ተስፋ ሰጪ ሥራ እየሠራ ነው


**ሞገስ ጸጋዬ**

ሐረር፡- በሐረሪ ክልል እየተሠሩ የሚገኙ የዶሮና የወተት ላም ርባታ ስራዎች እንደ ሀገር ለተያዘው የሌማት ትሩፋት ሥራ ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ መሆኑን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። በሀረሪ ክልል የሌማት ተሩፋት አካል የሆኑ የእንስሳት ርባታ ሥራዎች በግብርና ሚኒስቴር ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ተጐብኝተዋል።

በጉብኝቱ ወቅት ንግግር ያደረጉት የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ እንደገለጹት፣ በሀረሪ ክልል እየተሠሩ ያሉ የዶሮ እና የወተት ላሞች ርባታ እንደ ሀገር ለተያዘው የሌማት ትሩፋት እውን መሆን ተስፋ የሚሰጡ ናቸው፡፡

የሌማት ትሩፋት ትኩረቱ በወተት፣ በእንቁላል፣ በዓሣና በማር ላይ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በሀረሪ ክልል እየለማ ያለው የወተትና የዶሮ ምርት ውጤታማ ነው። በወተት ልማት የተሰማሩ ግለሰቦች በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሥራዎችን እየሠሩ ይገኛሉ። በሀገር ደረጃ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለውና በቀን እስከ 32 ሊትር ወተት የሚሰጡ ላሞች እንዳሉ መመልከታቸውን ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፣ በከተማ ውስጥ በእንስሳት ውጤቶች ምርት ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ከራሳቸው አልፈው ማኅበረሰቡን እየጠቀሙ ነው።



ሌሎችም ልምድ በመውሰድ ወደ ልማት እንዲገቡና ኢትዮጵያ የያዘችውን የልማት ጉዞ እንዲደግፉ አሳስበዋል። በሀረሪ ክልል የሚሠሩ ልማቶች የሌማት ትሩፋቱ እንዲሳካ ትልቅ እገዛ እያደረጉ ነው።

ከሌማት ትሩፋት ዓላማዎች መካከል ማንኛውም ግለሰብ በቤቱ የልማት ሥራ መሥራት አለበት ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ሁሉም ወደ ልማት በመሰማራት ከራሱ አልፎ አካባቢውን መደገፍ አለበት። ከእንስሳት ርባታ ጐን ለጐን የመኖ ማቀነባበሪያ ማዕከል ማቋቋም አስፈላጊ ነው። መንግሥትም በዘርፉ ያለውን ችግር በመገንዘብ ለመደገፍ ዝግጅት ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

የሀረሪ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንትና የክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ሚስራ አብደላ በበኩላቸው፣ የሌማት ትሩፋትን በክልል ደረጃ ለማሳካት ቀጣይ አራት ዓመታትን ያገናዘበ ዕቅድ ይዘን እየሠራን ነው ያሉ ሲሆን አርባ የዶሮ፣ አርባ የወተት እና አራት የማር መንደሮችን ለመመስረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተያዘው ዓመት ወደ 30 ሺህ ጫጩት ለማከፋፈል ታስቦ ባለፉት ስድስት ወራት ወደ 16 ሺህ ጫጩቶችን ማከፋፈል መቻሉን የገለጹት ምክትል ፕሬዚዳንቷ፣ በቀጣይ ለኅብረተሰቡ የሚከፋፈሉ ጫጩቶች እንዳሉ ጠቁመው የኅብረተሰቡን ፍላጐት ለማሟላት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ዘርፉ አዋጭና በመንግሥት አቅም ብቻ የሚቻል ባለመሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ዘርፉ እንዲሰፋ እየተሠራበት ነው ሲሉ ጠቁመዋል። በቀጣይም የተጀመረውን ሥራ በማስፋት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንደሚሠራና የሕዝቡን ተጠቃሚነት እንዲሁም የሥራ ዕድል ፈጠራን እያስፋፋን እንሄዳለን ብለዋል።



# በስልጤ ዞን ሁለት ሺህ 814 ሄክታር መሬት የመስኖ ስንዴ እየለማ ነው

## - ከ100 ሺህ ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይጠበቃል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል የሚገኘው የስልጤ ዞን ሁለት ሺህ 814 ሄክታር መሬት ላይ የበጋ መስኖ ስንዴን እያለማ እንደሚገኝ የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡ ከለማው ስንዴ ከ100 ሺህ ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይጠበቃል፡፡

የስልጤ ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ሙርሰል አማን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመስኖ ስንዴ ልማት በዞኑ የተጀመረው ባለፈው ዓመት ሲሆን በዚህም ከ100 ሄክታር በላይ ለምቷል፡፡ በዚህ ዓመት ደግሞ የተሻለ የበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን በዚህም ሁለት ሺህ 814 ሄክታር እየለማ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ ሙርሰል ገለጻ፤ በዘንድሮው የመስኖ ስንዴ ልማት ከሰባት ሺህ 500 በላይ አርሶ አደሮችን ያሳተፈ ሲሆን ትላልቅ ክላስተሮች የተፈጠሩበት እና አዳዲስ የእርሻ መሬቶች ወደ ልማት የገቡበት ነው፡፡ በተለይም በስልጤ ወረዳ አንድ ክላስተር ላይ እስከ 400 ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም ማልማት ተችሏል፡፡

በተለየ ሁኔታም ከስደት ተመላሾች በማኅበር ተደራጅተው በመስኖ ስንዴ ልማት እንዲሰማሩ መደረጉ ትልቅ ዕድል ነው ያሉት የመምሪያ ኃላፊው፤ እንደ ክልልም የተሻለ አፈጻጸም የታየበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የስንዴ ምርቱ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ሰብሉ በመድረሱ በቅርቡ ወደ ምርት መሰብሰብ እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡ ከሚገኘው የበጋ መስኖ ስንዴ ምርት ላይ 50 በመቶ ያህሉን ለኤክስፖርት ግብይት እንዲውል ከሚመለከተው አካል ጋር እንሰራለን ነው ያሉት፡፡

ባለፈው ዓመት የበጋ መስኖ ስንዴን ለማምረት አርሶ አደሮች የግንዛቤ ክፍተት ነበረባቸው ያሉት አቶ ሙርሰል፤ በተግባር ማልማት እንደሚቻል ሲረዱ ግን ምርታማነታቸውን ከፍ በማድረግ ከዚህ ቀደም 42 ኩንታል በሄክታር የሚለማውን የስንዴ ምርት ሞዴል አርሶ አደሮች እስከ በሄክታር እስከ 60 ኩንታል ማምረት ጀምረዋል ብለዋል፡፡

ዘመናዊ የመስኖ ካናሎች አለመኖር፣ የፓምፕ እጥረት እና የነዳጅ አቅርቦት እጥረትና ዋጋ መጨመር ዋነኞቹ ችግሮች ነበሩ ያሉት አቶ ሙርሰል፤ ይህንን ችግር ለመፍታት በየደረጃው ያሉ መዋቅሮች ማገዝ እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

# በአማራ ክልል

## ለመልሶ ማቋቋም 1 ቢሊዮን ብር ተመድቦ እየተሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ይልቃል ከፋለ (ዶክተር)

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ለመልሶ ማቋቋም ሥራዎች 1 ቢሊዮን ብር ተመድቦ እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ (ዶክተር) ገለጹ።

ለሦስት ቀናት ሲካሄድ የቆየው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት 6ኛው ዙር 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 5ኛ መደበኛ ጉባዔው ትናንትና ተጠናቋል። በአንድ ቢሊዮን ብር በጀት በክልሉ የተለያዩ ዘርፎች ላይ የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ዶክተር ይልቃል አስታውቀዋል።

ከፌዴራል መንግሥት ለመልሶ ማቋቋም የሚውል ገንዘብ በቅርቡ እንደሚለቀቅ ይጠበቃልም ያሉት ዶክተር ከፋለ፤ በክልሉ በሰሜኑ ጦርነት ወቅት በተለያዩ ዘርፎች ላይ የደረሰውን ጉዳት በተመለከተ ጥናት በማድረግ ሰነድ አዘጋጅቷል ሲሉም አስረድተዋል።

ድህነትን ለማሸነፍ ዋነኛው የትኩረት ዘርፉችን የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ነው፣ ምርታማነትን በማሳደግ ልማትን ማፋጠን ዋነኛው መሳሪያ አድርጎ መውሰድ ወቅቱ የሚጠይቀው ስለሆነ በተመረጡ ሰብሎች ላይ ማተኮር ይገባል ብለዋል።

የአርሶ አደሩን ምርታማነት ለመጨመር በዓመት ሦስት ጊዜ ማምረት፣ ቴክኖሎጂን መጠቀምና ምርጥ ዘር ማስፋፋት ላይ መሰራት እንዳለበት አስረድተዋል።

ማዕድን ሀብት ልማት ላይ እምቅ ሀብት አለ ያሉ ሲሆን፤ ለአብነትም በዓባይ ሸለቆ አካባቢ የተጀመረውን የሲሚንቶ ምርት ጅማሮ የበለጠ ማጠናከር እንደሚገባ ገልጸዋል።

የከተማ ልማትን ለማፋጠን ከተሞችን በዕቅድ በመምራት ማልማቱ አስፈላጊ እንደሆነ፤ በአብዛኛው ቤትን ወደ ላይ ማልማት የመሬትን ችግር እንደሚቀርፍ ጠቁመዋል።

የመንግሥት ሰራተኛውን ኑሮው ለማሻሻል ደመወዝ መጨመር ብቸኛ መፍትሔ እንዳልሆነና ሌላ አሰራር መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ነው የተናገሩት።

በክልሉ የመስኖ ፕሮጀክቶች አበረታች ለውጥ እየታየባቸው መሆኑንም አንስተው፤ በመስኖ ልማት ዙሪያ የሚታዩትን ችግሮች መፍታት እንደሚገባም ገልጸው፤ ችግር ያለባቸውን የመስኖ ግድቦችን መጠገን፣ መከታተልና ማስተካከል አስፈላጊ እንደሆነ አሳስበዋል።

በተጨማሪ በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ረገድ በክልሉ ችግር መኖሩንም ጠቁመው፤ የመብራት ችግርን መፍታት ጥረት ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል በክልሉ ገቢ በመሰብሰብ ረገድ በትኩረት መሥራት እንደሚገባም ገልጸው፤ የተሰበሰበው ገቢ ለተፈለገው ዓላማ መዋል ይገባዋልም ብለዋል።

በወረዳዎች ትክክለኛ ያልሆኑ የበጀት አጠቃቀሞች መኖራቸውን አንስተው፤ ወረዳዎች በጀትን በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

ሕዝቡ ሙስናን ለመከላከል በሚደረገው ሂደት ድጋፍ እንዲያደርግም ጠይቀዋል፤ በሙስና ትግሉ በቀጣይ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ሊተላለፉ እንደሚችሉም ገልጸዋል።

የፀጥታ መዋቅሩ ከነበረው በተሻለ ቁመና ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ ሀገርን ለማስቀጠል መተጋገዝ፣ መረዳዳትና ትብብር በእጅጉ መሰረታዊ ጉዳዮች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ክልሉ በኢንቨስትመንት፣ በቱሪዝም እና በሌሎች የልማት አማራጮች አስተማማኝ እንዲሆን በቅንጅት እየሰራን ነው ያሉት ዶክተር ከፋለ፤ የክልሉ መንግሥት በሠራው ጠንካራ ሥራ የሰላምና ደህንነት ችግር የነበረባቸው አካባቢዎች ወደ ሰላም መመለሳቸውንም አስረድተዋል።

# ምርት በሚደብቁና ሕገ ወጥ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ ቁጥጥር እየተደረገ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ምርት በሸማቾች ማህበራት በኩል በብዛት እንዲቀርብ ከሚሰራው ስራ ጎን ለጎን ምርት የሚደብቁና ሕገ ወጥ የዋጋ ጭማሬ የሚያደርጉ አካላትን የመቆጣጠርና እርምጃ የመውሰድ ስራ መጀመሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ባወጣው መግለጫ የከተማ አስተዳደሩ የኑሮ ውድነትና የዋጋ አለመረጋጋት እንዲሁም የትራንስፖርት አቅርቦት የከተማችን ነዋሪ የኑሮ ጫና ያከበዱ ፈተናዎች እንደሆኑ እንደሚገነዘብ ገልጿል።

ከኑሮ ውድነት ጋር የተያያዘውን ችግር ለመቅረፍ ምርት በሸማቾች ማኅበራት በኩል በብዛት እንዲቀርብ ከሚሰራው ስራ ጎን ለጎን ምርት የሚደብቁና ሕገ ወጥ የዋጋ ጭማሬ የሚያደርጉ አካላትን መቆጣጠርና እርምጃ መውሰድ መጀመሩን ይፋ አድርጓል።

በከተማዋ ስር የሰደዱና የተወሳሰቡ በርካታ ኢኮኖሚያዊ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም መዋቅራዊ ችግሮችን ያሉበት ሲሆን ችግሮችን ሕዝቡን ባሳተፈ አግባብ ለመፍታት ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ከተማ አስተዳደሩ ገልጿል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከከተማዋ ነዋሪዎች የተሰጠውን ኃላፊነት በውጤታማነት ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑን በመግለጫው አመላክቷል።

በከተማዋ እየተካሄዱ ባሉ ሰው ተኮር ፕሮግራሞችም የበርካታ አረጋውያንና አቅመ ደካሞችን ቤት በመጠገን የኑሮ ጫናቸውን ለማቃለል ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስተዳደሩ በመግለጫው አስታውቋል።

ባለሀብቶችን በማስተባበር በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች የተቋቋሙ የምገባ ማዕከሎች በቀን አንዴ እንኳን ምግብ ለማግኘት ይቸገሩ የነበሩ ዜጎቻችን ተመግበው እንዲውሉ መደረግ በመቻሉ የከተማ አስተዳደሩ ዜጎችን ለመጥቀም እየሰራ መሆኑን አመላካች ነው ሲል አስረድቷል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የተማሪዎቻችን ብሩህ አዕምሮ በምግብ እጥረት እንዳይጎዳ በትምህርት ቤቶች የምገባ ፕሮግራሞች ተቀርፀው ተግባራዊ መደረጋቸውን መግለጫው አመላክቷል።

በከተማ ደረጃ የተለያዩ ሜጋ ፕሮጀክቶች ተቀርፀው በፍጥነትና በጥራት ተጠናቀቀው ለሕዝቡ አገልግሎት ከመስጠታቸውም በላይም የከተማዋንና የአገሪቱን ገፅታ ወደ አዲስ ምዕራፍ ከፍ በማድረግ ደረጃ ትልቁን ሚና እየተጫወቱ ይገኛል ሲል አስተዳደሩ አስታውቋል፡፡

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ የልማት ስራዎቹ የከተማዋን ስምና ታሪኳን በሚመጥን መልኩ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ 2ኛ ዓመት 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ባሳለፈው ውሳኔ፤ ወቅታዊ የኑሮ ውድነትና የገበያ አለመረጋጋት የዋጋ መናርን መነሻ በማድረግ በአስቸኳይ ምርት ወደ ከተማዋ እንዲገባና እንዲሰራጭ ግብረ ኃይል አቋቁሟል።

ለተማሪዎች ምገባ የሚያቀርቡ እናቶች በአሁኑ ዋጋ ማቅረብ መቸገራቸውን መነሻ በማድረግ ለተማሪዎች ምገባ በወር 54 ሚሊዮን ብር በዓመት 540 ሚሊዮን ብር ተጨማሪ በጀት አጽድቋል። ይህ ማለት ለአንድ ተማሪ በቀን ሃያ ብር የነበረውን ወደ ሃያ ሶስት ብር ከፍ እንዲል ተደርጓል።

በተጨማሪ ከወቅቱ ዋጋ መናር እና የገበያ አለመረጋጋት ጋራ ተያይዞ አከራዮች የቤት ኪራይ ዋጋ እስከ ሰኔ 2015 ዓ/ም እንዳይጨምሩ መወሰኑ የሚታወስ ነው።

# እየጣለ ያለው ዝናብ ለበልግ ግብርና ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል

**አማን ረሺድ**


ዶክተር አሳምነው ተሾመ

አዲስ አበባ፡- ከሰሞኑ እየጣለ የሚገኘው ዝናብ ለበልግ ግብርና ስራዎችና ለማሳ ዝግጅት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሜትሮሎጂ ትንበያና ማስጠንቀቂያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር አሳምነው ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከየካቲት ወር ወጨረሻ አንስቶ በተለያዩ አካባቢዎች የሚጥለው ዝናብ ለበልግ ግብርና ስራ ጠቃሚ ነው።

በበልግ ወቅት የሚፈጠር ዝናብ አዘል እርጥበት ለማሳ ዝግጅት ስራዎች ጠቃሚ ነው። ይህም በግብርናው ስራ የሚከናወኑ የዝግጅት ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚረዳ ይታመናል ብለዋል።

ዶክተር አሳምነው እንዳስታወቁት፤ ከባለፈው ሳምንት ጀምሮ ለበልግ ዝናብ መፈጠር አመቺ የሆነ የአየር ንብረት በምስራቅ አማራ፣ በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች፣ በምስራቅ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ደጋማ አካባቢዎች ተስተውሏል።

በተጨማሪ በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች እንዲሁም አብዛኛው የስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋና የተጠናከረ የደመና ክምችት እንደነበር ጠቁመዋል። በተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ መመዝገቡንም አስረድተዋል፡፡

ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ካስተናገዱ አካባቢዎች መካከል ድሬዳዋ፣ ማጂ፣ ጂንካ፣ አደሌ፣ ሊሙገነት እንደሚገኙበት የገለጹት ዶክተር አሳምነው፤ አዲስ አበባ እና ጅማ ከተሞች መካከለኛ የዝናብ መጠን እንዳስመዘገቡ አስረድተዋል።

በበልግ ዋነኛ የዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች ላይ በቀጣይ የተጠናከረ የደመና ክምችት እንደሚኖራቸው ጠቁመዋል። በትንበያ መረጃዎች መሰረት በተለይም በሰሜን ሶማሌ፣ በደቡብ ኦሮሚያ ቆላማ አካባቢዎች፣ በጉጂ፣ በቦረና፣ በባሌ፣ በሲዳማ ክልል ፣ ደቡብ ምዕራብ ክልል እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ አስታውቀዋል።

ለበልግ ዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት እየተጠናከረና እየተስፋፋ ስለሚሄድ የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብ እንደሚያስፈልግ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ዶክተር አሳምነው እንደገለጹት፤ ዝናብ በሚያገኙ አካባቢዎች የሚኖሩ አርሶና አርብቶ አደሮች እንዲሁም የተለያዩ የመንግሥት ተቋማት የሜትሮሎጂ መረጃውን ከግንዛቤ በማስገባት የሚገኘውን ዝናብ ለበልግ የግብርና ሥራ፣ ለውሃ አቅርቦት፣ ለእንስሳትና ለሰው ልጅ መጠጥ ውሃ በአግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

በተለየ ሁኔታ የመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች፣ የምስራቅ ኢትዮጵያ፣ የምስራቅ አማራ፣ አፋርና ደቡብ ትግራይ የሀገሪቱ አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን ሊኖራቸው እንደሚችል በታህሳስ ወር መጨረሻ ላይ የአየር ትንበያ መረጃ መቅረቡ የሚታወስ ነው፡፡

# መንግሥት የቀድሞ ተዋጊዎች ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው ሰላማዊ ሕይወት እንዲመሩ እየሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል መንግሥት የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የቀድሞ የሕወሓት ተዋጊዎች ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው ሰላማዊ ሕይወታቸውን እንዲመሩ በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑን የብሔራዊ ተሐድሶ ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ገለጹ።

መንግሥትና ሕወሓት የተፈራረሙት የሰላም ስምምነት ትግበራ አካል የሆነው ብሔራዊ የተሃድሶ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ትናንትና በመቀሌ ከተማ ተካሂዷል።

በውይይቱ ላይ የተገኙት አምባሳደር ተሾመ፤ ብሔራዊ የተሃድሶ ኮሚሽን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 525/2015 ተቋቋሞ በይፋ ሥራ መጀመሩን አስታውቀዋል። በሰላም ስምምነቱ መሠረትም ተዋጊዎችን ትጥቅ የማስፈታት፣ ወደ አንድ ማዕከል የማሰባሰብና ተገቢውን ተሐድሶ አካሂዶ በአገሪቱ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ግንባታ ውስጥ እንዲሳተፉ ይሠራል ብለዋል።

ጦርነቱ አስከፊ ጉዳት ያደረሰና ኢትዮጵያውያን ቆም ብለው እንዲያዩ ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡ በቀጣይ ጦርነት በቃን ልንል ይገባል ያሉት አምባሳደር ተሾመ፤ በትብብር ኢትዮጵያን መገንባት ላይ ትኩረት ልናደርግ ይገባል ብለዋል፡፡

መንግሥት የሰላም ስምምነቱን በመተግበር ረገድ ትላልቅ ስራዎችን እያከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ የትጥቅ ማስፈታትና ተዋጊዎችን ወደ ማኅበረሰቡ የመቀላቀል ስራ እንዲሳካም በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑን አንስተዋል።

የቀድሞ ተዋጊዎች እንደማንኛውም ዜጋ የተረጋጋ ሕይወት እንዲመሩ አስፈላጊው ሁሉ ድጋፍ የሚደረግ ሲሆን ለተግባራዊነቱም የፖለቲከኞችና የሌሎች ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው ሲሉ ገልጸዋል።



አምባሳደር ተሾመ ቶጋ


አቶ ጌታቸው ረዳ

የቀድሞ የሕወሓት ተዋጊዎች በጉልበታቸውና በዕውቀታቸው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ልማት ተግተው ለመሥራት መዘጋጀት እንዳለባቸውም አምባሳደር ተሾመ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በመድረኩ ላይ የተናገሩት አቶ ጌታቸው ረዳ ብሔራዊ የተሐድሶ መርሃ-ግብሩ የቀድሞ ተዋጊዎች ትጥቅ ፈትተው በልማት ስራዎች እንዲሳተፉ የሚያደርግ መሆኑ ፋይዳው የጎላ ነው ብለዋል። መንግሥትና ሕወሓት የሰላም ስምምነት መፈራረማቸውን ተከትሎ ተዋጊዎችን ወደ ማኅበረሰቡ መልሶ ለመቀላቀል ትጥቅ ማስፈታት የመጀመሪያው ሂደት መሆኑን ገልጸዋል። በዚህም ትጥቅ ማስፈታት ብቻ ሳይሆን የተሐድሶ ስራዎችን በተቀናጀ መልኩ መተግበር እንደሚገባም ጠቁመዋል።

የተሐድሶ ሥራው በሀገር ደረጃ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ያነሱት አቶ ጌታቸው፤ ሂደቱን በማሳካት በመልሶ ግንባታ የአገርን አቅም ማጎልበት እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል። በመሆኑም የተጀመረውን የሰላም ሂደት አጠናክሮ በማስቀጠል ረገድ ሁሉም በቁርጠኝነት ሊሰራ እንደሚገባም ገልጸዋል።

# በኦሮሚያ ክልል በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች 2 ነጥብ 1 ሚሊዮን ኩንታል የሰብዓዊ ድጋፍ ቀርቧል

## - 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በተከሰተው ድርቅ ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የተለያዩ የምግብ አይነቶችን በማሰባሰብ ለተረጂዎች ማድረስ መቻሉን የክልሉ መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ።

በክልሉ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት እየተደረገ ያለውን አጠቃላይ ድጋፍ አስመልክቶ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን በትናንትናው ዕለት መግለጫ ሰጥቷል።

የኮሙዩኒኬሽን ኃላፊው አቶ ኃይሉ አዱኛ እንዳስታወቁት፤ በክልሉ 10 ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 79 ወረዳዎች ለድርቅ ተጋልጠዋል። የክልሉ መንግሥት ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመሆን ባደረገው እንቅስቃሴ ለ3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ለተከሰተው ድርቅ የሚውል የገንዘብ ድጋፍ፣ የምግብ እንዲሁም የእንስሳት መኖና ውሃ እየቀረበ መሆኑን ጠቁመዋል። በቦረናና በሌሎች የኦሮሚያ ዞኖች በተከሰተው ድርቅ ምክንያት እየተደረገ ባለው ድጋፍ ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የተለያዩ የምግብ አይነቶችን በማሰባሰብ ለተረጂዎች ማድረስ መቻሉን አስታውቀዋል።

በተጨማሪ ከተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች የተሰባሰበ አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ መደረጉን አቶ ኃይሉ ተናግረዋል፡፡

ድርቁ ከተከሰተ በኋላ የዜጎች ሕይወት እንዳይጠፋ የተለያዩ የሰብዓዊ ድጋፍ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ከፌዴራል መንግሥት አንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል ምግብ፣ በክልሉ ቡሳ ጎኖፋ አማካኝነት 39 ሺህ 596 ኩንታል ምግብ፣ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ 83 ሺህ 715 ኩንታል ምግብ ድጋፍ መደረጉን አስረድተዋል፤

መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ደግሞ 88 ሺህ 273 ኩንታል በአጠቃላይ ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የተለያዩ የምግብ አይነቶችን በማሰባሰብ ለተረጂዎች ማድረስ መቻሉን አስታውቀዋል።

የፌዴራል መንግሥት ከምግብ ድጋፍ ባለፈ በገንዘብ 626 ሚሊዮን 465 ሺህ ብር በላይ አቅርቧል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በበኩላቸው 535 ሚሊዮን 173 ሺህ ብር የሚጠጋ ገንዘብ በማቅረብ በድምሩ አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ መደረጉን ገልጸዋል።

የክልሉ መንግሥት በሁለት ሳምንታት ውስጥ ባደረገው ጥሪ መሠረት 850 ሚሊዮን ብር ድጋፍ መሰብሰቡን የተናገሩት ኃላፊው፤ የፌዴራል መንግሥት ለድርቅ ድጋፍ የሚውል 101 ቦቴ ውሃ አቅርቧል። አሁን ላይ 37 የውሃ ቦቴዎች በቦረና እንደሚገኙና ለተጎጂዎች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል ብለዋል።

እንስሳትን ከሞት ለመከላከል አስፈላጊው ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ኃይሉ፤ የእንስሳትን ሕይወትን ለመታደግ 248 ሺህ 45 እስር የሳር መኖ በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች ማድረስ እንደተቻለ አስረድተዋል። በተጨማሪም የእንስሳት መኖ ወዳለባቸው አጎራባች ዞኖች በማንቀሳቀስ ሕይወታቸውን ለመታደግ ጥረት መደረጉን ጠቁመዋል።

የክልሉ መንግሥት አጠቃላይ ለተሰሩ የድጋፍ ሥራዎች ምስጋና ያቀረበ ሲሆን በቀጣይም የድርቁ ሁኔታ ከቀጠለ ሁሉም የሚችለውን ድጋፍ በማድረግ የበኩሉን እንዲወጣ አቶ ኃይሉ ጥሪ አቅርበዋል።



አቶ ኃይሉ አዱኛ

## የአገልግሎት አሰጣጥን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

አገልግሎት አሰጣጥ የሚያሳድግ ማዕከል መገንባቱ ለስራዎች መሳካት የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ በመዲናዋ የሕዝቡን ኑሮ ለማዘመን የሚረዱ ተስፋ ሰጪ ፕሮጀክቶችን በስፋት እንደሚከናወኑ ተናግረዋል።

ከንቲባዋ እንዳስታወቁት፤ በመዲናዋ በ90 ቀናት ውስጥ የተጠናቀቁት የተለያዩ ፕሮጀክቶች ትልቅ ድካም የጠየቁና የልማት አሻራ ያረፈባቸው ናቸው። በዚህም በሺዎች ለሚቆጠሩ ነዋሪዎች የሥራ እድል በመፍጠርና የአገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን ጉልህ ሚና እያከበረቱ ይገኛል።

ከተማ አስተዳደሩ በክፍለ ከተማው አገልግሎትን ከማዘመን ባሻገር አራት የዳቦ ፍብሪካዎች ተገንብተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ጥረት ማድረጉን ወ/ሮ አዳነች ገልጸዋል።

በተጨማሪ ሦስት የምገባ ማዕከላቶች በርካታ ችግረኞች ባሉባቸው አካባቢዎች አቅራቢያ መገንባታቸውን ጠቁመው፤ የእንጀራ ፋብሪካም በክፍለ ከተማው እየተገነባ መሆኑን አስረድተዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ዋና ዓላማ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ በ90 ቀናት ፕሮጀክቶች በርካታ የልማት ስራዎችን በማከናወን ሰው ተኮር የልማት ስራዎች፤ በመሰረተ ልማት ግንባታ፣ በአገልግሎት አሰጣጥና በተለያዩ ዘርፎች ውጤት እየመጣ መሆኑን ጠቁመዋል።

በክፍለ ከተማው ከተመረቁ የ90 ቀናት ፕሮጀክቶች ውስጥ የአገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን የሚረዳ የዲጂታል ቴክኖሎጂ መተግበሪያን ያካተተ ዘመናዊ የአስተዳደር ህንጻ አንዱ ሲሆን፤ በተጨማሪ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ለሚገኙ አርሶ አደሮች የሚያገለግሉ የውሃና የኤሌትሪክ መሠረተ ልማቶች ተመርቀዋል።

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የክፍለከተማው ነዋሪዎች የተገነቡ 240 ቤቶችን የያዙ ስድስት ባለ አራት ወለል ህንጻዎች ተመርቀዋል። በዲጂታል አገልግሎት የሚሰጡ ሁለት ጤና ጣቢያዎችና የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጠት የሚችል ሞዴል ወረዳን ከንቲባ አዳነች ሥራ አስጀምረዋል።



## በሰባት ወራት የ2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስ ትመንት ፕሮሞሽን ቡድን መሪ አቶ ታሪኩ ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እንደ አገር የተጀመረው አገር በቀል ኢኮኖሚን ለማሳደግ በትኩረት ከሚሰራባቸው ዘርፎች መካከል ግብርና፣ ማቀነባበር፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ በማዕድንና በአይሲቲ ተጠቃሽ ናቸው።

ኮሚሽኑ በመንግሥት የተሰጠው ተልዕኮ ኢንቨስትመንትን የመሳብ፣ የማበረታታትና የመደገፍ ሚና መሆኑን የገለጹት ቡድን መሪው፤ ዘርፎቹን መሰረት በማድረግ የአገሪቱን የኢንቨስትመንት ፍሰት ለማሳደግ እየተሰራ ነው። አንዱ ማሳያም ከተለያዩ አገራት ፍላጎት ያሳዩ ባለሀብቶችን ወደ አገር ውስጥ መዋዕለንዋያቸውን እንዲያፈሱ ማድረግ፤ ፍላጎት ያሳዩትን ማበረታታትና ወደ ተለያዩ ዓለም ሀገራት በመሄድ ኢንቨስተሮችን የመሳብ ስራ ማከናወን ነው። በዚህም ከቻይና፣ ህንድና ከአውሮፓ አገራት የመጡ አልሚዎችን ማስተናገድ መቻሉን ገልጸዋል።

በቅርቡ ከፓኪስታን አገር 71 የሚሆኑ ልዑካንን በመቀበል በሀገሪቱ ያሉ የኢንቨስትመንት ዕድሎችንና አማራጮችን የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል ያሉት አቶ ታሪኩ፤ ከዚህ በፊትም ከተለያዩ አገራት የመጡ ባለሀብቶችን በማግባባት ኢንቨስት ሊያደርጉ የሚችሉበት ስራ ተሰርቷል ብለዋል።

አቶ ታሪኩ እንዳሉት፤ ኢንቨስትመንት የማስተዋወቅ ስራ በአንድ ጊዜ የሚሳካ ጉዳይ ሳይሆን የበርካታ ባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር የሚጠይቅ በመሆኑ በተለያዩ ሀገራት ኢትዮጵያን ወክለው ካሉ ዲፕሎማቶችና አምባሳደሮች ጋር እየተሰራ ነው። ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግም በትኩረት እየተሰራ ስለመሆኑም ገልጸዋል።

በበጀት ዓመቱ ስድስት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የታቀደ ሲሆን ባለፉት ሰባት ወራት 2 ነጥብ 02 ቢሊዮን ዶላር ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ ተችሏል። ይህም የተገኘው 129 ካምፓኒዎች በኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት መመዝገባቸውን ተከትሎ ነው። ክንውኑ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ 18 በመቶ ብልጫ አለው። ይህም የተገኘው በአብዛኛው ከማምረቻ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከተሰማሩ ባለሀብቶች ነው። በፋርማሲቲካል፣ በጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ በኬሚካል ኢንዱስትሪ፤ የጽዳትና መሰል ዘርፎች ላይ አብዛኛዎቹ መሰማራታቸውን አቶ ታሪኩ ተናግረዋል።

በበጀት ዓመቱ ቀሪ አምስት ወራት እቅዱን ለማሳካት እየተሰራ ሲሆን በሚቀጥለው ወር 500 በላይ የተለያዩ ሀገራት ባለሀብቶች የሚሳተፉበት ሁነት ይዘጋጃል። ይህም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው። በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ የተሰማሩት ባለሀብቶች ስራቸውን እንዲያስፋፉ የማድረግ ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አቶ ታሪኩ ገልጸዋል።

## ከአቮካዶ ምርት...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ሌሎችም ሁኔታዎች ምርቱን ለማሳደግ መልካም ዕድሎች መሆናቸውን አስታውሰዋል።

አገሪቱ ከአቮካዶ ምርት የሚፈለገውን ያህል ገቢ ሳታገኝ ቀርታለች ያሉት አቶ አጥላው፤ ለዚህም ድህረ ምርት አያያዝ፣ ቴክኖሎጂዎችና የመገልገያዎች ግብዓቶች እጥረት፣ የችግኝ ጥራት ማነስ፣ መደበኛ ብድር ማግኘት አለመቻል፣ አቮካዶ አብቃይ አርሶአደሮች በአቮካዶ ላይ ልዩ የኤክስቴንሽን አገልግሎት አለማግኘት፣ ያልተደራጀ የአቅርቦት ሰንሰለት መኖሩ፤ የጋራ ማሸጊያና የደረጃ አወሳሰድ እጥረት፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ውስንነት፣ ያልዳበረ የገበያ መሠረተ ልማት እና ሌሎች ማነቆዎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

የፍራፍሬውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ለአምራቾች የተሰጡ ድጋፎች መኖራቸውን የገለጹት ኃላፊው፤ መንግሥት የእሴት ሰንሰለት ለያዙ አነስተኛ አቮካዶ አብቃዮች የኤክስቴንሽንና የቴክኒክ ድጋፍ፣ የምክርና የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል። አነስተኛ አርሶ አደሮችን በማደራጀትና ምርታቸውን በማስተባበር በአገር ውስጥ ገበያ ለጅምላ አከፋፋዮች በቀጥታ ገበያ እንዲያቀርቡ፣ ለአርሶአደሮቹ የችግኝ ማባዛት ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የፍራፍሬ ችግኝ ማቋቋሚያና ለአቮካዶ ክላስተር ልማት ድጋፍ፣ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት እና ዩኒየኖችን ማደራጀትና ማጠናከር ትኩረት የሚሰጠው ተግባር መሆኑን ጠቅሰዋል።

ባለፉት ሰባት ወራት ከ 1500 ቶን በላይ የአቮካዶ ምርትን ወደ ውጭ በመላክ ከ 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል። አውሮፓና የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የምርቱ ዋና መዳረሻ ናቸው። በሀገሪቱ ባለፉት አምስት ዓመታት የአቮካዶ ምርት በአማካይ በ42 ነጥብ 7 በመቶ መጨመሩን አቶ አጥላው ተናግረዋል።

ይህም የዘርፉን ልማት ለማሳደግ በኮንትራት እርሻ እና ከአምራቾች ጋር ከግል ባለሀብቶች ጋር ትክክለኛ ትስስር ያስፈልገዋል። መንግሥት በቀጣይ የግብርና-ሜካናይዜሽን አጠቃቀምን ከአቮካዶ ምርትና ማቀነባበሪያ እሴት ሰንሰለት ለማሳደግ፣ በአቮካዶ ዘርፍ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ፤ በምርምርና በልዩ የግብርና ኤክስቴንሽን ለማገዝ ቁርጠኝነት እንዳለው ገልጸዋል።

# አገልግል

**የቅዳሜ መጽሄት**



**« ትምህርት የሥርዓት ለውጡን ተከትሎ መቀያየር የለበትም »**

- አቶ ሸዋንግዛው ጥላሁን

ገጽ 6



## በውጭ ምንዛሬ ግኝት

ቡናን እየተከተለ ያለው ዘርፍ

ገጽ 13



## በውል ተዋዋዮች አለመተማመን ሰበር የቋጨው ክርክር

ገጽ 10


የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን
Ethiopian Intellectual Property Authority

## ማሳሰቢያ

የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 320/1995 ከተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መካከል፤ በኢትዮጵያ የአእምሯዊ ንብረት ህጎችንና ደንቦችን ስራ ላይ ማዋልና መከታተል ይገኝበታል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ባለስልጣኑ የሚደርሱ መረጃዎችና ጥቆማዎች እንደሚያመለክቱት፤ በቅጂና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 410/1996 ስር የህግ ጥበቃ የተደረገላቸው የቅጅና ተዛማጅ መብቶች በተለይም የቴሌቪዥን ድራማዎች፣ ፊልሞችና ሌሎች ፕሮግራሞች በተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተቀርፀው በኢንተርኔትና በማህበራዊ ሚዲያዎች በተለይም በዩቲዩብ እና ቴሌግራም ላይ እየተጫኑና ህገወጥ በሆነ መንገድ እየተሰራጩ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል።

ይህ ተግባርም ከላይ የተጠቀሰውን የሀገሪቱን የቅጅና ተዛማጅ መብቶች አዋጅን በቀጥታ የሚጥስ ከመሆኑ ባሻገር ከፍተኛ መዋዕለንዋይ በማፍሰስ የተለያዩ ይዘቶችን እያቀረቡ ለሚገኙ የመገናኛ ብዙሀን እና የፈጠራ መብት ባለሙያዎች የሚሰሩ የፕሮዳክሽን ኩባንያዎችና የስራ እድል በመፍጠር በስራቸው ለሚያስተዳድሯቸው ዜጎችም ዘርፈ ብዙ ጫና እያሳደረ ይገኛል።

ይህን መሰል ድርጊት በሚፈጽሙ አካላት ላይ በአዋጅ ቁጥር 410/1996 አንቀፅ 34 እና 36 መሰረት ለደረሰ ቁሳዊ ጉዳት ካሳ የመክፈል፣ ሆነ ተብሎ የሚፈጸም የመብት ጥሰት ከ5 እስከ 10 ዓመት ፣ ከፍ ባለ ቸልተኝነት የተፈጸመ እንደሆነ ደግሞ ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እንደዚሁም በማሻሻያ አዋጁ 872/2007 መሰረት ለተፈጸመው ወንጀል የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስከትል በህጉ ተደንግጓል።

ስለሆነም በዚህ ህገወጥ ድርጊት ላይ የተሰማራችሁ ግለሰቦችና ድርጅቶች በአዋጁ ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶች መጣስ የፍትሐብሔርና የወንጀል ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል ተገንዝባችሁ ከዚህ ድርጊት በአስቸኳይ እንድትቆጠቡ ባለስልጣኑ ያሳስባል።

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ትምህርት የሥርዓት ለውጥን ተከትሎ መቀያየር የለበትም››

- አቶ ሸዋንግዛው ጥላሁን

ምሕረት ሞገስ

ዋሲያ አንደኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት 50ኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን አክብሯል:: አዲስ አበባ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን አካባቢ ከ76 ዓመታት በፊት ይህችን ምድር የተቀላቀሉት አቶ ሸዋንግዛው ጥላሁን ደግሞ ትምህርት ቤቱን መሥርተዋል:: አቶ ሸዋንግዛው ለቤተሰባቸው ሰባተኛ ልጅ ናቸው:: ወላጆቻቸው እርሳቸውን ጨምሮ አምስት ሴት እና አራት ወንድ ልጆችን ሲወልዱ፤ ታታሪ በመሆናቸው በተትረፈረፈ ሃብት ዘጠኙንም ልጆች አንደላቅቀው ለማስተማር የሚያንሱ አልነበሩም::


በቤተሰባቸው ልዩ እንክብካቤ ያደጉት ልጆች ወላጆቻቸው በሕይወት እያሉ በ1958 ዓ.ም ለእያንዳንዳቸው ካርታ ያለው 380 ካሬ ሜትር ቦታ ተሰጥቷቸዋል:: ለየራሳቸው ቦታ ቢሰጣቸውም ቤት የሰራ ሰው አልነበረም:: የሁሉም መሬት ዛፍ ተተክሎበት ቆየ:: የአቶ ሸዋንግዛው አባት አቶ ጥላሁን በላይነህ ለልጆቻቸው ብቻ አይደለም፤ አልፈው ተርፈው በቅርብ ተከራይቶ ለሚኖር €€አባቴ‹‹ እያለ ለሚጠይቃቸው ወዳጅ ሳይቀር 200 ካሬ ሜትር ቦታ ሰጥተዋል:: ሙሉ መሬት እና ቤቱን ከማውረስ በተጨማሪ፤ አቶ ጥላሁን ለባለቤታቸው ማለትም ለአቶ ሸዋንግዛው እናት መርካቶ እና ሌሎችም አካባቢዎች የሚከራዩ ሱቆችን በባለቤትነት ይዘው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ እና ለፈለጉት ሰውም እንዲሰጡ ፈቅደው ነበር::

አቶ ሸዋንግዛው እንደሌሎቹ ወንድም እና እህቶቻቸው ሁሉ በልዩ እንክብካቤ ትምህርታቸውን ተከታተሉ:: በ1962 ዓ.ም ምኒልክ ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ፤ በአዋሽ ሸለቆ ባለስልጣን አሳይታ ልዩ ስሙ ዱብቲ በሚባል አካባቢ ሥራ ተመደቡ:: የልጅ ሸዋንግዛው እናት በረሃ በመሆኑ ልጃቸው እንዳይሔድ ከለከሉ::

አቶ ሸዋንግዛው የእናታቸውን ይሁንታ ባለማግኘታቸው ከአዲስ አበባ አልወጡም፤ ሥራም አልተቀጠሩም:: ከገነት ሆቴል በታች ከማሞካቻ በላይ ያሉት የሚከራዩት ሱቆች እና ቤቶች የእርሳቸው ቤተሰብ ቤት ሃብት ነበሩ:: ከፊት ለፊትም ገራዥ ነበራቸው:: መርካቶ ያሉት ሱቆች ተጨምረው ገቢያቸው ከፍተኛ በመሆኑ አልተቸገሩም:: የግድ ሥራ ለመሥራት አልተገደዱም:: ነገር ግን የሥራ ፍላጎት ስለነበራቸው፤ ትምህርት ቤት ለመክፈት አሰቡ::

በቅርብ አካባቢያቸው ቤት ተከራይተው ትምህርት ቤት ከፈቱ:: አባታቸው የታወቁ ነጋዴ እና ባለሃብት በመሆናቸው የእናታቸው ዕገዛ ታክሎበት ትምህርት ቤቱን ለመክፈት በገንዘብ እጥረት አልተቸገሩም:: ጭራሽ አስፋፍተው እስከ ሶስተኛ ክፍል የነበረውን ትምህርት ቤት እስከ ስድስተኛ ክፍል ለማስተማር እንዲቻል አድርገው ገነቡት:: በኋላ ግን ትምህርት ቤቱ በደርግ ስርአት ተወርሶ ነገር ግን በኋላ እንደፈለጉት አልሆነም፤ ትምህርት ቤቱ ለሕዝብ ተሰጠ:: የህዝብ ትምህርት ቤት ተሰኘ:: እርሳቸውም በመሠረቱት ትምህርት ቤት ተቀጣሪ ሆኑ:: ነገር ግን ተቀጥረው ለመስራትም አልተመቻቸውም፤ ስለዚህ በስደት አሜሪካ ሄዱ:: እነሆ ዛሬ ደግሞ ትምህርት ቤቱ አድጎ የተመሠረተበትን 50ኛ ዓመት አከበረ:: እርሳቸው ተጋባዥ እንግዳ ሆነው በመገኘት፤ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ እንኳን ለ50ኛ ዓመት በዓል አደረሳችሁ አደረሰኝ ለማለት በቁ::

እንዴት ከ50 ዓመት በፊት የግል ትምህርት ቤት አቋቋሙ? እንዴት ትምህርት ቤቱ የሕዝብ ሆነ? በምን ምክንያት ትምህርት ቤቱን ለቅቀው ተሰደዱ? የአገሪቱን የትምህርት ሥርዓት በተመለከተ ምን ይላሉ? በሚሉ እና በሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል:: መልካም ንባብ፡-



ፎቶ፡ አጋፔ ገዮን

**አዲስ ዘመን፡- በ1962 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ትምህርትዎን አጠናቀቁ፤ በ1964 ዓ.ም ትምህርት ቤት ከፍተው እንደነበር ሰምቻለሁ:: በዛ ዘመን ትምህርት ቤት የመክፈት ሃሳቡ እንዴት መጣልዎ?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** ትምህርቴን ካጠናቀቅኩ በኋላ ሥራ ባገኝም ወደ በረሃ አትሔድም ተብዬ ተከለከልኩ፤ በ1963 ዓ.ም ትምህርት ቤት ለመክፈት ፍላጎት ስለነበረኝ፤ ምን ዓይነት መንገድ ብጠቀም የተሻለ ይሆናል? ብዬ ፈቃድ አውጥቼ ሶስት ክፍል ቤት ተከራየሁ:: ህዳር 4 ቀን በ1963 ዓ.ም የምግብ ማብሰያ ኩሽናውን ቢሮ አድርጌ መምህራንን ቀጥሬ በሶስቱ ክፍል ማስተማር ጀመርኩ:: የተማሪዎቹ ቁጥር 68 ነበር፤ ክፍሎቹ በቂ አልነበሩም:: ስለዚህ ለእናቴ ትምህርት ቤቱን በቤተሰቡ መሬት ላይ አስፋፍቼ ልሥራ አልኳት:: እህት እና ወንድሞቼን አስፈቀደች:: የተቃወመ አልነበረም::

በጊቢው የነበረው ዛፍ ተቆረጠ:: በዛ ጊዜ የተቆረጠው ዛፍ ብቻ 990 ብር ተሸጠ:: ይህ ብር በጣም ብዙ ነበር:: ዛፉ ተሸጦ ገንዘብ ቢገኝም ጉቶውን መቁረጥ ፈተና ሆኖ ነበር:: ሰዎች በነፃ ነቅለው እንዲወስዱ ብፈቅድም፤ ብዙ ሰው ባለመውሰዱ የጉልበት ሰራተኛ ተቀጥሮ ጉቶ ተነቅሎ ሜዳው ተስተካከለ:: በአስቤስቶስ (በሲሚንቶ) ግድግዳቸው ያማረ 10 ክፍሎች ተሰሩ:: መጀመሪያ ለማስተማር ፈቃድ የተሰጠኝ እስከ ሶስተኛ ክፍል ብቻ ነበር:: ክፍሎቹ ተገንብተው ሲታዩ ትምህርት ቤቱ አስደሳች ሆነ፤ እስከ ስድስተኛ ክፍል እንዳስተምር ፈቃድ ተሰጠኝ፤ ሥራዬን ቀጠልኩ::

**አዲስ ዘመን፡- በ1964 ዓ.ም በግለሰብ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተከፈቱ ተማሪዎች በክፍያ ይማሩ ነበር?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** አዎ! ብዙ ቦታ የግል ትምህርት ቤቶች ነበሩ:: በጊዜው መምህራንን በተለይ አስራ ሁለተኛ ክፍል አጠናቀው ሥራ ያልያዙትን መቅጠር የተለመደ ነበር:: በመጀመሪያ መምህራን የሚቀጠሩት በ40 ብር ነበር:: ተማሪዎች ደግሞ በወር የሚከፍሉት ለ1ኛ ክፍል አንድ ብር ከሃምሳ፤ ለሁለተኛ ክፍል ደግሞ ሁለት ብር ነበር:: በየደረጃው ክፍያው እንደዛው እየጨመረ ይቀጥላል:: እስከ መስከረም 18 ቀን 1968 ዓ.ም ድረስ ትምህርት የሚሰጠው በክፍያ ነበር::

**አዲስ ዘመን፡-ትምህርት ቤቱን ሲከፍቱ ዓላማዎት ምን ነበር? ማትረፍ ነው? ወይስ ሌላ ዓላማ ነበርዎት?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** ከልጅነቴ ጀምሮ ስለዕድገት እና መልካም ዜጋን ስለማፍራት በተደጋጋሚ አስባለሁ:: ይህ ሊሆን የሚችለው በትምህርት እንደሆነ ልቤ ያምናል:: ስለዚህ መምህር መሆንንም አስብ ነበር:: መምህር ትልቅ የአገር ባለውለታ ነው:: ወታደር ዳር ድንበር ጠብቆ አገር እንደሚያቆየው ሁሉ፤ መምህርም ጥሩ ዜጋን በመቅረፅ አገር የሚረከብ ትውልድን የሚያፈራ ሰው ነው:: በአገራችን ብዙ ክብር እና ቦታ ተሰጥቶት ባይኖርም፤ የሚከፍለው መስዋዕትነት ቀላል አይደለም:: የመምህር አበርክቶ በህዝብ ዕድገት ላይ የሚኖረው ሚና ቀላል አይደለም:: ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ትምህርትን ለማስፋፋት እና ለማሳደግ አስቤ ነበር:: ገንዘብ ትርፍ ብፈልግማ ነጋዴ መሆን እችል ነበር::

ትምህርት ቤቱን የጀመርኩት ሙሉ ለሙሉ እናቴ ገንዘብ ሰጥታኝ ነው:: ከመርካቶ የሚገኘው ገንዘብ ወደ ሶስት ሺህ ብር እና ሌላም ተጨማሪ ገንዘብ ጨምራልኝ ለመምህራን ደሞዝ እና ለሌሎችም የትምህርት ቤት ወጪዎች ሳውል ነበር:: የተማሪዎቹ ክፍያ ለመምህራን ደሞዝም በቂ አልነበረም::

እናቴ ትምህርት ቤቱን እንድገነባ ከመፍቀድ አልፋ፤ በገንዘብ ስትደግፈኝ በጣም ደስተኛ ነበርኩ:: ግርማ አካሉ ከተባለው ከታላቅ እህቴ ልጅ ጋር ማስተማር ስንጀምር ጥረታችን በስነምግባር የታነፀ ብቁ ዜጋን ማፍራት ነበር:: የትልቋ እህቴ ልጅ ግርማ ግን ብዙ አልቆየም:: ለትምህርት ወደ ራሺያ ሔደ:: እኔ ግን ትምህርት ቤቱን ማጠናከር ቀጠልኩ:: የተማሪዎችም ቁጥር 258 ደረሰ። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ የደርግ መንግስት የግል ትምህርት ቤቶችን የሕዝብ እንዲሆኑ የሚደነግገውን አዋጅ አወጀ።

**አዲስ ዘመን፡- አዋጁ ሲታወጅ እና ትምህርት ቤትዎ ሲወረስ መሆኑን ሲሰሙ ምን ተሰማዎ?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** ሁልጊዜም መኝታዬ አጠገብ ሬዲዮ እና ትንሽ ቴፕ አስቀምጥ ነበር:: ደርግ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የሚታወጁ አዋጆችን ዕቀዳ ነበር:: በየዕለቱ የሚታተሙ ጋዜጣዎችን ተከታትዬ አነባለሁ፤ አሰባስባለሁ:: አዲስ ዘመን፣ ፖሊስ እና እርምጃው እንዲሁም ሌሎች ጋዜጦችንም እየገዛሁ እያነበብኩ ጠርዤ አስቀምጥ ነበር:: አዋጆችንም በተመሳሳይ መልኩ ጠዋት፣ ምሳ ሰዓት ላይም ሆነ ማታ በማንኛውም ሰዓት ሲታወጅ ቀድቼ አስቀምጥ ነበር::

መስከረም 18 ቀን 1968 ዓ.ም ጠዋት አንድ ሰዓት ላይ ተኝቼ ጊዜያዊው ወታደራዊ አስተዳደር የግል ትምህርት ቤቶችን የሕዝብ የሚያደርግ አዋጅ አውጇል ሲል እንደልማዴ አዋጁን ቀዳሁት:: ለጊዜው ደነገጥኩ፤ ግን የተወረሰው የግል ትምህርት ቤት ብቻ አይደለም:: ትልልቅ የእርሻ መሬቶች ፣ ሱቅ እና ቤቶች የተወረሰባቸው ብዙ ናቸው:: የእኔ የተለየ አልነበረም:: ከትምህርት ቤቱ በተጨማሪ የቤተሰቦቼ የከተማ ቦታ እና ብዙ ቤት ተወርሷል::

እናቴ በጠዋት ቤተክርስቲያን ሔዳ ነበር:: ሰዎች ነግረዋት ተደናግጣ ወደ ቤት መጣች፤ አመጣጧ ካልሰማሁ ቀሥ ብላ ነግራ ልታፅናናኝ ነበር:: ነገር ግን ወደ ቤት ስትገባ ሬዲዮ እያዳመጥኩ ነበር:: ቀድሜ መስማቴን ስታውቅ ‹‹ያለ የሌለ ገንዘቤን ሰብስቤ እሰጥሃለሁ፤ ሌላ ሥራ ትጀምራለህ›› አለችኝ:: ይናደዳል ብላ ሰግታ ነበር:: በኋላ ግን እውነት ለመናገር ምንም አልመሰለኝም:: ምክንያቱም አዋጁ የታወጀው በእኔ ላይ ብቻ አይደለም::

በማግስቱ መስከረም 19 በጠዋት እንደለመድኩት ትምህርት ቤት ሔድኩ፤ ምንም አልነበረም:: ያሉ ነገሮችን አዘጋጀሁኝ:: ከትምህርት ቢሮ ተደውሎ የሚያረካክቡ ሰዎች እንደሚመጡ እና እንድዘጋጅ ተነገረኝ፤ የነበረውን የዕለት መንቀሳቀሻ ገንዘብ ፔቲ ካሽ ሳይቀር አዘጋጀሁ::

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



አረካካቢዎች መጡ፡፡ በአካባቢያችን የኮንጎ ዘማች የወታደር ልጆች ይበዙ ነበር፡፡ የኑሮ ሁኔታቸው ዝቅተኛ ስለነበር የፅህፈት መሳሪያ እና መፅሃፍት ሳይቀር እየሠጠሁ ወደ 58 ተማሪዎች በነፃ አስተምር ነበር፡፡ አረካካቢዎች የትምህርት አመራር ኮሚቴ ይመረጣል አሉ፡፡

የትምህርት አመራር ኮሚቴ መምህራንንም ሆነ የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህር መቅጠርም ማባረርም ይችላሉ ተባለ፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ ተሰበሰበ፤ የትምህርት አመራር ኮሚቴ ለመሆን መስፈርት አልነበረውም፡፡ በኮሚቴነት ከተመረጡት መካከል ሶስቱ ጉሙሩክ ውስጥ የጉልበት ሥራ የሚሠሩ ነበሩ፡፡ በኮሚቴው ውስጥ ሌሎችም ደሀና የተማሩ ሰዎችም ነበሩ፡፡ እኔ በዛን ጊዜ ትንሽ ንብረት ያለው ሰው «አድሃሪ » ይባል ስለነበር፤ ለመመረጥ አልፈለግኩም፡፡

ህዝቡ ግን በሆታ «በፍፁም ልጆቻችንን በነፃ ሳይቀር ሲያስተምር የነበረ ሰው ከትምህርት ቤቱ መለየት የለበትም…» አለ፡፡ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ይሁን ተባልኩኝ፡፡ አዋጁ ላይ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር የኮሚቴው ሊቀመንበር ይሆናል ይላል፡፡ ስለዚህ ኮሚቴው የሚለውንም ሆነ የሚወስነውን ከመስማት አልፌ በትምህርት ቤቱ ጉዳይ ላይ ድምፅ መስጠት ቻልኩ፡፡ ነገር ግን ሌላ ነገር ተከሰተ፡፡ እኔ ትምህርት ቤቱን ስመራ ለራሴ የምወስደው ምንም ገንዘብ አልነበረም፡፡ በርዕሰ መምህርነት ስቀጠር ቀድሞ ደሞዝህ ስንት ነበር የሚል ጥያቄ ቀረበ፡፡ እኔ ደግሞ እውነቱን ተናገርኩ፤ የማገኘው ምንም ዓይነት ገንዘብ አልነበረም አልኩ፤ እኔም ሆንኩ የእህቴ ልጅ ስንሰራ በደሞዝ አልነበረም፡፡

አንዳንዶቹ የኮሚቴ አባላት ሆን ብለው በቀል በሚመስል መልኩ «ለራሱ ሲከፍል የነበረውን ደሞዝ በማስረጃ ያቅርብ ያለበለዚያ ለመክፈል እንቸገራለን» በማለታቸው ለረዥም ጊዜ ያለደሞዝ ቆየሁ፡፡ በኋላ በአንድ ወቅት የትምህርት ሚኒስቴር ስምንት የሚደርሱ የጊዜው አመራሮች የተወረሱ ትምህርት ቤቶችን እየዞሩ ሲጎበኙ፤ እኛ ትምህርት ቤት መጡ፡፡ የዛን ጊዜ የተማሪዎቻችን ቁጥር ከፍ ብሏል፤ የትምህርት ቤቱም ሁኔታ ተጠናክሮ በደንብ መስመር በመያዙ እና የሚመጡ የትምህርት መመሪያዎች በደንብ እየተተገበሩ ነበር፡፡

ሁሉን ነገር በሥነሥርዓት ይዤ ስለነበር ባዩት ሁኔታ በጣም ተደሰቱ፡፡ «ደሞዝ ስንት ነው?» የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡ፡፡ ደሞዝ እየተከፈለኝ አይደለም አልኩኝ፡፡ «ቤተሰብ የለህም እንዴ?» የሚል ጥያቄ አቀረቡ፤ «አዎ» የሚል ምላሽ ሰጠሁ፡፡ «ቤተሰብም ባይኖር ደሞዝ ሊከፈለው ይገባል» ብለው የትምህርት አመራር ኮሚቴውን ጠየቁ፡፡

የትምህርት አመራር ኮሚቴው «ደሞዙን ለመወሰን እርሱ መነሻ ደሞዝ ስለሌለው ተቸግረን ነው» ሲል ምላሽ ሠጠ፡፡ «እንደዛ ቢሆን ሰው እየሠራ እንዴት አይበላም? በአስቸኳይ ደሞዙን ወስናችሁ እንድታሳውቁን፡፡» ብለው ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ በአጋጣሚ እናቴ የገዛችልኝ መኪና ነበረኝ፡፡ አንዱ የኮሚቴው አባል «እርሱ የሕዝብ ገንዘብ እየበላ ተንደላቆ መኪና እየነዳ የሚኖር ነው፡፡» አለ፡፡

ሌላ የኮሚቴ አባል ደግሞ «ታዲያ መኪና ቢነዳ ምን አገባን የሠራውን ትምህርት ቤት ወርሰን እያሠራነው የግል ሕይወቱ ውስጥ መግባት የለብንም፡፡» አሉ፡፡ እኔ ወጥቼ ኮሚቴው ተነጋግሮ በጊዜው እርግጠኛ ባልሆንም የቆረጡልኝ ደሞዝ ከ200 ብር አይበልጥም ነበር፡፡ ነገር ግን ደሞዝ ባይከፈለኝም ስራዬ አልተደናቀፈም ነበር፡፡ ከዛ ተነስተን ትምህርት ቤቱ አደገ፤ ተማሪው በሺ መቆጠር ጀመረ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የመሠረቱትን የለፉበትን ትምህርት ቤት ትተው የሄዱት መቼ ነው? ለምን ሔዱ? ይህንን ውሳኔ ለመወሰን ያደረስዎ ምን ነበር?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** ጊዜው 1983 ዓ.ም ነበር፡፡ ኢህአዴግ አገሪቷን ሲቆጣጠር በየቀበሌው ሰላምና መረጋጋት፤ በየትምህርት ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተቋቋመ፡፡ መምህራኑ ኮሜርስ አካባቢ አውሮራ ጎን ያለው የኢህአዴግ ተወካይ ጋር በትምህርት ሰዓት ስብሰባ ብለው በመሄዳቸው ተማሪዎቹ በበቂ ሁኔታ የሚማሩበት ዕድል ተመናመነ፡፡ እኔ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በመሆኔ ብዙ አለመግባባት ተፈጠረ፡፡

ቦታው ላይ በመሆኔ ትምህርት ቤቱን የመምራት ሙሉ ኃላፊነት ነበረብኝ፤ ስለዚህ መምህራኖቹን እባካችሁ ተው አልኩኝ፡፡ ኃላፊ የተባለው ሰው ታጋይ ነው፤ መምህራኖቹን በአግባቡ ሥራችሁን ሥሩ በማለቴ ቢሮ ጠርቶ መሳሪያ አስቀምጦ እጅግ አዋርዶ ሰደበኝ፡፡ ተስፋ ቆርጬ እኔ ልጆች ወልጃለሁ፤ አንተንም ብወልድህ አደርስሃለሁ፤ ለህዝብ መጥተናል እያላችሁ ይህን ያህል ሰው ማዋረድ ተገቢ አይደለም፤ ብዬ ተናገርኩት፡፡

አስተማሪዎችን ትንቃለህ፤ ታዋርዳለህ ብሎ ለመገሰፅ ሞከረ፡፡ እኔ በፍፁም ሰው አልንቅም፤ ሰውን ካላከበርኩ ክብር እንደማላገኝ አውቃለሁ፡፡ እርሱ የነገሩህን ብቻ ሳይሆን እኔንም እኩል ማዳመጥ አለብህ አልኩት፡፡ ስንነጋገር አንድ ሌላ እንደእርሱ አይነት መሣሪያ የያዘ መጥቶ ሲያዳምጥ የነበረ ሰው «እርሳቸው ይሂዱ እኔ እፈልግሃለሁ» አለው፡፡ «ትምህርት ቤት ድረስ እመጣለሁ፤ እንደዚህ ህዝብ ላይ እያላገጡ መኖር አይቻልም፡ አሁን ከቢሮዬ ውጣ» አለኝ፡፡

ከቀናት በኋላ ወደ ትምህርት ቤት መጥቶ እርሱ ጋር ከሚመላለሱ መምህራኖች ጋር ሲያወራ ቆይቶ፤ « ከአሁን በኋላ ወደ እኔ ሊመጡ ሲሉ ምንም ዓይነት ተፅዕኖ እንዳትፈጥርባቸው» አለኝ፡፡ እኔም እሺ አንተ ጋር ሁለት እና ሶስት ሆነው ሲመጡ ተማሪዎቹ ስለማይማሩ ተማሪዎቹን ወደ ቤታቸው እሰዳቸዋለሁ አልኩት፡፡ ትቶኝ ሔደ፡፡ ወዲያው በሳምንቱ ቅዳሜ ከሰዓት የትምህርት አመራር ኮሚቴው እና መምህራኖቹ እንዲገኙ አዘዘ፡፡

በዕለቱ ሶስት ታጣቂዎችን ይዞ ተገኙ፡፡ ሁለቱ ታጣቂዎች ስብሰባው ውስጥ ገቡ፤ አንዱ ታጣቂ እደጅ ቆመ፡፡ በሰዓቱ እነዛ የቅሬታ ኮሚቴ አባላት የተባሉት መምህራኖች ብዙ ነገር ተናገሩ፡፡ «ይንቀናል፤ ትሸታላችሁ ይለናል» አሉ፡፡ ነገር ግን እኔን የሚለካኝ የትምህርት ቤቱ ውጤታማነት ነበር፡፡ በዛን ጊዜ በዞኑ ጠንካራ ተብሎ የሚጠራ ትምህርት ቤት ነበር፡፡ ለዛ ደረጃ ያደረስኩት ብዙ ለፍቼ ነው፡፡

የትምህርት አመራር ኮሚቴዎቹ ደግሞ ቅሬታ ያቀረቡትን መምህራኖች «እስከዛሬ ምንም ሳትሉ ለምን ዛሬ እንደዚህ ትላላችሁ?» አሏቸው፡፡ በእርግጥ እኔ ተማሪዎች በሳምንት ሁለት ጊዜ ጥፍራቸውን እንዲቆረጡ እና አጠቃላይ ንፅህናቸውን እንዲጠብቁ ፀጉራቸውን እንዲያበጥሩ እና ንፁህ እንዲሆኑ እቆጣጠር ነበር፡፡ ተማሪዎቹም ጎበዝ ነበሩ፡፡ «እኛ ክትትል እንደሚደረግብን፤ መምህራኖችስ ለምን ንፅህናቸውን እንዲጠብቁ አትከታተሉም፤ ጫማቸው የሚሸት መምህራኖች አሉ፡፡» ብሎ ስሙን ሳይፅፍ በጣም የማከብረው አንድ ጎበዝ ተማሪ በሃሳብ መስጫ ሳጥን ውስጥ የተቀነባበረ አስተያየት ፅፎ አገኘሁ፡፡ ማንነቱን ደረስኩበት፤ ሃሳቡም ትክክል ነበር፡፡ የመምህራን ስብሰባ ላይ በተማሪዎች የተፃፈውን ተናገርኩ፤ መምህራን ንፅህናችሁን ጠብቁ በማለቴ በዕለቱ ያንን ስብሰባ አስታውሰው ወቅሰው ተናገሩ፡፡

ቢሮው ውስጥ ሲያዋርደኝ የነበረ ሰው በድጋሚ በሰዎች ፊት አዋርዶ መናገር ጀመረ፡፡ ስነስርዓት ያዝ አልኩት፡፡ ከትምህርት ቤቱ አጠገብ ቀበሌ 24 አለ፡፡ እዛ የሠፈሩ ታጣቂዎች ነበሩ፡፡ እኔ ታጣቂዎቹን ሳይቀር ማታ ማታ አስተምር ነበር፡፡ ነገሩ ጠንከር ሲል ሃይለኛ ራስ ምታት ጀመረኝ፤ ከዛ ወስዶ ሊያስረኝ እንደሚችል ገመትኩ፤ ስለዚህ ዶክሜንት አምጥቼ እንዳሳይ ይፈቀድልኝ አልኩ፡፡

ሲፈቅዱልኝ ቀድሜ በሳምሶናይት ያዘጋጀሁትን የተዘጋጀ ሰነድ ከቢሮዬ ይዤ በግቢው በዋናው በር ሳይሆን፤ በሴቶች መፀዳጃ ቤት አድርጌ ወደ ሰው ጊቢ ዘለልኩ፡፡ አቆራርጬ ቤቴ ገባሁ፤ ራሴን ሳትኩ በኃይል ነሰረኝ፡፡ ብዙ ደም ፈሰሰኝ፡፡ ባለቤቴም በጊቢው ውስጥ ያሉ እህት ወንድሞቼ መላው ቤተሰቤ ተደናገጠ፡፡ ለሶስት ቀን ሆስፒታል ተኛሁ፡፡

ከሆስፒታል ስወጣ ባለቤቴ ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት የቅሬታ ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ የሆኑትን ሰው ቀጠሮ አስይዛ በጋራ አብረን አስረዳን፡፡ ሲያዋርደኝ የነበረው ቂርቆስ አካባቢ የነበረው ሰው እና ቅሬታ አቀረቡ የተባሉ የቅሬታ ሰሚ መምህራን ስለጉዳዩ ማስረጃ ይዘው እንዲያስረዱ እኔም ማስረጃዬን እንዳቀርብ ተነገረኝ፡፡ የቅሬታ ሠሚ ኮሚቴዎች ተብለው እኔን ሲያሰቃዩኝ የነበሩት መምህራን ብዙ ጥፋት ነበረባቸው፤ ስለዚህ ሰነዳቸውን ማደራጀት ከባድ አልነበረም፡፡ በቀጠሮ ቀን ተገኘሁ፤ ኮሚቴዎቹ ግን ቀሩ፡፡

ዋና ሰብሳቢው በብስጭት ማስረጃቸውን ይዘው እንዲያቀርቡ በድጋሚ አዘዛቸው፡፡ እኔ በሙሉ አቀረብኩ፡፡ እነርሱ ግን ማስረጃ ለማቅረብ ሁለት ወር ጠየቁ፡፡ «አይሆንም ሁለት ወር ብዙ ነው፤ የከሰሳችሁት ውሸታችሁን ነው ማለት ነው፡፡» አላቸው፡፡ ተጨማሪ ዕድል ቢሰጣቸውም በድጋሚ ማስረጃ ማቅረብ አቃታቸው፤ በመጨረሻም ከስራዬ አግደውኝ ነበር፡፡ ወደ ሥራ እንድመለስ፤ በምትካቸው አዲስ ኮሚቴ እንዲመረጥ ለደቡብ ትምህርት ዞን ፅህፈት ቤት ደብዳቤ ተፃፈ፡፡

መምህራን በትምህርት ሰዓት ከጊቢ መውጣትም ሆነ ስብሰባ መሔድ እንደማይችሉ በመግለፅ በመመሪያ መሠረት ሥራዬን እንድቀጥል ተነገረኝ፡፡ ያ እንደዛ ሲያዋርደኝ የነበረ ሰው ተጠርቶ በድጋሚ ያንን ድርጊት እንዳይፈጽም ማስጠንቀቂያ ተሰጠው፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ በሳምንቱ አሜሪካን እሄድ ነበር፡፡ ሰኞ ግን ሥራ ገባሁ፡፡ በሥራ ላይ ቂም በቀል የለም፤ የሚሰማችሁን አቅርባችኋል የሚዳኘን ህግ ነው፤ በሥራ ሰዓት ስብሰባ መሄድ አትችሉም ብዬ ተናግሬ ስራዬን ቀጠልኩ፡፡

እሁድ የወላጆች ስብሰባ ነበር፡፡ አርብ እስከ ምሽት ሶስት ሰዓት ሥሠራ ቆይቼ ማንም ሳይሰማ ቅዳሜ ጠዋት እንገናኛለን ብዬ ወደ ቤቴ ሄድኩኝ፡፡ እኔ ግን ቅዳሜ ጠዋት ወደ አሜሪካ ለመሄድ ኤርፖርት ተገኘሁ፡፡ መሔዴን ማንም ስለማያውቅ ከአገር እንዳይወጡ ከተዘረዘሩ ስሞች ውስጥ የእኔ ስም አልነበረም፤ በዚህ መልኩ የመሠረትኩትን ትምህርት ቤት ትቼ ሄድኩ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥ ወደ አሜሪካ የሄዱት በሁኔታው ተማረው ነው ወይስ ቀድሞም አሜሪካ መሄድ ይፈልጉ ነበር?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** በፍፁም አሜሪካን መሔድ አልፈልግም ነበር፡፡ በዛ በ45 ዓመት እድሜዬ አሜሪካንን እንዴት አስባለሁ? በ45 እና በ46 ዓመት ስደት እና ኑሮን ከዜሮ መጀመር በጣም ከባድ ነው፡፡ ከዛ በፊትም ዕድሉ ነበረኝ፡፡ ግን አልሔድኩም፡፡ ፈጣሪ በዚያ ኑር ልጆችህንም በዛ አሳድግ ሲል በዛ ዕድሜ ከአገሬ ወጣሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የትምህርት ቤቱን 50ኛ ዓመት ለማክበር ተጠሩ፤ ምን ተሰማዎት?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** በጣም ተደስቻለሁ፤ በአጥር ዘልዬ እስከ መውጣት ደርሼያለሁ፡፡ አሁን ግን ተገቢው ክብር ተሰጥቶኝ ትምህርት ቤቱም እዚህ ደረጃ ላይ ደርሶ በማየቴ ደስ ብሎኛል፡፡ ያስተማርኳቸውን ተማሪዎቼን አሜሪካንም በተለያዩ ቦታዎች አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ዋሽንግተን ሆስፒታል ውስጥ ሌሎችም ትልልቅ ቦታዎች ላይ ደርሰው ያገኘኋቸው አሉ፡፡ በሆነው ባለውና ባለፈው በሁሉም ነገር ደስተኛ ነኝ፡፡ ጓደኞቼ አልፈዋል፡፡ እኔ ጤነኛ ነኝ፡፡ 76 ዓመቴ ነው፤ ጡረታ ወጥቻለሁ፡፡ ነገር ግን ረዥም ሰዓት ኮምፒውተር ላይ አሳልፋለሁ፡፡ መፅሃፍ አነባለሁ፤ እዋኛለሁ፤ እስፖርት እሰራለሁ፡፡ ምንም አይነት ችግር የለብኝም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከ50 ዓመት በፊት ትምህርት ቤት ከፍተዋል፡፡ መምህር ነበሩ፤ ውጪም ኖረዋል፡፡ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓትን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** የትምህርት ጥራት በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወረደ ነው፡፡ ቀድሞም ቢሆን መምህራን እና ተማሪዎች ግንኙነታቸው የአባት እና የልጅ መሆን አለበት፡፡ ከአገር ከወጣሁ በኋላ ተማሪዎች መምህራንን ይገመግሙ ነበር ሲባል ሰምቼያለሁ፡፡ መምህራን ተከብረው በተሰጣቸው ኃላፊነት ትውልዱን የሚቀርፁ መሆን አለባቸው፡፡ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን እና መምህራኖችን አክብረው ቀለም መቅሰም አለባቸው፡፡ በቀዳማይ ኃይለስላሴ ጊዜ በቀዳማይ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበርኩ፡፡ የትምህርት ስርዓቱ ጥሩ ነበር፡፡

በደርግ ጊዜ ግን ሥርዓቱን ለማራመድ የሚያስችል የትምህርት ስርዓት ተቀረፀ፡፡ ብዙ ችግር የተፈጠረው በዛ ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን አሁንም በተመሳሳይ መልኩ መምህሩ ምን ማስተማር አለበት ተማሪውስ ምን መማር አለበት ለሚለው የነጠረ መመሪያ የለም፡፡ በዚህ ምክንያት በትምህርት አመርቂ ውጤት ማግኘት አልተቻለም፡፡

በእርግጥ የዛሬ የኢትዮጵያ ወጣቶች ምጡቅ አዕምሮ ያላቸው ብዙ መሆናቸውን ተከታትዬ አይቻለሁ፡፡ አሜሪካን ድረስ ሔደው የሚማሩ፤ በኢትዮጵያም ያሉ ብዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን በአግባቡ አልተያዙም፡፡ ዋናው ችግር ግን ፖለቲካው እና ትምህርት የተለያዩ አለመሆናቸው ነው፡፡ በተጨማሪ የችግር መነሻ መንግስት እና ፖለቲካው ነው ብንልም፤ ዋናው ግን የህብረተሰቡ በአግባቡ ኃላፊነትን አለመወጣትም ዋነኛው መንስኤ ነው፡፡ ወላጆች አጠቃላይ ማህበረሰቡ ግፊት አያደርግም፡፡ መስተካከል ያለበት ሥርዓተ ትምህርት እንዲስተካከል ሕዝብ መጠየቅ አለበት፡፡

ትምህርት የሥርዓት ለውጥን ተከትሎ የሚቀያየር መሆን የለበትም፡፡ በአፍሪካ ውስጥ የተለመደው አንድ መንግስት ሔዶ ሌላ ሲተካ የትምህርት ስርዓቱ ላይም የተሠራውን አፍርሶ እንደአዲስ መጀመር ይስተዋላል፡፡ ይሔ ትክክል አይደለም፡፡ ይህ እንዳይሆን ሕዝብ መታገል አለበት፡፡ ትምህርት ከሁሉም ነገር በላይ ነው፡፡ የትኛውም መንግስት ይምጣ የትኛውም መንግስት ይሒድ ከትምህርት ሥርዓቱ ጋር መገናኘት የለበትም፡፡ ማንኛውም መንግስት የትምህርት ሥርዓቱን እንደፈለገው የማድረግ መብት የለውም፡፡ የትኛውም መንግስት የሚመጣው በሕዝብ ምርጫ ነው፡፡ ግን ደግሞ መሥራት ያለበት ለህዝብ የሚበጅ ነገር ብቻ ነው፡፡ በእርግጥ እዚህ ላይ የሕዝቡም ዳተኝነት አለ፡፡

**አዲስ ዘመን፡-አገር እንድታድግ እና እንድትለወጥ ቀጣይነት ያለው የትምህርት ስርዓት እንዲኖር ምን መሠራት አለበት?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** እንደኔ ሃሳብ ቀጣይት ያለው ሥርዓተ ትምህርትን መቅረፅ የሚችሉ ብዙ ምሁራን አሉ፡፡ ስርዓተ ትምህርቱ ልክ እንደ ህገመንግስት ምሁራን ተቀምጠው ከሃይማኖትም ሆነ ከብሔር ተፅዕኖ ውጪ ሆነው ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ይህ ሥርዓት እንደ ህገመንግስት ሁሉም ሊመራበት ይገባል፡፡ አሁን የሚታዩት ባለምጡቅ ዓዕምሮ ልጆች ዘመኑ የቴክኖሎጂ በመሆኑ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው እንጂ ከትምህርት ቤት ባገኙት ዕውቀት ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡

እንደሚታየው የሥርዓተ ትምህርት በየጊዜው እየተለወጠ ነው፡፡ መጀመሪያም ቢሆን ተማሪዎች 10ኛ ክፍል ተፈትነው ትምህርት እንዲያቆሙ መደረጉ በየትኛውም ዓለም የሌለ ነው፡፡ በሰለጠነውም ዓለም ትምህርት እስከ 12ኛ ክፍል ነው፡፡ አሜሪካንም ተመሳሳይ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ግን ትምህርት ከፖለቲካ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ነገር ግን ቋሚ እና አገሪቷን ሊወክል የሚችል የትምህርት ሥርዓት መኖር አለበት፡፡ እዚህ ላይ ብዙ ማለት ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በውጪው ዓለም ለትምህርት እና ለምርምር ዘርፍ የሚመደበው በጀት ከፍተኛ ነው፡፡ ከህዝብ ባሻገር መንግስትስ ለትምህርት ዘርፍ በጀት ከመመደብ ጀምሮ የሚሰጠው ትኩረት ምን ያህል መሆን አለበት?**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** ለትምህርት ዘርፉ በቂ በጀት ሊያዝለት ይገባል፤ ነገር ግን እንደማውቀው ከሆነ ለትምህርት ዘርፉ የሚወሰነው በጀት በቂ አይደለም፡፡ በቅድሚያ መንግስት በትምህርት ዘርፍ ላይ የሾማቸው ሰዎች የትምህርት ችግር ምንጩ ምንድን ነው የሚለውን ማየት አለባቸው፡፡ አገሪቷን ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ የሚቻለው ተረካቢ የሚኖርበትን ሁኔታ በመፍጠር ነው፡፡ ስርዓተ ትምህርቱ ላይ ብዙ ነገሮችን እያየን ነው፡፡ የሚያስተውል የሚመረምር ትውልድ ካልተፈጠረ ዞሮ ዞሮ አገርን መግደል ነው፡፡ ያልተማረ ትውልድ የአገርን እግር መተብተቡ አይቀርም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ሸዋንግዛው፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

# ማህደረ ጤና

## የደም ማነስ በሽታ ብዙ ሰዎችን የሚያጠቃው ስምንድነው?

**እፀገነት አክሊሉ**

የደም ማነስ በሽታ የሚከሰተው በሰውነታችን ውስጥ የሚገኙ ቀይ የደም ህዋሳት ቁጥር ሲያንስ ወይም በውስጣቸው የሚገኘው ሄሞግሎቢን የሚባለው ሞለኪውል መጠን ሲያንስ መሆኑን የህክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ቀይ የደም ህዋሳት በደማችን ውስጥ ከሚገኙ ብዙ አይነት ሌሎች ህዋሳት አንደኛው ሲሆኑ ዋነኛ ስራው በደም ስራችን ውስጥ አክስጅንን ከቦታ ቦታ ማዘዋወር ነው። ሁሉም የሰውነት ክፍሎቻችን ይህንን አክስጅን ከምግብ የምናገኘውን ንጥረ ነገሮች ወደ ኃይል (ጉልበት) ለመቀየር ይጠቀሙበታል። በመሆኑም የደም ማነስ በሚኖርበት ጊዜ የሰውነታችን ህዋሳት በሙሉ በቂ ኃይል ስለማያገኙ ድካም፣ አቅም ማጣት እና የመሳሰሉ ምልክቶች ይስትዋላሉ።

የደም ማነስ ህመም ብዙ ሰዎችን ያጠቃል። ይሄ ችግር በተለይ እንደኛ ባሉ ታዳጊ አገራትና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገራት ላይ በብዛት ያታያል። በተለይም በህጻናት፣ እርጉዝ ሴቶች እና በእድሜ የገፉ አረጋውያን ላይ የችግሩ ተጋላጭነት ይበልጥ የጨመረ መሆኑን ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡

እንደ ዓለም ጤና ድርጅት መረጃ በዓለም ላይ ካሉ ሰዎች 25 በመቶ የሚደርሱት ወይም ከአራት ሰው አንዱ የደም ማነስ በሽታ ይገኝበታል፤ ይህም ወደ 1 ነጥብ 62 ቢልየን ሕዝብ በዓለም ላይ የደም ማነስ ችግር ውስጥ መሆኑን ያመላክታል ።

50 በመቶ ያህሉ ለትምህርት ያልደረሱ ህፃናት የደም ማነስ ህመም አለባቸው፣ የሚለው ይኸው የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ ከእርጉዝ ሴቶች መሃል 40 በመቶ የሚደርሱት ለደም ማነስ ህመም የተጋለጡ ናቸው። ይህ መሆኑ ደግሞ በእርግዝና እና ወሊድ ጊዜ ለተለያዩ ህመሞች ከማጋለጡም በላይ ለእናቶች ሞት ምክንያት በመሆን ይጠቀሳል።

### የደም ማነስ በምን ምክንያት ይፈጠራል ?

በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው የደም ማነስ በቀይ የደም ሴሎች (ህዋሳት) ቁጥር ማነስ ወይም በውስጣቸው የሚገኘው ሄሞግሎቢን መጠን መቀነስ የሚመጣ ችግር ነው። ይህ ደግሞ በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ይከሰታል ተብሎ በዓለም ጤና ድርጅት ተቀምጧል።

1. **ሰውነታችን በቂ የሆነ ቀይ የደም ሴል (ህዋሳት) ሳያመርት ሲቀር፡-** መቅኒ (bone marrow) ቀይ የደም ሴሎች (ህዋሳት) የሚመረቱበት ቦታ ነው። ለግንባታው የሚያስፈልጉት ንጥረ ነገሮች አይረን (Iron፣ ቪታሚን ቢ 12 /Vitamin B 12፣ ፎሊክ አሲድ Folic acid በ በቂ ሁኔታ ካላገኘን የምርት መጠናቸው ስለሚቀንስ የደም ማነስ ይከሰታል።

2 **ቀይ የደም ህዋሳት በተለያዩ ምክንያቶች ቶሎ ቶሎ የሚሞቱ ከሆነ፡-** ቀይ የደም ሴሎች በአማካይ 120 ቀን ወይም 3 ወር ያህል ይኖራሉ። ከዛ መቅንያችን በሚያመርተው በአዲስ ሴሎች (ህዋሳት) ይተካሉ። ለዚህም ነው አንድ ጤነኛ ሰው ሌላ ችግር እስከሌለበት ድረስ በየሶስት ወሩ ደም ቢሰጥ ችግር የለውም የሚባለው። የተለያዩ አይነት በሽታዎች ለምሳሌ ወባ፣ ቀይ የደም ህዋሳት ከላይ ከተገለጸው ጊዜ ቀድመው ቶሎ እንዲሞቱ በማድረግ የደም ማነስ በሽታ እንዲፈጠር ያደርጋሉ።

3 **የደም መፍሰስ፡-** ከአደጋ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ከፍተኛ የደም መፍሰስ የሚጠቀስ ሲሆን፣ ሴቶች ከወር አበባ ጋር ተያይዞ ብዙ ደም የሚፈሳቸው ከሆነ ወይም በወሊድ ጊዜ የሚከሰት ከፍተኛ የደም መፍሰስ ለአጣዳፊ እና ዘላቂ የደም ማነስ ሊያጋልጥ ይችላል።

አደገኛ የደም ማነስ ምክንያት የቫይታሚን ቢ 12 እጥረት ነው። ስለዚህ፣ ምንም እንኳን በአመጋገብ በኩል በቂ ውሃ በማይጠጣበት ጊዜ ሊታይ የሚችል እውነት ቢሆንም፣ ይህ ምክንያት በውስጡ የበለፀጉ ምግቦችን በማስተዋወቅ በቀላሉ የሚስተካከል ነው:: ነገር ግን የቫይታሚን ቢ 12 ጉድለት መንስኤ የጄኔቲክ ችግር ወይም የአንጀት ሁኔታ በሚሆንበት ጊዜ ለአደገኛ የደም ማነስ ችግር የመጋለጡም መጣን በዛው ልክ ከፍ ያለ ይሆናል፡፡

ስለዚህ አንጀት ቫይታሚን ቢ 12 ን በበቂ ሁኔታ መምጠጥ በማይችልበት ጊዜ ይህ አደገኛ የደም ማነስ ይታያል። ይህ በአጠቃላይ በቂ ሞለኪውሎች (ውስጣዊ ምክንያቶች በመባል የሚታወቁት) በመኖራቸው ምክንያት በመደበኛ ሁኔታዎች ውስጥ እነዚህ ቫይታሚኖች በምግብ ውስጥ በመግባት በአንጀት ይመረታሉ።

አሁን፣ አንጀቶች ለምን በቂ ውስጣዊ ነገር አያደርጉም? ቢባል ምክንያቱ የአንጀት መታወክ እና በጄኔቲክ ስህተቶች ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በጨጓራ ህመም ምክንያት የሆድ ውስጠኛው ሽፋን ሲዳከም ነው። እናም ይህ አንጀቶች ከዚያ በኋላ ቫይታሚን ቢ 12 እንዲወስዱ ይገደዳል። ቫይታሚን ቢ 12 በዚህ መንገድ መወሰዱ ደግሞ ለደም ማነስ ችግር ያጋልጣል፡፡

አደገኛ የደም ማነስ መንስኤዎች መከላከልን አስቸጋሪ ነው፤ እንደ እድል ሆኖ፣ በፍጥነት ከተያዙ፣ በህክምናው ብዙ ውጤቶችን ማምጣት ይቻላል።

### የደም ማነስ ካለብን ምን ምልክቶች እናያለን?

የደም ማነስ በተለያዩ ምክንያቶች የሚመጣ ስለሆነ ምልክቶቹ እንደ ምክንያቶቹ ሊለያዩ ይችላሉ። በዋነኝነት ግን የድካም ስሜት፣አቅም ማጣት፣ የትንፋሽ ማጠር፣ የከለር መገርጣት ወይም ነጭ መሆን፣ አንዳንዴ ደግሞ እንደ በሽታው አይነት የአይን እና ቆዳ ከለር ቢጫ መሆን፣ የማዞር ስሜት፣ ራስ ምታት፣ የትኩረት ማጣት በተለይ ህጻናት ላይ ትምህርት የመማር አቅማቸውን እና የማስታወስ ችሎታቸው እንዲቀንስ ማድረግ ይጠቀሳል።

አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ምልክቶች ላይታዩና የግድ የላብራቶሪ ምርመራ ሊያስፈልግ የሚችልበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል።

### በላብራቶሪ የደም ምርምራ የደም ማነስ አለ ምንለው መቼ ነው ?

እንደ ዓለም ጤና ድርጅት አገላለጽ በላብራቶሪ የደም ምርመራ የደም ማነስ አለ የምንለው ለወንዶች የሄሞግሎቢን መጠን ከ 13 mg/dl በታች ሲሆን ለሴቶች ደግሞ ከ 12 mg/dl በታች ሲሆን ነው። ይህ ቁጥር እንደ እድሜያችን፣ የእንቅስቃሴያችን አይነት እና የምንኖርበት ቦታ ሊለያይ ይችላል:: ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያ ከፍታማና ተራራማ ቦታዎች በሚበዙበት አካባቢ ለምንኖር ሰዎች የሄሞግሎቢን መጠን ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል።

በምርመራ ወቅት ከሄሞግሎቢን በተጨማሪ የደም ማነስን ሊያመጡ የሚችሉ ምክንያቶችን በተመለከተ የህክምና ባለሙያዎች ምርመራ ሊያደርጉ ይችላሉ። ለምሳሌ የቫይታሚን ቢ12፣ የፎሊክ አሲድ መጠን እና የአይረን (የብረት ንጥረ ነገር) አብሮ ሊመረመር ይችላል።

### የደም ማነስ እንዴት ይታከማል ?

የደም ማነስ በግዜ ካልታከመ ዘላቂ ችግር ሊያመጣ ይችላል። ህክምናውም እንደ ምክንያቱ ይለያያል። ለምሳሌ ህፃናት ከአይረን (የብረት ንጥረ ) ጋር በተያያዘ ለሚከሰት የደም ማነስ በጣም ተጋላጭ ናቸው። ይሄ ደግሞ አካላዊ እና አእምሮአዊ እድገታቸውን ይጎዳዋል። በተለይ በትምህርት ዕድሜ ላይ ያሉ ህፃናት ትምህርት የመቅሰም ችሎታቸውን ይቀንሰዋል። ስለዚህ ተገቢ የሆነ መደበኛ ምርመራ ህፃናት ማግኘት ይኖርባቸዋል።

የአይረን እጥረት ያለባቸው ከምግብ ጋር ወይም በእንክብል መልክ ንጥረ ነገሩን እንዲያገኙ በማድረግ ህክምና ማግኘት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ የአይረን ይዘታቸው ከፍተኛ የሆኑ ምግቦች ማለትም ቀይ ስጋ፣ አሳ፣ ባቄላ፣ ጥቁር ጎመንና አተር የመሳሰሉት አዘውትሮ መመገብ የደም ማነስን ለማከም ይጠቅማል።

በዚህ መስተካከል ያልቻለን የደም ማነስ ችግር ግን እንደሁኔታው ሀኪሞች የአይረን እንክብሎችን በማዘዝ እንዲስተካከል ሊያደርጉ ይችላሉ። በተጨማሪም እንደ ብርቱካን፣ እንጆሪ፣ ቃሪያና ቲማቲም ያሉ ከፍተኛ ቫይታሚን ሲ ያለባቸው ምግቦች መመገብ በራሱ ከምግብ የምናገኘውን አይረን ወደ ሰውነታችን ተብላልቶ እንዲገባ ያግዛል።

እንደኛ ባሉ ታዳጊ አገራት ውስጥ የአንጀት ውስጥ ጥገኛ ተዋሲያን ሌላው የደም ማነስ ምክንያቶች ሊሆኑ ስለሚችሉ በተለይም ህፃናት ላይ ለዚህ የሚሆን ተገቢ ምርመራና ህክምና ማግኘት አለባቸው። እርጉዝና የሚያጠቡ እናቶች ደግሞ ለደም ማነስ በጣም ከፍተኛ ተጋላጭ ስለሆኑ እነሱም ተገቢውን ክትትልና ህክምና ማግኘት አለባቸው፡፡ በእርግዝና ወቅት የአይረን እጥረትና የፎሊክ አሲድ እጥረት ለደም ማነስ ከሚያጋልጡ ምክንያቶች ዋንኞቹ ሆነው በዓለም ጤና ድርጅት መረጃ ውስጥ የተካተቱ በመሆኑ እጥረቱ እዳይከሰት ነፍሰ ጡር እናቶች ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው ይመከራል፡፡

ቫይታሚን ቢ 12 ከአስራ ሦስቱ አስፈላጊ ቪታሚኖች አንዱ ነው እና “የተመረቱ” ቀይ የደም ሴሎችን በማምረት ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም የፊዚዮሎጂ ሂደቶች የሚያነቃቃ ስለሆነ ከአመጋገብ ጎን ለጎን በጣም አስፈላጊ ነው። አጥንት በቂ የቫይታሚን ቢ 12 ደረጃዎች ከሌሉ ሰውነት አስፈላጊውን የኦክስጂን ትራንስፖርት ለማረጋገጥ በቂ ቀይ የደም ሴሎችን ማምረት አይችልምና።

> **ሰዎች ከላይ የገለጽናቸው ምልክቶችን እንዳዩ በቶሎ ወደ ጤና ተቋም መምጣት ቢችሉ ውጤታማ ይሆናሉ ነገር ግን የሕመም ምልክቶች ከታዩ በኋላ ብዙ ወራት ከወሰደ፣ የሚያስከትለው የነርቭ ጉዳቱ ዘላቂና የማይቀለበስ ሊሆን ይችላል**

### ሕክምና

ሰዎች የደም ማነስ በተለይም ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የደም ማነስ ከታየባቸው ሐኪሞች በተቻለ ፍጥነት ሕክምናውን ይጀምራሉ ፣ በመሆኑም ሰዎች ከላይ የገለጽናቸው ምልክቶችን እንዳዩ በቶሎ ወደ ጤና ተቋም መምጣት ቢችሉ ውጤታማ ይሆናሉ ነገር ግን የሕመም ምልክቶች ከታዩ በኋላ ብዙ ወራት ከወሰደ፣ የሚያስከትለው የነርቭ ጉዳቱ ዘላቂና የማይቀለበስ ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩልም ከተለመደው ወይም ቀላል ከሆነው የደም ማነስ ችግር ከፍ ብሎ አደገኛ የሚባለው ደረጃ ላይ ከደረሰ ብዙውን ጊዜ በየወሩ የቫይታሚን ቢ 12 መርፌን መጠቀም ሊጠይቅ ይችላል። በዚህ መንገድ፣ በሽተኛው በቂ የደም ደረጃዎች ላይ በመድረስ፣ ቀይ የደም ሴሎችን ማምረት እንዲነቃቃ እና ሰውዬው መደበኛ ደረጃዎች እንዲኖሩት በማድረግ የሰውነት ትክክለኛ ኦክስጅኔሽን እንዲኖር ያስችላል። ለከባድ የደም ማነስ በወር ከአንድ በላይ መርፌ ሊያስፈልግ ይችላል፣ ግን ይህ በጣም የተለመደ አይደለም።

በእርግዝና ወቅት አይረን እና ፎሊክ አሲድ የያዙ እንክብሎች በመደበኛነት እንዲሰጡ ይደረጋል። በእርግዝና ወቅት ተገቢውን ክትትል ማድረግ እና መድሃኒቶችን ሰዓት ጠብቆ መውሰድ የእናትንም የልጅንም ጤና ይጠብቃል።

የደም ማነስ በሌሎችም ተጓዳኝ ህመሞች ምክንያት የሚከሰት መሆኑም ሊታወቅ ይገባል፤ ለምሳሌ የኩላሊት ህመም የተለያዩ የካንሰር ህመሞች የደም ማነስ ችግርን ሊያመጡብን ስለሚችሉ ሃኪም ጋ በመሄድ ተገቢውን ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

የደም ማነስ በድንገት በደረሰ አደጋ ወይም በልጅ መውለድ ወቅት በሚፈስ ከፍተኛ የደም መጠን ከተከሰተ ለሕይወት አስጊ ሊሆን ስለሚችል በዚህ ወቅት ደምን የመተካት ሕክምና ይደረጋል። ብዙዎች በተለይ እናቶች የደም መተካት ሕክምና ባለማግኘት ለሞት ይዳረጋሉ።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "ባለመስማማት መስማማት"

**የጽንሰ ሃሳብ መነሻ፤**

ዋናው ርዕሳችን የተወሰደው "agree to disagree" ከሚለው የባዕድ ሀረግ ተተርጉሞ ነው። በተቃርኖ ሃሳብ የተዋቀረ የሚመስለው ይህ ሀረግ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው እ.ኤ.አ ጁን 29 ቀን 1750 ዓ.ም ጆርጅ ዋይትፊልድ በተባሉ በእንግሊዛዊ የቤተክርስቲያን አገልጋይ አማካይነት ነበር። እኚህ ካህን ይህንን ሀረግ የተጠቀሙት ጆን ዌሲሊ ከተባሉትና አብረው ከሚያገለግሉት የቅርብ ጓደኞቻቸውና ወዳጃቸው ጋር በተፈጠረ የእምነት ቀኖና ዶግማ ልዩነት ምክንያት በመካከላቸው ጠላትነት ተፈጥሮ እርስ በእርስ እንዳይጎዳዱ በጻፉላቸው የማሳሰቢያ ማስታወሻ ውስጥ ነበር።

ደብዳቤው የደረሳቸው ካህኑ ዌስሊ ያንን የቀድሞ ወዳጃቸውን ጦማር በክብር ካስቀመጡ ከሃያ ዓመታት በኋላ እ.ኤ.አ በ1770 ዓ.ም ከሰንዱቃቸው ውስጥ አውጥተው ለሕዝብ ይፋ ያደረጉት ወዳጃቸው ጆርጅ ዋይትፊልድ አርፈው በቀብር ሽኝታቸው መርሃ ግብር ላይ ባደረጉት ንግግር ነበር። የንግግራቸው ይዘት የሚከተለውን ይመስላል፤

"ወዳጆች ሆይ!..." አሉ ጆን ዌስሊ ለሀዘንተኞቹ ቀብርተኞች ንግግራቸውን ሲጀምሩ፤ "...በእኔና በወዳጄ ጆርጅ ዋይትፊልድ መካከል የተፈጠረው የዶግማ አስተምህሮ ልዩነት በፍጹም ስሜታችንን አሻክሮ ጓደኝነታችን ላይ ጥላ አላጠላም። በልዩነታችን ተከባብረን አብረን ለመኖር የቻልነው ልበ ብርሃኑ ወዳጄ "ባለመስማማት መስማማት' - ‹agree to disagree› የሚለውን መርህ በልበ ሰፊነት አክብረንና ተከባብረን ልዩነታችን እንደተጠበቀ በራሳችን መረዳት ልክ በነፃነት እንድናገለግል የቃል ኪዳን ያህል ስለተስማማን ነው።

ስለዚህም በአስተሳሰብና በአስተምህሮ ብንለያይም በወዳጅነታችንና በጓደኝነታችን መካከል ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ውስጥ በፍጹም ነፋስ ሊገባ አልቻለም። ወዳጄ አርፈዋል፤ እኔም ተራዬን እየጠበቅሁ ነው። የሁለታችንም በድን ከአፈር ጋር መቀላቀሉ ግድ ነው። ሁለታችንም ከአገልግሎታችን ፍሬ የተነሳ ህያው ሆነን ስንጠቀስ እንኖራለን ብለን ብናስብ አንኳን፤ ስማችንን ‹እነ እከሌ› እያሉ የሚያስታውሱን ወዳጆቻችንና በዘመናችን የታተሙት የጽሑፍ ውጤቶች ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ።"

"ስለዚህም ወዳጄ ዋይትፊልድ ሆይ! ‹ባለመስማማት መስማማት› በማለት የገለጹት የአስተምህሯችንን ልዩነት ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ ከሚቀረው ከየራሳችን ማንነትም ጋር ሳይቀር የልዩነት ሃሳብ እንደምናስተናግድ ጭምር እንድናስታውስ ረድቶናል። ሰው ነና! ከልዩነታችን ይልቅ በመንግሥተ ሰማያት ለዘለዓለም አብረን እንደምንኖር በሚገባ ስለተረዳን ‹ባለመስማማት ተስማምተን› በፍቅርና በመከባበር ኖረን ዛሬ እርስዎን እንሸኛለን፤ ነግ ተነገወዲያ ደግሞ እኔ እከተልዎትና በልዩነታችን ከማንከራከርበት የአምላካችን ዙፋን ሥር ነፍሶቻችን እየሰገዱ በየፊናችን በዘመናችን ያገለገልነውን ልዑል አምላክ በማመስገን ለዘለዓለም አብረን እንኖራለን። ወዳጄ ሆይ ነፍስዎት በሰላም ትረፍ! አክባሪዎ።"

"ባለመግባባት መግባባት" የሚለው የዚህ ዘመን ዘለል ሀረግ ዕድሜ ወደ ሦስት መቶ ክፍለ ዘመን እየተጠጋ ቢሆንም አገልግሎቱ ገንኖ በዓለም ዙሪያ በሁሉም አንደበትና ጽሑፍ ውስጥ የዕለት ተዕለት መግባቢያና የልዩነት ማቻቻዬ መርህ ተደርጎ ሲተገበር አይስተዋልም። ቢሆን ኖሮማ ዓለማችን በሰላም አሸብርቃ በተረጋጋች ነበር። ጉዳዩን ወደ ራሳችን በመመለስ የአገራችንን ገመና ብንፈትሽበት ይበልጥ ትርጉም ስለሚሰጠን "ሙታንን ከማመስገን፤ ሕያዋንን ማስተንተን" እንዲሉ ትኩረታችንን ሰብስበን "ኢትዮጵያ ሆይ!..." እያልን እንቃትታለን።

**"አታምጣው አታምጣው ስለው ከቤቴ በላይ ቀልሉት ሄደ"፤**

ሰውየው ማንምና ምንም ሊሆኑ ይችላሉ። የፈለጉትን አመለካከትና ፍልስፍናም ማራመድ መብታቸው ነው። በአገራችን ባገለገሉበት ዘመንም ቢሆን ባበረከቱትም ሆነ ባጎደሉት ውጤቶች የሚያውቋቸው ወገኖች ስለ ሰውዬው የፖለቲካ አቋምና በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ስላላቸው አቋም የወደዱትንና የመሰላቸውን አስተያየት ሊሰጡ እንደሚችሉ አይጠፋኝም። የሚያመሰግኗቸው የመኖራቸውን ያህል የሚኮንኗቸው እንዳሉም ይገባኛል። ይህ ጸሐፊ በማንም አመለካከት ላይ ጫና ለማድረግ አይሞክርም። ምክንያቱስ? ከተባለ መርሁ የጆርጅ ዋይትፊልድ "ባለመስማማት መስማማት" የሚለው ፍልስፍና ስለሆነ ነው።

እናፍታታው፡- ሰውዬው በኢትዮጵያ የቀድሞው የአሜሪካ አምባሳደር ሚ/ር ቲቦር ናጊ ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያገለገሉትም እ.ኤ.አ ከ1999 እስከ 2002 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ውስጥ ነው። እኚህ አንጋፋ ዲፕሎማት ከጥቂት ቀናት በፊት በቲዩተር ገጻቸው ላይ ያሰፈሩት ሰፋፊ እውነቶችን የያዘ የግል አስተያየታቸው የአገሬን ወቅታዊ ሁኔታ በሚገባ የገለጸ ስለሆነ እንደሚከተለው በተዛማጅ ትርጉም ወደ ቋንቋችን መልሼዋለሁ።

"ኢትዮጵያ ውስጥ ቀረ የሚባል አጨቃጫቂ ተጨማሪ ርእሰ ጉዳይ ይኖር ይሆን?..." በማለት ቲቦር ናጊ ከጠየቁ በኋላ በእኛው በራሳችን የአገሪቱ ልጆችና በዓለም ፊት መሳቂያና መሳለቂያ ያደረጉንን ትዝብታቸውን እንዲህ በማለት ይዘረዝራሉ። "... በዘረኝነት፣ በሃይማኖት፣ አሁን በቅርቡ ደግሞ የታሪካቸው አንድ አካል በሆነው በአድዋ የጦርነት የድል ታሪክ እንኳን መስማማት አልቻሉም። በአስደማሚ ታሪኮች የተዋበችው ኢትዮጵያ ራሷን ለመከፋፈል የተለያዩ አማራጭ መንገዶችን ተግታ የምትፈልግ መስላ ትታየኛለች። አንድነታቸው እንዲጠበቅ እግዚአብሔር ይርዳቸው።"

ኢትዮጵያን በሚገባ የሚያውቋት እኚህ ጉምቱ አሜሪካዊ ዲፕሎማት በትዝብታቸው ከጠቀሷቸው እውነቶች መካከል አንድም ስህተት የለበትም። ፖለቲካው ሲግተን የኖረው የዘረኝነት መርዝ ውሰጣዊ ሰላማችንን እያናጋ ሞት፣ መፈናቀል፣ የንብረት መውደምና እጅግ በርካታ ተያያዥ ችግሮች የታሪካችን አካል ሆነው ከተዋሃዱን ሰነባብቷል። ዘመኑን በተግባራዊ ማሳያ እናመላክት ካልን ይህ ክፉ የእንክርዳድ ዘር እውቅና ተሰጥቶት ከተዘራና እንድንመራበት ከተደረገ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከሦስት አሥርት ዓመት በላይ ተቆጥሯል።

በእነዚህ ዓመታት ውስጥ አንድ ልጅ ተወልዶ፣ አድጎ፣ ተምሮ፣ ትዳር በመያዝ ልጆች ወልዶ የሚስምበት ጊዜ ነው። ዕድሜያቸው በዚህ ዘመን ውስጥ የሚወድቀው ዜጎች ቁጥር ምን ያህል ሚሊዮን ሊሆን እንደሚችል ትክክለኛውን አሀዝ ለመጥቀስ ያስቸግር ይሆናል። ነገር ግን "ኢትዮጵያ የወጣቶች አገር ናት" የሚለውን ማሞካሻ እውነትነት የምንቀበል ከሆነ ከአገሪቱ ዜጎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ እንደሚታቀፉ የዘርፉ ምሁራን ግምት ያረጋግጥልናል።

ስለምንድን ነው ብሔራችንን በአግባቡ በማክበርና የሌሎችንም እንዲሁ በአክብሮት እየተቀባበልን በጋራ ከማደግ ይልቅ የዘረኝነት ደዌ ሰልጥኖብን ታማሚ ልንሆን የቻልነው? ስለምንስ ነው በአንድ ካቆራኘን የኢትዮጵያዊነት ክብር ይልቅ በራስ ጎጥ ውስጥ መወሸቅን እንደ ፀጋ ቆጥረን የምንገፋፋው? የጥያቄው መልስ ተወሳስቦብናል ወይንም ኅብረ ብሔራዊነታች ደምቆ እንዲኖር አልተፈቀደለትም። የትኛውም ዘር ከየትኛውም የበለጠ ወይንም ያነሰ ያለመሆኑ እየታወቀ ስለምን ለመቋሰል በየጓዳችን እንበረታታለን። የተመረጠም ይሁን የተወገዘ ብሔር በኢትዮጵያ ምድር ይኖራል ብሎ ለመገመት ከኅሊና የመጣላት ያህል የከበደ ነው።

ሁሉም ብሔር የራሱ ውብ መገለጫዎች አሉት። በራሱ ባህል፣ ቋንቋና ወግ ይኮራል፣ መኩራትም ክብሩ ነው። እኔነት የሚደምቀው ከሌሎች ጋር አብሮና ተከባብሮ በመኖር እንጂ የራስን አካባቢ ብቻ እንደ ኤደን ገነት አቆንጅቶ "ነፍሴ ሆይ! እረፊ፣ ደስም ይበልሽ" እያሉ የስንፍና ዜማ በማንጎራጎር አይደለም። የራስን መገኛና ማንነትን ተራራ ላይ ሰቅሎ የሌላውን ብሔር ህልውና ከተራራው እግር በታች አሳንሶ ሸለቆ ውስጥ መክተት የአስተሳሰብ ድኩምነት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ስያሜ የሚሰጠው አይሆንም።

እርግጥ ነው ከአገራዊ የታሪኮቻችን መሰዊያ ላይ ፍሙን ከመጫር ይልቅ፤ አመዱን እየዛቅን በእርስ በራሳችን የማስተዋል ዕይታ ላይ እንድንበትን "የፖለቲካው ግብዣ የቀረበልን" ገና ከጠዋቱ መሆኑ አይጠፋንም። ባህር ማዶኞቹ **"from the alter of history take the fire not the ash"** የሚለውንና ባለፉት ጽሑፎቼ ውስጥ ደጋግሜ ያነሳሁትን ሃሳብ ለማብራራት መሞከሬ እንደሆነ ልብ ይሏል።

የብሔራችንን መንፈስ አጀግነን "የፍልሚያ ሸማ የተጣጣልንባቸው" ያለፉት ዓመታት ምን ትርፍ አስገኙልን? በመቆራቆዝ ያጣነው ነፍስና የወደመው ንብረት የሀዘን ከል እንድንለብስ ምክንያት ከመሆን ውጭስ ምን ፈየደልን? አገራዊ ችግሮቻችንን "ባለመስማማት በመስማማት" እየተከባበርን ከመኖር ይልቅ በዱላና በጎመድ ካልተፋለምን እያልን ማቅራራቱ ምንና ማንን ጠቀመ? ቲቦር ናጊ ታዝበውን ገመናችንን አደባባይ ያሰጡት እኛን እንደቸገረን እሳቸውንም ቢቸግራቸው እንደሆነ የትዝብታቸው ይዘት ምስክር ነው።

ድንበሬን አትለፍ፣ ክልሌን አቋርጥ፣ በመንገዴ ላይ አትራመድ፣ የሚለው የጅሎች ፍልስፍና ውሎ አድሮ "አየሬን አትተንፍስ፣ የወንዜን ውሃ አትጠጣ፣ በማሳዬ ላይ የበቀለውን እህል እንዳትቀምስ ወዘተ." ወደሚል እብደት እንዳንገባ ከፍ ያለ ሥጋት አድሮብናል፤ ምልክቶቹም የሚጠቁሙት መርዘኛ አካሄድ ነው። ይህ በሽታ በአጭሩ ካልተቀጨና መፍትሔ ካልተፈለገለት በስተቀር በወንዝ ከሚመሰለው የትውልዶች ጅረት ውስጥ እንደ ፈረሰኛ ውሃ እየጋለበ ሲበክል እንደሚኖር ለመገመት አይከብድም።

የፖለቲካ ህመማችንን በተመለከተ ምክርም፣ ምክክርም፣ ጸሎት/ዱዓም፣ ጾምም ሆነ ወደ ፈጣሪ የምንጮኸው ጩኸት ለጊዜው ሰሚ ያገኘ አይመስልም። በተማጽኗችንም ሆነ በኪራላይሷችን ላይ ስለምን ጀንበሯ እንደከፋችብን አልገባንም፤ ከውስብስብነቱ መጠዝ የተነሳም መፍትሔው ዳምኖብናል። መፍትሔ የጠፋለት ይህ የዘመናችን አገራዊ ስራይ በምን መድኃኒት ተፈውሶ እንደምናይ በእጅጉ ጓጉተናል። ሙሾ አሙሺዋ የአገሬ አስለቃሽ፡-

**"ሀዘንሽ ቅጥ አጣ፤ ከቤትሽ አልወጣ፣**
**የገደለው ባልሽ፤ የሞተው ወንድምሽ"**

በማለት አልቅሳ እንዳላቀሰችው፤ ሟቹም ገዳዩም፣ ዒላማውም ተኳሹም፣ ቀብረተኛውም ተቀባሪውም ከዚህቺው አገር ይሏት ጉድ ማህጸን የተገኙ ልጆቿ ናቸው።

በሁሉም የሕይወታችን ውሎ አምሽቶ ውስጥ ጆርጅ ዋይትፊልድ ፈጠሩት የሚባለው፡- "ባለመስማማት መስማማት" መርህ ባህላችን ሆኖ ልንገዛለት ቀርቶ እንግዳ አድርገንም እንኳን አልፎ አልፎ በየመድረኮቻችን ላይ ስሙን ያለማንሳታችን የእንቀቅልሻችንን ግዝፈት፣ የልባችንን ድንዳኔና ጽናት በሚገባ ያመለክታል። ወደ ጋራ መተማመን ደረጃ ባንደርስ እንኳን ስለምን መቀባበልና መከባበር ተሳነን? የዚህን አዚማችንን ሥርወ መነሻ የሚያስረዳን ብናገኝ ለጊዜውም ቢሆን መንፈሳችን ይረጋ ነበር።

"በቡሐ ላይ ቆረቆር" እንዲሉ ዘረኝነቱና የፖለቲካ ነውጡ ያነሰን ይመስል ስለ ሰላምና ስለ ዘላለማዊነት በሚሰብኩ ቤተ እምነቶቻችን ውስጥ ሳይቀር ተጋቦሹ ተዛምቶ እንደ አገር ህመማችንን አባብሶታል። ክርስቶስን እንደሰቀሉት አይሁዶች ወይንም ነብዩ መሐመድን ከመካ ወደ መዲና እንዲሰደዱ ምክንያት እንደሆኑት "የክፉ ዘመን ክፉዎች" ዛሬም ስመ ፈጣሪ በሚጠራባቸው ቤተ እምነቶች ውስጥ "የአምልኮ መልክ አንጂ የግብር ፍሬ" በማያፈሩ ጉዶች ተጥለቅልቋል። "ውሃ ቢያንቅ በምን ይውጡ፤ ምላጭ ቢያብጥ በምን ይውጡ" እንዲሉ ለነፍስና ለመንፈስ ፈውስ እንደሚሰጡ የሚታመንባቸው ቤተ እምነቶች ራሳቸው እንደ ባሕር ወጀብ ሲነዋወጡ ማስተዋል ለወሬም ለፍርድም አይመችም።

በታሪኮቻችን ላይ የምንሰናዘረው የእንካ ሰላንትያ ፍልሚያዎች ከእኛም አልፈው ወደ ቀጣዩ የትውልድ ዘመን ሲሸጋገሩ ምን ውጤት እንደሚያስከትሉ ለመተንበይ "የአራት ዐይናማነት ፀጋ" ለመታደል ግድ አይልም። "ባለመግባባት ተቻችሎ መግባባት" እየተቻለና የሚያግባቡንን ታሪኮቻችንን እያደመቅን፣ በአብሮነታችን ከመዝለቅ ይልቅ የሚለያዩንን የጠገጉ ቁስሎች እየደነቋቆልን ሕመማችን እንዲያገረሽ መትጋት ለማንምና ለምንም የሚጠቅም አይደለም። አምባሳደር ቲቦር የታዘቡት አንዱ አገራዊ ችግራችን ይህንኑ ከታሪክ ጋር ፍልሚያ የገጠምንበትን አገራዊ እብደት በሚገባ የሚያሳይ ነው።

ለማጠቃለያነት የሚያግዘን አንድ ጥቅስ ከቅዱስ መጽሐፍ በመዋስ የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ እንደምድምበት፡- "ከተምች የቀረውን አንበጣ በላው፤ ከአንበጣ የቀረውን ደጎብያ በላው፤ ከደጎብያ የቀረውን ኩብኩባ በላው።" የእኛስ ሁኔታ ከዚህ እውነታ በምን ይለያል? መፍትሔው የመነሻ ሃሳባችን ነው፡- "ባለመስማማትም ቢሆን መስማማትና" አብሮና ከብሮ በጋራ ድምቀት መኖር። ይኼው ነው። ሰላም ለሕዝባችን፤ በጎ ፈቃድም ለዜጎች።

# ተናጋሪው ዶሴ

# በውል ተዋዋዮች አለመተማመን ሰበር የቋጨው ክርክር

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ቢሄድም ክርክሩ መቆጫ አላገኘም። ከጉዳዩ መወሳሰብና ባለጉዳዮች ግራ ቀኙን ጠበቃ አቁሞ መከራከር እና የነገሩ መካረር አሁንም ወደ ቀጣዩ የፍርድ ሂደት ሊያመራ ግድ ሆነ። ወደ ሰበር ችሎትም ደረሰ። ጉዳዩም መዝገብ ተከፍቶለታል። የሰነድ መለያ ቁጥር 32899 የተሰጠው ሲሆን ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም ሰበር ችሎት የመጨረሻውን ውሳኔ ሊያሳርፍ ነው።

አብዱልቃድር መሐመድ፣ መስፍን ዕቁበዮናስ፣ መድህን ኪሮስ፣ ዓሊ መሐመድ እና ሱልጣን አባተም የተሰኙት ዳኞች ከችሎት መንበሩ ላይ ተሰይመዋል። አመልካች ወይዘሮ አስካለማርያም ታደሰ እና ተጠሪው አቶ ተሾመ ካሣዬ በአካል ቀርበው ሰበር የሚለውን የሚበይነውን የመጨረሻ ውሳኔ ለመስማት ጓጉተዋል። በዛሬው የዶሴ አምዳችን የምንቃኘው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በ2001 ዓ.ም ቅፅ 7 ካሰፈራቸው የፍርድ ሂደቶችና ውሳኔ የተመለከተ ይሆናል።

**ጉዳዩ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በመጋቢት 5 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተከሳሽ በሱሉልታ ሙሎ ወረዳ የማህበር አባል ነኝ በማለት ድርሻዬ ነው ያሉትን ቦታ በብር 18,400 (አስራ ስምንት ሺህ አራት መቶ) ሸጠውልኝ የቦታውን ካርታ አስረክበውኛል። ቦታውን አጥሬ ለመስራት ስሞክር ግን ቦታው የተገኘው በሕገ ወጥ መንገድ ነው በማለት የመሬት አስተዳደር ቦታውን ወርሶብኛል። በመሆኑም ተከሳሽ ገንዘቤን እንዲመልስልኝ ይወስንልኝ የሚል ክስ ነው።

ተጠሪው ሌላ ቤት የገዛባቸው አቶ ኤልያስ ደምሴ የተባሉት ተከሳሽ ደግሞ በሰጡት መልስ ይህ ክስ መቅረብ የሚገባው በቤት ሥራ ማህበሩ እንጂ በእኔ ላይ አይደለም። ከሣሽ ካርታውን የተቀበሉት ከማህበሩ እጅ በመሆኑ ስለቦታው ሕጋዊነት መጠየቅ ያለባቸው ማህበሩ ነው። በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ከከሳሽ አልተቀበልኩም በማለት ተከራክረዋል። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠና ማስረጃም ከሰማ በኋላ ተከሳሽ ገንዘቡን መቀበላቸውንና በውላቸው ደግሞ ቦታውን ለከሣሽ ካላስረከብኩኝ ገንዘቡን እመልሳለሁ በማለት ግዴታ መግባታቸውን በማስረጃ ስለተረጋገጠ በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ለከሳሽ ይክፈሉ ሲል ወስኗል።


በመቀጠልም ፍርድ ቤቱ ተጠሪውን በተከሳሽ ስም የተመዘገበው ቤት የገዛሁት በመሆኑ እግዱ ይነሳልኝ በማለት አመልክተውም ነበር። አመልካችም ደግሞ በተከሳሽ ላይ ቀደም ብሎ የወሰዱት ገንዘቤን እንዲመልሱልኝ ያስወሰንኩኝ በመሆኑና ቤቱም ተሸጦ ገንዘቤን የማስመልስበት የተከሳሹ ሃብት በመሆኑ እግዱ መነሳት የለበትም በማለት ተቃውመዋል።

ፍርድ ቤቱም አቶ ተሾመ ካሣዬ ገዛሁት የሚሉትን ቤት የሽያጭ ውል ስልጣን ባለው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ በፍትሐብሔር ቁጥር 2878 መሠረት ውጤት የለውም። እግዱ በቀረበው አቤቱታ መልኩ ሊነሳ የሚችልበት ምክንያት የለም በማለት ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል።

**ይግባኝ ለችሎት**

በዚህ የእግዱ ይነሳልኝ ጥያቄ መሠረት ተጠሪው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ይግባኝ ባይ ቤቱን ከአቶ ኤልያስ ደምሴ መስከረም 19 ቀን 1998 ዓ.ም በተፈፀመ የሽያጭ ውል ገዝተው ስም ለማዛወር በሒደት ላይ መሆኑን ገልጾ ነው ውልና ማስረጃ የእግድ ትዕዛዙን የመዘገበው፤ ሽያጩ በክብር መዝገብ የተመዘገበው የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለመመዝገብ ስልጣን ባለው አካል በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት እግዱ አይነሳም ማለቱ በአግባቡ አይደለም በማለት እግዱ እንዲነሳ ሲል ውሣኔ ሰጠ።

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይግባኝ ቀርቦለት ይግባኙን መሠረት በማድረግ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ አፀና።



በዚህን ጊዜ አመልካች ለዚህ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ አቀረቡ። የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ አግባብ አይደለም በማለትም በመቃወም ነበር። ቅሬታውም አቶ ኤልያስ ደምሴ ገንዘቡን ከንብረታቸው እንዲከፍሉኝ ተወስኖልኛል። አቶ ተሾመ ካሣዬ ቤቱን ገዝቼዋለሁ ቢሉም የሽያጭ ውሉ ስልጣን ባለው አካል አልተመዘገበም። ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉን ለማስመዝገብ ጥያቄ መቼ እንዳቀረበ ሳያጣራ ተመዝግቧል በማለት እግዱን ማድረጉ አግባቡ አይደለም የሚል ነው። ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሣኔ ማጽናቱ ተገቢ አልነበረም። ሁለቱም ፍርድ ቤቶች በፍትሃብሄር ቁጥር 2878 የተደነገገውን ሳያገናዝቡ የሰጡዋቸው ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ ተሽረው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ሊፀናልኝ ይገባል የሚል መከራከሪያም አቀረቡ።

**ውሳኔው ይከበርልኝ**

ተጠሪው በበኩላቸው በሰጡት መልስ፤ የሽያጭ ውሉ በፍትሃብሔር ቁጥር 2878 መሠረት እስከተመዘገበ ድረስ ስም ያለመዛወር የሚያመጣው ለውጥ የለም። የሽያጭ ውሉ ከመዝገቡ ጋር አይያያዝም። ቀደም ብሎ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመለያ ቁጥር 16109 ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የሽያጭ ውሳኔ ከመዝገቡ ጋር መያያዝ በቂ ነው። በመለያ ቁጥር 21448 የተጠቀሰው የፍትሐብሄር ቁጥር 1123 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም። የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠው የሽያጭ ውሉ ከተያያዘ በኋላ ነው። በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀናልኝ ይገባል በማለት ተከራከሩ፤ ችሎቱም ሃሳባቸውን ማዳመጥ ቀጠለ።

**የህግ ድምዳሜ**

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቤቱ ላይ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ በተጠሪው አመልካችነት ሊነሳ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርመረ። መዝገቡ እንደተመረመረውም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘው የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥሩ ኮ/ቁ/ 09/3/መ/00/180/ 6904/00 በሆነው ቤት ላይ የእግድ ትዕዛዝ የሰጠው መጋቢት 29 ቀን 1998 ዓ.ም ነው። ይህ የእግድ ትዕዛዝ ደግሞ በኮልፌ ቀራንዮ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ተመዝግቧል። እግዱ በተመዘገበበት ጊዜም ቤቱ በአቶ ኤልያስ ደምሴ ስም የተመዘገበ መሆኑን የሽያጭ ውሉ ከማህደሩ ጋር የተያያዘ ቢሆንም የስም ማዞሩ ጉዳይ በሂደት ላይ ያለ መሆኑን የመሬት አስተዳደር ባለስልጣኑ ገልጿል።

ነገር ግን የመሬት አስተዳደር ባለስልጣኑ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል ያለው የሽያጭ ውል መቼ ከመዝገቡ ጋር እንደተያያዘ አልገለፀም። በማስረጃነት ቀርቦ ከፍርድ ቤቱ መዝገብ ጋር ተያይዞ የሚገኘው የሽያጭ ውል ጽሑፍም ስንመለከተው እላዩ ላይ ከብ የውሎችና የክብር መዝገብ ማስረጃ ማህተም ከማረፉ በስተቀር ይህ ማህተም መቼ የውል ጽሑፍ ላይ እንደተደረገ አይታወቅም። በሽያጭ ውሉ ጽሑፍ ላይም ይሁን ጀርባ ላይ ያረፈ አራት ማዕዘን ማህተም የለም።

የሽያጭ ውሉ የክብር መዝገብ ውስጥ የተያያዘው መቼ እንደሆነ ካልታወቀ ደግሞ የተያያዘው የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ነው ለማለት ያስቸግራል። በሌላ በኩል ደግሞ የሽያጭ ውሉ የተያያዘው የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ነው ከተባለም በፍትሐብሔር ቁጥር 2878 የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም ተብሎ ከተደነገገው ጋር በማዛመድ ስንመለከተው የሽያጭ ውሉ በማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ከመፃፉ በፊት የሽያጭ ውሉ መኖር ያለመኖሩ አስቀድሞ መረጋገጥ ይኖርበታል። ይህ በተጠሪውና በአቶ ኤልያስ ደምሴ መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ግን በፍትሐብሔር ቁጥር 1723 በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተሰራ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም። በመሆኑም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ጽሑፍ የማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ የተፃፈው ሳይረጋገጥ በመሆኑ ውሉ በአመልካች ላይ የሚያመጣው ለውጥ ወይም የሚያስገኘው ውጤት የለም።

በተጠሪው በመከራከርያነት የተጠቀሰው ቀደም ብሎ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመለያ ቁጥር 16109 የሰጠውን ውሣኔ ስንመለከተውም ፍርድ ቤቱ የውሉ ከማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ጋር መያያዝ በቂ ነው ያለው የሽያጭ ውሉ ግንቦት 9 ቀን 1987 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ መምሪያ አዋዋይነት የተደረገ መሆኑን በመመልከቱ ምክንያት በመሆኑ ጉዳዩ በዚሁ መዝገብ ከሚታየው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ ባለመሆኑ የተጠሪው ክርክር አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም ይላል።

የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የሽያጭ ውሉን ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ የቀረበለትን የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሃብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን ስለሌለው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ የመሬት አስተዳደሩ ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሽያጭ ውል የመመዝገብ ስልጣን አለው፤ የሽያጭ ውሉ በዚሁ ሁኔታ የተመዘገበ በመሆኑ እግዱ መነሳት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና መታረም የሚገባው ነው ሲል አስቀመጠ።

በመሆኑም አመልካች ቀደም ብለው ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የእግድ ትዕዛዝ ያሰጡት ከአቶ ኤልያስ ደምሴ የሚፈልጉትን ገንዘብ ለማስመለስ በመሆኑና በዚሁ መሠረትም ያስወሰኑ ስለሆነ ቤቱን በሐራጅ በመሸጥ ገንዘባቸውን የማስመለስ መብታቸው የተጠበቀ ነው። ይህ መብታቸው ቀሪ ሊሆን ይችላል የነበረው የቤቱ ባለቤትነት ከአቶ ኤልያስ ደምሴ ወደ ተጠሪ ዞሮ ቢገኝ ነው። ይሁን እንጂ ቤቱ በአቶ ኤልያስ ደምሴ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑና በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ የተያያዘው የሽያጭ ውልም ስልጣን ባለው አካል ያልተረጋገጠ በመሆኑ ቀደም ብሎ የተሰጠው እግድ ተነስቶ የባለቤትነቱ ስም ወደ ተጠሪው እንዲዛወር ማድረግ ተጠሪው ያለአግባብ እንዲጠቀሙ አመልካች ደግሞ በፍርድ ያገኙትን መብት የሚያሳጣ በመሆኑ እግዱ በተጠሪው አመልካችነት የሚነሳበት የሕግ ምክንያት የለም። በዚሁ ምክንያትም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊሻር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል በማለት የመጨረሻውን ውሳኔ አሳርፏል።

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመለያ ቁጥር 29717 ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመለያ ቁጥ 50420 መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል ሲል ይደመድመዋል።
2. በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘው በካርታ ቁጥር ኮ/ቁ/09/3/መ/00/180/6904/00 የተመዘገበው ቤት ላይ በመለያ ቁጥር 32777 የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው እግድ በተጠሪው አመልካችነት ሊነሳ የሚችልበት ምክንያት የለም። እግዱ ሊነሳ የሚችለው አመልካች ከአቶ ኤልያስ ደምሴ እንዲከፈላቸው የተወሰነላቸው ብር 18,400 ይከፈላቸው ወይም ደግሞ ቤቱን በሐራጅ ለመሸጥ እንዲቻል አመልካች እግዱ እንዲነሳ ሲጠይቁ ነው በማለት ተወስኗል። በዚሁ መሠረትም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመለያ ቁጥር 32777 ጥቅምት 22 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል ሲል መዝገቡ ተዘግቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የማድነቅና የማመስገን ባህል

**ቦጋለ አበበ**

ትዝብት አንድን ነገር መተቸትና አቃቂር እያወጡ ማብጠልጠል ብቻ አይደለም። የሚተቹ ነገሮች በራሱ ዝም ብሎ ለመተቸት ሳይሆን ነገ ተሻሽለው ወደ ጥሩ መስመር እንዲገቡ ታሳቢ ባደረገ መልኩ መሆን አለበት። ከዚህ አንፃር አንድን መልካም ነገር የማድነቅና የማበረታታት ባህላችን ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው። ብዙ ጊዜ ትችታችንም የተሻለ ነገር ለመፍጠር ወይም ዛሬ የተጣመመው ነገር ነገ እንዲቃና ሳይሆን ይበልጥ እንዲሰበር የሚያደርግ መሆኑን በብዙ አጋጣሚዎች ታዝበናል።

እኛ ለእኛ ብሎ የሚለፋልንን ማጀገን እና ሌላ ጀግና እንዲወለድ ማድረግ አለመደብንም። ሁሉንም መልካም ነገሮች ከሃይማኖት፣ፖለቲካ፣ብሔርና ሌሎች ነገሮች ጋር እያገናኘን መተቸትና ማድነቅን ባህላችን እስኪመስል እየተለማመድነው መጥተናል። አድናቆታችንም ይሁን ትችታችን በነዚህ ጉዳዮች ተፅእኖ ስር ወድቀዋል ወይም በነዚህ ጉዳዮች የተቃኙ ሆነዋል ብለን ደፍረን መናገር የምንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።

አንዳንድ ነገሮች ግን አሉ፣ ሳይደነቁ የማይታለፉ። መልካም ነገር ሁሌም ሊበረታታና ሊደነቅ ይገባልና የዛሬው ትዝብታችንም በአድናቆት የተሞላ ነው። ልናደንቀው የመረጥነው ጉዳይም አድናቆት ቢያንስበት እንጂ አይበዛበትም።

በዚሁ ሳምንት መጀመሪያ አንድ ትልቅ ጉዳይ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። ይህም ከሰባት ሺህ በላይ አረጋዊያንና የአዕምሮ ህሙማንን በውስጡ በመያዝ አገልግሎት እየሰጠ ለሚገኘው መቄዶኒያ አዲስ ላስገነባው ህንጻ በርና መስኮት ለማሟላት የተካሄደው የቀጥታ ገቢ ማሰባሰቢያ መርሀ ግብር የታሰበውን አሳክቶ ተጠናቋል። መቄዶኒያ ያስጀመረው ባለ 12 ወለል ሕንፃ ከሁለት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር በላይ የሚፈጅ ሲሆን፤ በርና መስኮት ለመግጠም 151 ሚሊየን ብር ያስፈልግ ነበር።

በኮሜዲያን እሸቱ መለሰ አስተባባሪነት የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሚዲያ ባለሙያዎች ታዋቂ ግለሰቦች በተሳተፉበት የዩቲዩብ የቀጥታ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀ ግብር ላይ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ድጋፍ አድርገዋል። በተደረገው የገቢ ማሰባሰብ መርሀ ግብርም ለ888 በሮች እና ለ739 መስኮቶች የሚውል ገንዘብ የተገኘ ሲሆን፤ የአንድ በር ዋጋ 106 ሺህ ብር የአንድ መስኮት ዋጋ ደግሞ 80 ሺህ ብር መሆኑ ተገልጿል። መቄዶንያ አረጋውያንና የአእምሮ ህሙማንን ለመመገብ ብቻ በቀን አንድ ሚሊየን ብር በላይ ወጪ ያለበት እንደመሆኑ በራሱ አቅም ይህን ለማሳካት አይችልምና ሌላ መፍትሄ የግድ ይላል። ግን እንዴት? የሚለው አሳሳቢ ነበር። ኢትዮጵያ በእንዲህ አይነት ጉዳዮች ላይ መፍትሄ ይዞ የሚመጣ ጀግና ሁሌም አታጣም። ይሆናል ብሎ ለመገመት በሚከብድ ሁኔታ ነገሮችን የሚያስተካክል ጀግና በዚህኛው ትውልድም አልጠፋም።

በኮሜድያን እሸቱ መለስ ዶንኪ ቲዩብ አስተባባሪነት ለመቄዶኒያ የበርና መስኮት ማሰሪያ እሁድ የካቲት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 9:00 ሰዓት የተጀመረው የ1 ሚሊዮን ዶላር የገቢ ማሰባሰብ መርሐግብር 48 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በማግስቱ ሰኞ ለሊቱን ዕቅዱን አሳክቷል።

ይህ የደጋግ ኢትዮጵያውያን የዘመናችን ትልቅ ገድል ነው። ከዚህ በላይ ጀግንነት የለም። ከዚያም አልፎ "ሰውነት አልሞተም" ብለን እንድንደመድም በቂ ምሳሌ ነው። በዚህ ጊዜ እኛ ኢትዮጵያውያን ብሎም በዓለም ላይ የሚታየው የሚሰማው ሁሉ ሰው ሰውነቱን በቃ አጣ? ዓለም ለመኖር አስፈሪ እየሆነች ይሆን? የሚያስብሉ ሰው የሰው ስጋት እየሆነ የመጣበት አስከፊ ነገሮች ተከስተዋል እየተከሰቱም ነው፣ ሰብዓዊነትም እየተሸረሸረ የመጣበት ጊዜ ነው።

ነገር ግን አሁንም በጨለማ ውስጥ ብርሃን የሆኑ እና ለመኖር እንድንጓጓ የሚያደርጉን ጥቂት የማይባሉ ለነብሳቸው ያደሩ ልበ ብሩሃን መልካም ሰዎች ዛሬም አሉ። በልበ ብሩሁ ቢኒያም አማካኝነት ለተቋቋመው መቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል የማስፋፊያ ህንፃ ግንባታው ተጠናቆ ነገር ግን ያላለቁ የበር እና የመስኮት እንዲሁም አንዳንድ የፊኒሺንግ ስራዎች ለማጠናቀቅ የሚውል ገንዘብ አሰባስቤ ሳልጨርስ ከዚች ወንበር ንቅንቅ አልልም ብሎ ራሱን ለመልካምነት አሳልፎ የሰጠውን በበጎ ስራዎቹ የምናውቀው ኮሜድያን እሸቱ መለሰን አለማድነቅ አይቻልም። እንደዚህ ያሉ መልካም ሰዎች ቢያንስ በተግባራቸው ማድነቅና ማበረታታት መለመድ አለበት። እነዚህን ሰዎች ብንችል ሽልመንና እውቅና ሰጥተን ልናበረታታቸው ይገባል።

ይህን የበጎነት ጥግ የሆነ ተግባር የትኛውም ሃይማኖት፣ የትኛውም የፖለቲካ አቋም፣ የትኛውም ብሔር አባል ነኝ የሚል ሰው ላለማድነቅ ምክንያት የለውም። ለእንደዚህ አይነት መልካምነት አድናቆት ከሌለን ነገ ሌሎች በጎ ሰዎችን መፍጠር አንችልም። ዛሬ የምናየውን ጀግና ማድነቅ ካልቻልን ነገ ሌላ ጀግና አይወለድልንም።

ዛሬ ላይ የምንኖረው ምስጋና የለሽ በሆነ ዓለም ውስጥ ቢሆንም ሁላችንም ብንሆን ባንናገረውም ሌሎች በመልካም ተግባራችን እንዲያመሰግኑን መፈለጋችን ተፈጥሯዊ ነው። ሌሎችን ከልብ በመነጨ ስሜት ስናመሰግናቸው እንዲበረታቱና መንፈሳቸው እንዲታደስ እናደርጋለን። ከልብ የመነጨ ምስጋና፣ ሰዎች አቅማቸው የሚፈቅደውን ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉ ያነሳሳቸዋልና ማመስገንና ማድነቅ ይልመድብን።

# ዓለም አቀፍ




## በጀርመኗ ሀምቡርግ በሐይማኖታዊ ስፍራ በተከፈተ ተኩስ በርካቶች ተገደሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በጀርመኗ ሀምቡርግ ከተማ በሐይማኖታዊ ስፍራ በተከፈተ ተኩስ በርካቶች ተገደሉ። ጥቃቱ በይሖዋ ምስክሮች የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ አንድ ግለሰብ በከፈተው ተኩስ የተነሳ መፈጠሩን ቢቢሲ ዘግቧል።

ፖሊስ ጥቃት አድራሹ ግለሰብ ብቻውን ተኩስ መክፈቱን እና በጥያቄ ከ6 እስከ 7 ሰዎች መደገላቸውን የአገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል።

ፖሊስ ግለሰቡ ጥቃቱን እንዲፈጽም ምን እንዳነሳሳው እስካሁን ግልጽ አይደለም ብሏል። ከሟቾች በተጨማሪ በርካቶች በጥቃቱ ቢቢሲ ዘግቧል።

ፖሊስ ጥቃቱ በተፈጸመበት ቦታ ጥቃቱን ያደረሰው ግለሰብ ሳይሆን አይቀርም ያለውን ግለሰብ አስክሬን ማግኘቱን አስታውቋል።

የድረሱልኝ ጥሪ ለጸጥታ አስከባሪ ኃይሎች በደረሰ በደዲቃዎች ልዩነት ፖሊስ በስፍራው ሲደርስ በጥይት ተመትተው ክፉኛ የቆሰሉ እንዲሁም ሕይወታቸው ያለፉ ሰዎች ማግኘቱን የፖሊስ ቃል አቀባይ ሆልገር ቬህሬን ተናግረዋል።

እስካሁን የምናውቀው በርካታ ሰዎች በቦታው መገደላቸውን፣ በርካቶች ተጎድተው ወደ ሆስፒታል መወሰዳቸውን ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ግለሰቡ ጥቃቱን ለማድረስ ምን እንዳነሳሰው "እስካሁን ሙሉ በሙሉ ግልጽ አይደለም ብለዋል።"

የግዛቷ ከፍተኛ ባለስልጣን የሆኑት ኤንዲ ግሮት የልዩ ፖሊስ ኃይል አባላትን ጨምሮ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጸጥታ ኃይል አባላት በስፍራው መስማራታቸውን በትዊተር ገጻቸው ገልጸዋል።

የጀርመን የአገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ፖሊስ ተጎጂዎችን ወደ አምቡላንስ ውስጥ ሲያስገባ አሳይተዋል።

ፖሊስ ጥቃት ከደረሰበት ስፋራ ደርሶ ኦፕሬሽኑን በሚያከናውንበት ወቅት የአካባቢው ነዋሪዎች ከቤታቸው እንዳይወጡ ተነግሯቸው ነበር።

ዋና መቀመጫውን ኒውዮርክ ያደረገው የይሖዋ ምስክሮች በ19ኛው ክፍለ ዘመን በአሜሪካ የተመሰረተ ሲሆን የክርስትን እምነት መሰረት ያደረገ እንቅስቃሴ ነው።

## ተመድ ቀይ ባሕር ላይ በአሮጌ መርከብ የተከማቸ ነዳጅን ሊያስወግድ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት /ተመድ/ ቀይ ባሕር ላይ በአሮጌ መርከብ የተከማቸ ነዳጅን ሊያስወግድ መሆኑን አሳውቋል።

የመን ባሕር ዳርቻ አካባቢ በአንዲት አሮጌ መርከብ ምክንያት በተፈጥሮ ላይ የተጋረጠን አደጋ ለመቀልበስ በሚል ግዙፍ ነዳጅ ጫኝ መርከብ መግዛቱን ቢቢሲ ዘግቧል።

አደጋውን ታስከትላለች የተባለችው መርከብ እየበሰበሰ ባለ መጫኛዋ ከአንድ ሚሊዮን በርሜላ በላይ ድፍድፍ ነዳጅ ጭና ቀይ ባሕር ላይ ለዓመታት ቆይታለች።

ይህች አሮጌ ነዳጅ ጫኝ ግዙፍ መርከብ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ልትሰባበር አሊያም ልትፈነዳ ትችላለች የሚል ስጋት የፈጠረች ሲሆን፣ ይህም በቅርቡ ከተከሰቱት የባሕር ላይ ነዳጅ መፍሰስ አደጋዎች ሁሉ የከፋ ሊሆን ይችላል ተብሏል።

ሐሙስ ዕለት የተባበሩት መንግሥታት ግዙፍ ነዳጅ ጫኝ መርከብ በመግዛት በቆመችው አሮጌ መርከብ ውስጥ ያለውን ድፍድፍ ነዳጅ ወደ አዲሱ እንደሚዘዋወር አስታውቋል።

"ይህንን ግዙፍ መርከብ የገዛነው ሊፈስ የተቃረውብ ነዳጅ በጥንቃቄ ቀድተን ሰብዓዊ እና አካባቢያዊ አደጋን ለመከላከል ነው" የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (ዩኤንዲፒ) ባለሥልጣን አኺም ስታይነር ተናግረው "ይህ ትልቅ እርምጃ ነው" ብለዋል።

የመንግሥታቱ ድርጅት አካል የሆነው ዩኤንዲፒ፤ መርከቧን በጣም ታዋቂ ከሆነ ዩሮናቭ ከተባለ ድርጅት እንደገዛም አስታውቋል።

ነዳጁ ቢፈስ በቀይ ባሕር ዳርቻ የመን ውስጥ ላሉ ዓሳ አጥማጆች አደጋ ነው። 200 ሺህ ሰዎች አደጋ ላይ ሊወድቁ ይችላሉ። በርካታ ሰዎች ሕይወትን ለሚያሰጋ አደጋ ሊጋለጡ ይችሉ ነበር። የተበከለ ውሃ ደግሞ ሚሊዮኖች ጋር ሊደርስ ይችላል ይላሉ።

አንድ ነገር ግልፅ ላድርግላችሁ። ይሄ አደጋ ያለበት ሥራ ነው። የሆነ ስህተት ልንሠራ እንችላለን" ሲሉ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ባልደረባ ተናግረዋል።



ዩኤንዲፒ አክሎ ነዳጁ ቢፈስ ለማፅዳት የሚወስደው ወጪ 20 ቢሊዮን ዶላር ሊጠጋ ይችላል ሲልም አመልክቷል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በመርከቧ ምክንያት በቀይ ባሕር ላይ የተደቀነውን አደጋ ለማስወገድ ለዓመታት መፍትሄ ሲያፈላልግ እና ለዚህም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ልገሳ ሲጠይቅ ቆይቷል።

መርከቧ የምታስከትለውን አደጋ ለማስቀረት ለሚከናወነው ሥራ በድርጅቱ ለተያዘው ዕቅድ ማስፈጸሚያ 129 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልጋል የተባለ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥም 75 ሚሊዮን ዶላር ሲገኝ 20 ሚሊዮን ዶላር ደግሞ ቃል ተግብቷል።

ኤፍኤስኦ ሴፈር የተባለችው ለዓመታት ባሕር ላይ የቆመችው አሮጌ መርከብ በየመን የእርስ በርስ ጦርነት ከተቀሰቀሰ በኋላ በሆዴያ ወደብ ተረስታ ትገኛለች።

መርከቧ ከፈረንጆቹ ከ2015 ዓመት ጀምሮ ጥገና ተደርጎላት አያውቅም።

በ1976 የተመረተችው መርከብ ለነዳጅ ማከማቻነት ስታገለግል ቆይታለች። በየመኑ የሁቲ አማፂያን የሚመራው ራስ ኢሳ የነዳጅ ማከመቻ አካባቢ ቆማ ትገኛለች።

376 ሜትር የምትርዝመው መርከብ በትንሹ 1 ነጥብ 14 ሚሊዮን በርሜል ድፍድፍ ነዳጅ እንደያዘች ይገመታል።

መርከቧ በ2015 በሳዑዲ አረቢያ የሚደገፈው የየመን አስተዳደር እና የሁቲ አማፂያን ጦርነት ከጀመሩ ወዲህ እንክብካቤ የሚያደርግላት አጥታ ውሃ ላይ እንዳለች እየዛገች መጥታለች።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ማሸነፍ ከፈለክ ትእግስተኛ ሁን

አስናቀ ፀጋዬ



በእልህ አስጨራሹ የማራቶን ሩጫ ሁሉም ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚሆን ነው የሚመስለው። ገና የማስጀመሪው ተኩስ ሲተኮስማ ሁሉም እየተጋፋ ሲሮጥ አሸናፊ ይመስላል። ነገር ግን ያ ሁሉ የማሸነፍ ወኔ እየቀነሰ መጥቶ በመሃል መንጋው መበተን ይጀምራል። መራራቅ ይጀምራል። በመጨረሻ ውድድሩ ሲጠናቀቅ ግን አንደኛ የሚሆነው ሰው ይታወቃልና ሪቫን በጥሶ አሸናፊ ይሆናል። ከአሸናፊው ቀጥሎ ሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚቀመጠው ሰው ሲጠበቅ! ሲጠበቅ! በደቂቃዎች ዘግይቶ ይመጣል። ለሶስተኛና አራተኛ ደረጃ የሚጠበቁትማ የት ጠፉ? እየተባሉ ቆይተው አንደኛና ሁለተኛ ደረጃን ይዘው ካጠናቀቁት የበለጠ ዘግይተው ይመጣሉ።

እዚህ ጋር ስለማራቶን ሩጫ ለማውራት አይደለም የፈለኩት ስለ ሕይወት ሩጫ እንጂ። ልክ እንደማራቶን ሩጫ ሁሉ የሕይወት ሩጫም በቅድሚያ ፍጥነት፣ በመሃል መቀዝቀዝ በስተመጨረሻ ደግሞ ከናካቴው ከሩጫው ውጭ መሆን አለ። ሰዎች በሕይወት ኡደት ውስጥ ሁሉንም ነገር ይጀምራሉ። ትምህርት፣ ስራ፣ የፍቅር ግንኙነት፣ ሌላም ሌላም ነገር ይጀምራሉ። በአብዛኛው ግን የሚጀምሯቸው ነገሮች ፍፃሜ የላቸውም።

ትዳር ጥሩ ነው። የትዳር ጥሩነትን ሰዎች ተገንዝበው ውሃ አጣጫቸውን ፈልገው በሥርግ ያገባሉ። ለጊዜውም ፍቅራቸው ደርቶ በፍቅር ክንፍ ይላሉ። ቀናት፣ ወራትና አመታት ያልፋሉ። ጋብቻ የወለደው ፍቅራቸው ግን ዘላቂነት ሳይኖረው በአጭር ተደምድሞ ፍቺ ይፈፅማሉ።

መቼም በዚህ ምድር ገንዘብ ማግኘትና ኑሮውን ማሻሻል ብሎም ሕይወቱን መለወጥ የማይፈልግ ሰው የለም። ለዛም ነው ብዙ ሰዎች አዳዲስ ቢዝነሶችን የሚጀምሩት። ነገር ግን ስንት ተለፍቶበት የተሰራው ቢዝነስ በአመቱ ብትንትኑ ሲወጣ ይታያል። ያ ሁሉ ህልም በአጭር ይቀጫል።

ይህም የብዙዎቻችን ሕይወት ችኮላ የተሞላበት እንደሆነና ትእግስት እንደሌለው ያሳያል። የአብዛኛዎቻችን ክፍተትም ነው። ትእግስት በአለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ሚስጥር ነው። ለዛም ነው የታገሰ አፈሰ የሚባለው። ለዛም ነው ትእግስት ዘሯ መራራ ቢሆንም ፍሬዋ ጣፋጭ ነው የሚባለው። የሰዎች ትእግስት ግን የመቶ ሜትር ሩጫ ያህል በጣም አጭር ናት።

እያንዳንዱ ሰው አቅምና አውቀት ቢኖረውም ፤ በሰዎች ቢከበብም ትእግስት ከሌለው የዘራውን ሊያጭድ አይችልም። የለፋበትን አያሳካም። በክረምት የዘራኸውን በመኸር የምታጭደው ታጋሽ ከሆንክ ብቻ ነው። በሕይወትህ ውስጥ ደስተኛ የምትሆነው የትእግስትን ጥበብ ከተላበስክ ብቻ ነው። ብዙ ሰዎች ይጣደፋሉ። ይቻኮላሉ። ነገሮች ለምን በቶሎ አይሳኩልኝም ይላሉ። የሕይወት ትእግስት በጥቂቱም ቢሆን የገባቸው ግን መታገስ ይጀምራሉ። ትእግስታቸውም ፍሬ አፍርቶ በሕይወታቸው ስኬታማ መሆን ይችላሉ። ለመሆኑ መታገስ ማለት ምን ማለት ነው?

መታገስ ማለት ለጊዜያዊ ደስታ ብለህ ነገህን የሚጎዳ ውሳኔ አለመወሰን ነው። ስትታገስ ሀያሉ ጊዜ ካንተ ጋር ነው። ሁሉን አሳልፎ ጥሩውን ቀን ያመጣልሃል። ስትታገስ የፈጀውን ጊዜ ይፈጃል እንጂ ከናቁህና ዝቅ አድርገው ካዩህ ሰዎች በላይ ከፍ ትላለህ። ስትታገስ ግዙፍ መስሎ የታየህ ችግር ምን ያህል ቁጫጭ እንደነበር ይታይሃል። የፈጣሪ ታናሽ ወንድም የሚባለውን ኃያሉን ጊዜ ከጎንህ ማሰለፍ ከፈለክ ታገስ ወዳጄ!

አሜሪካ ኮሎራዶ ግዛት ውስጥ የተፈጠረ ታሪክ ነው። ሰውዬው ወርቅ ለማውጣት ብር ተበድሮ፣ ማሽንና መሬት ገዝቶ ቁፋሮውን ጀመረ። ነገር ግን ቢቆፈር ቢቆፈር ወርቁ ሊገኝ አልቻለም። ብዙ ሞከረ አልተሳካለትም። ተስፋ ቆረጠ። እናም «እዳዬም እየበዛ ነው። ስለዚህ ለምን ሽጬ አልወጣም» ብሎ ማሽኑንና መሬቱን ሸጦ ወጣ። በቦታው ላይ ሌላ ወርቅ ቆፋሪ መጣ። እርሱ ግን ከመቆፈሩ በፊት የማእድን ባለሙያ ቀጥሮ ወርቁን ማስፈለግ ጀመረ። አስገራሚ ነገር ተፈጠረ። የማእድን ባለሙያው አንድ ነገር አወቀ። ለካ ወርቁ ያለው የመጀመሪያው ሰውዬ ካቆመበት አንድ ርምጃ ርቀት ላይ ነበር። ያ የመጀመሪያው ወርቅ ቆፋሪ ምን ያህል ሊቆጨውና ሊፀፅተው እንደሚችል አስቡት።

እኛም ካልታገስን የለፋንበትን ማጨድ አንችልም። ስለዚህ እየለፋንና እየጣርን ከሆነ አንድን ነገር ከማቆማችን በፊት አንድ እርምጃስ ቢሆንስ የቀረኝ፣ አንድ ሳምንትስ ቢሆን የቀረኝ፣ አንድ ወርስ ቢሆን የቀረኝ፣ አንድ ዓመትስ ቢሆን የቀረኝ፣ የምፈልገው ነገር ሊመጣልኝና ሊሳካልኝ ትንሽ ጊዜ ቢሆንስ የቀረኝ ብለን ትግላችንን ማቆም የለብንም። መታገስ አለብን።

ልፋቱን ለፍተህ፤ ላብህን ጠብ አድርገህ እንዴት ልትበላ ስትል አይንህ ሌላ ያያል። ያቆሙ አሸንፈው አያውቁም። ተስፋ የቆረጡ ተረስተዋል። መንገድህ በጉም ተሸፍኖ ይሆናል። ልመለስ አትበል። እስከሚታይህ ድረስ ሂድ። ቢዝነሱ ውጤት የለውም አትበል። ስንት አመት ሰርተህ ነው፤ ምን ያህል ሞክረህ ነው እንዲህ የምትለው? «የምወደው ስራ ቢሆንም ምንም ለውጥ አልሰጠኝም ላቆመው ነው» አትበል። ፅዋው እስኪሞላ ታገስ። ዞር ብትልም ሌላኛው ስራ የሕይወት ምእራፍ ያንተን ትእግስት ይፈልጋል። የተኛውም ነገር ያንተን ትእግስት ይፈልጋል።

አንዳንዴ ከእኛ ያነሰ አቅም፣ እውቀትና ገንዘብ ያላቸውና ኧረ በጭራሽ እኛ ላይ አይደርሱም የምንላቸው ሰዎች፤ ለአብነት እንኳ በትምህርት ቤት እያለን ከኋላ የሚቀመጠው ያ ረባሽ ልጅ ዛሬ ትልቅ ቦታ ደርሷል። እንዴት እኔን በለጠኝ የምንላቸው ሰዎች አግብተዋል። ትዳር መስርተው ልጆች ወልደዋል። ከእኛ የተሻለ ሕይወት እየመሩ ነው። እኛ እኮ ከእነርሱ የተሻልን ነበርን። ታዲያ ለምን ይመስላችኋል እነርሱ እኛን የበለጡን። አቅም አጥተን አይደለም። ሰነፍም ሆነን አይደለም። ስላልታገስን ነው። ጥረታችንን ስላቆምን ነው።

መታገስ ዋጋ ያስከፍላል። ፍሬው ግን ጣፋጭ ነው። በሕይወታችን ካልታገስን የሆነ ነገር እያጣን ነው። አንድ ጫካ በዛፍ ለመሞላት ብዙ አመታትን ይጠይቃል። ጫካውን ለማውደም ግን አንዲት ክብሪት በቂ ናት። የለፋህበትን ለማፍረስ አንድ የችኮላ ውሳኔ በቂ ነው። ትእግስት ግን ሁሌም ዋጋ ያስከፍላል።

ጥሩ ነገር አይደል የምትፈልገው፤ ታዲያ ምን ትጠብቃለህ አሪፍ ዋጋ ክፈላ። እመነኝ አይቆጭህም፤ ለምን ታገስኩ ብሎ የቆጨው ሰው የለም። ልፋቱን አታቁም፤ ስፖርቱን ስራ፤ መፅሃፉን አንብብ፤ በጠዋት ተነስ፤ ገንዘቡን አስቀምጥ፤ ልፋትህንም አታቁም። ታገስ ሕይወትህን ትቀይራለህ። በአንዴ ተለውጬ በዙሪያዬ ያሉትን ሰዎች መቼ ባስገረምኳቸው አትበል። ለውጥ ሂደት ይጠይቃል። ጊዜ ይጠይቃል። መታገስ ይጠይቃል።

አንድ ድንጋይ ወርውረህ የሾላ ፍሬ አታረግፍም። ደጋግመህ በደንብ መወርወር አለብህ። መልፋት አለብህ። ታገስ፤ ካልታገስክ ለውጡን አታየውም። አትጓጓ፤ ከጓጓህ ከመንገድ ትቀራለህ። ህልምህ የስኬትህ መንገድ ነው። መንገዱን የምትሄድበት መኪና ግን ፅናት ነው። ያለ ፅናት የትም አትደርስም። ለአላማህ ስትል መፅናትና መታገስ አለብህ። የምፈልገው አልሆነም አትበል። ሞክሬ እኮ አልተሳካም አትበይ። እስኪሆን ድረስ መታገስ አቃተኝ በል። ጥግ ድረስ መሄድ መሞከር ከበደኝ በይ።

እንዲህ ስንል መፍትሄው ግልፅ ነው። መፍትሄው ወይ መታገስ ነው አልያም አካሄድ ቀይሮ በአዲስ መንፈስ መሞከር ነው። ማቆም የሚባል ነገር የለም። ለችግርህ ጊዜ የራቁህ በስኬትህ ጊዜ ዙሪያህን ቢከቡህ እንዳትገረም። የዛሬም ሺ ዓመት ሰዎች እንደዚህ ነበሩ። አየህ ታጋሽ ስትሆን እውነተኛ ለውጥ ታያለህ። ሰዎች ያደንቁሃል። ያከብሩሃል። ካልታገስ ግን ከሰዎች ትለምናለህ። ከሰዎች ትጠብቃለህ። ከሰዎች እንደመጠበቅ ልብ ሰባሪ ነገር ደግሞ የለም። ራስህን አትጠራጠረው። ራስህን የምታምን ከሆነ ታገስ። ራስን እንደመጠራጠር ህልም ገዳይ ነገር የለም። ትእግስት ይኑርህ። «ሁሉም ነገሮች ቀላል እስኪሆኑ ድረስ ከባድ ነበሩ» ይላል ፐርሺያዊ ገጣሚ ሰአዲ።

የጎደለህ ትንሽዬ ትእግስት ነው እንጂ የምትፈልገው ነገር ካንተ አያመልጥም። ታገስ ማለት ግን ቁጭ ብለህ ተመልከት ማለት አይደለም። ጥረትህን ሳታቆም ጠብቅ ማለት ነው። አንዳንዴ ምንም ነገር ሳይጎድለን ትእግስት ማጣት ብቻ ባለንበት ያስቀረናል። ይህች ዓለም ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ለረጅም ጊዜ የቆየ የሚያሸፍባት መድረክ ናት። ለምሳሌ መዝናናት፣ ፊታ ማለት እያማረህ «ቆይ እስኪ ዛሬ ይለፈኝ» ማለት ከጀመርክና ያን ጊዜ ለሚጠቅምህ ነገር ከተጠቀምከው አትጠራጠር ትክክለኛው መንገድህ ላይ ነህ። ያ ተከታታይ ድራማ ዛሬ ይለፈኝና ስራ ልስራ ማለት ከጀመርሽ ለውጡን በቅርቡ ታይዋለሽ። ትእግስት ማለት ገንዘብ አውጥቶ ፊታ ማለት ያምርህና ግን ለምን አንደኛዬን ጥሩ አቅም ሲኖረኝ አልዝናናም ብሎ ወጥሮ መስራት ነው።

አንተ እኮ ብዙ ፈተና ያለፍክ ሰው ነህ። አበቃልህ ሲባል ለዛሬ ደርሰሃል እኮ። ጠንካራ ነህ። አሁን ያለህበት ላይ ለመቆም አንተን መሆን ይጠይቃል። ያንተን ጥንካሬ ይጠይቃል። እውነት ነው ወደኋላ የሚጎትት መጥፎ ትዝታ ይኖርሃል። እርሱን እያሰብክ በመቆጨት የሚባክነውን ጊዜ አስብ። ያንተን ጊዜና ትኩረት የሚፈልጉ ብዙ ጉዳዮች አሉ። እንዴ ህልምህስ! ስራህስ! የነገ የፍቅር፣ የትዳርና የቤተሰብ ሕይወትህስ! ከእነርሱ የሚተርፍ ጊዜ ኖሮህ ነው ቀንህ በጭንቀት የሚያልፈው። እርግጠኛ ነኝ ብዙ ነገር መቀየር ማሳደግ የተሻለ ሕይወት መኖር ትፈልጋለህ። ያንን ማድረግ የምትችለው ጥረትህን ካላቆምክ ብቻ ነው። ከታገስክ ብቻ ነው።

እለፋለሁ መቼ ነው የሚሳካልኝ ብለህ አትፀፀት፤ አትዘን። ታገስ! ሕይወት ለሚታገሱ ብቻ ናት። ርስቱን የሚወርሱት፣ የሚስቁት ፣ የአድማስ ጥግ የሚጓዙት የታገሱ ብቻ ናቸው። ፍሬዋን የሚበሉት ታግሰው የጠበቁ ብቻ ናቸው።

ሰውዬው ኮፍያ አድርጓል። ጃኬት ደርቧል። ቀብረር ! ቀብረር! እያለ እየተጓዘ ነው። ከላይ ፀሐይና ንፋስ ያዩታል። ንፋስ በግልፍተኝነትና በጉራ ወደ ፀሐይ ዞሮ እንዲህ አላት፤ «ይኸውልሽ ፀሐይ እኔ አቅሜን ለማሳየት የዚህን ሰውዬ ኮፍያውንም ጃኬቱንም በአንድ ጊዜ ነው የማስወልቀው» አላት። ፀሐይም «እስኪ እንያ» አለች። ንፋስ በሃይለኛው መንፈስ ጀመረ። ሃይሉን ተጠቅሞ የሰውዬውን ኮፍያ ለማውለቅ የሚችለውን ሁሉ አደረገ። ሰውዬው ግን ንፋሱ ሲነፍስ ጃኬቱን ሰብሰብ አደረገ። ኮፍያውንም ጫን አድርጎ ያዘው። ንፋስም ተበሳጨ። ይበልጥ በኃይል ነፈሰ። ሰውዬው ግን ይበልጥ ኮፍያውን አጥብቆ ያዘ። ጃኬቱንም አጠበቀ።

ፀሐይ ፈገግ እያለች ወደንፋስ ዞራ እንዲህ አለች። «የታለ ኮፍያውን ያወለከው፣ የታለ ጃኬቱን ያስጣልከው እስኪ ደግሞ እኔ ላሳይህ» አለችው። ፀሐይ ቀስ ብላ መውጣት ጀመረች። መፍካት ጀመረች። ወከክ ማለት ጀመረች። ሰውዬው ንፋሱ ስለጠፋ እጁን ለቀቅ አድርጎ ኮቱን አስተካከለ። ከኮፍያው ላይ እጁን አወረደ። ፀሐይ ቀስ እያለች መሞቅ ጀመረች። መጋል ጀመረች። ሰውዬው ሞቀው። ጃኬቱን ቀስ አድርጎ አወለቀ። በድጋሚ ኮፍያውን አውልቆ በእጁ ያዘ። ፀሐይ ወደ ንፋስ ዞራ እንዲህ አለችው። «አንዳንዴ ነገሮች በጉልበት አይደሉም። በፍጥነት አይደሉም» አለችው።

በሕይወትህ ውስጥ ስለሮጥክ አትቀድምም። ስለሰራህ ብቻ አትቀየርም። አንዳንዴ ረጋ ብለህ ማሰብ አለብህ። ወዴት እየሄድኩ ነው ማለት አለብህ። መሮጥ መፍጠን ብቻ ሕይወት አይቀይርም። መታገስ አለብህ። ሰላም!!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# በውጭ ምንዛሬ ግኝት ቡናን እየተከተለ ያለው ዘርፍ

ፍሬሕይወት አወቀ



በ2015 በጀት ዓመት ባለፉት ሰባት ወራት ከሆርቲካልቸር ዘርፍ 414 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ተችሏል፤

ኢትዮጵያ ከሰብል ምርት በተጨማሪ በሆልቲካልቸር ዘርፍ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬዎችን በማምረት ለውጭ ገበያ ማቅረብ ከጀመረች ሁለት አስርት ዓመታትን ማስቆጠሯን መረጃዎች ያመለክታሉ። ዘርፉ ከእድሜ አንጻር በርካታ አመታትን ያስቆጠረ ባይሆንም፣ አበረታች ውጤት እየተመዘገበበት ይገኛል። አገሪቷ ለዘርፉ ምቹ የሆነ የአየር ንብረት፣ ውሃ፣ ለም አፈርና በቂ ሰው ኃይል ያላት መሆኑ ዘርፉን ስኬታማ እንዲሆን አስችለውታል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በሆርቲካልቸር ዘርፍ ከፍተኛ መነቃቃት እየታየ ይገኛል፤ ዘርፉ በሁለት አስርት አመታት ጉዞው እስከ 2014 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ አጠቃላይ ከአራት ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ ማስገኘት ችሏል።

በ2014 በጀት ዓመት ብቻ 589 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ከእቅድ በላይ 631 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ተገኝቶበታል። በተያዘው 2015 በጀት አመት ባለፉት ሰባት ወራት ብቻ 414 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ በማስገኘት ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት በግብርናው ዘርፍ ቀዳሚና አንጋፋ ከሆነው ከቡና ቀጥሎ የሁለተኛ ደረጃን መያዝ ችሏል።

አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬን በስፋት ማምረት የሚያስችል ዕምቅ አቅም ያላት መሆኑ የሚነገርላት ኢትዮጵያ፤ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አሁን ላይ ያላትን እምቅ አቅም በመጠቀም ከዘርፉ የውጭ ምንዛሬ በማግኘት ተጠቃሚ እየሆነች ትገኛለች። ዘርፉ በሥራ ዕድል ፈጠራና በቴክኖሎጂ ሽግግርም እንዲሁ የጎላ አስተዋጽኦ እያደረጉ ከሚገኙ ዘርፎች መካከል ተጠቃሽ እየሆነ መጥቷል።

በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስተዋጽኦ ጉልህ ሚና ያለው የሆርቲካልቸር ዘርፍ በተለይ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ስኬታማ እየሆነ እንደመጣም መረጃዎች ያመለክታሉ። የዘርፉን ስኬት መነሻ በማድረግም በዛሬው የስኬት አምዳችን የሆርቲካልቸር ማህበርን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና እያስመዘገበ ያለውን ስኬት እናዳስሳለን።

የኢትዮጵያ አበባ አምራቾችና ላኪዎች ማህበር ፕሬዝዳንት አቶ ነጋ መኳንንት እንደሚሉት፤ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ወደ ሥራ የገባው የሆርቲካልቸር ዘርፍ በቀዳሚነት አበባ አምርቶ ለውጭ ገበያ ያቀርብ ነበር። በሂደትም አትክልትና ፍራፍሬን ጭምር አምርቶ ለውጭ ገበያ ወደ ማቅረብ ተሸጋግሯል።

የሆርቲካልቸር ዘርፍ ካለፉት አስርት ዓመታት ወዲህ በተገቢው ሁኔታ እያደገ የመጣ ዘርፍ መሆኑን ፕሬዝዳንቱ ጠቅሰው፣ ባለፉት ጥቂት አመታት ከኮቪድ እና ከጸጥታ ጋር በተያያዘ ዘርፉ ተቀዛቅዞ እንደነበርም አስታውሰዋል። የኢትዮጵያ አበባ አምራቾችና ላኪዎች ማህበርም ዘርፉ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ያለውን ፋይዳ በመረዳት የዘርፉን ዕድገት ከፍ ለማድረግና ለማነቃቃት የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን ማከናወኑን በዚህም ውጤት ማስመዝገብ መቻሉን አስታውቀዋል።

ኢንዱስትሪው እያስመዘገበ ያለውን ውጤት ማስመዝገብ እንዲችልም ማነቆ የሆኑ በርካታ ችግሮች መፈታታቸውንም ተናግረዋል። በመንግሥት መፈታት ያለባቸውን ችግሮች ከመንግሥት ጋር በመነጋገር እንዲፈቱ መደረጉን አመልክተው፣ የማስፋፊያ መሬት የጠየቁ አልሚዎች የማስፋፊያ ቦታ እንዲያገኙ የተደረገበትን ሁኔታም ፕሬዝዳንቱ በአብነት ጠቅሰዋል።

ማህበሩ ምርታማነትን ለመጨመር የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠትና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ኢንዱስትሪው ከዓመት ዓመት እየተስፋፋ እንዲሄድና ውጤታማ እንዲሆን ሠርቷል ብለዋል። በአሁኑ ወቅትም ዘርፉ እየተነቃቃ መሆኑን ጠቅሰው፣ በ2012 እና 2013 በጀት ዓመታት ከተገኘው የአበባ ምርት ገበያ በበለጠ ካለፈው በጀት አመት ጀምሮ የተሻለ ገበያ መገኘቱንም ፕሬዝዳንቱ ገልጸዋል።

ዘርፉን ስኬታማ ለማድረግ የተከናወኑት ተግባሮች እንዳሉ ሆነው በርካታ አምራቾች የማስፋፊያ ቦታ ጥያቄ እያቀረቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ልማቱ መጠነኛ በሆነ ቦታ ላይ ብቻ እየተካሄደ መሆኑን ፕሬዝዳንቱ ጠቅሰዋል። በቀጣይ ጥያቄውን ሙሉ ለሙሉ ለመመለስ የማስፋፊያ ቦታ በማዘጋጀት ዘርፉ የበለጠ ውጤታማ መሆን እንዲችል ይሰራል ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሆርቲካልቸር ዘርፍ በዋናነት ኤክስፖርት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ግብዓቱ ከውጭ የሚመጣና ገዢውም ውጭ ያለ ነው። በአገር ውስጥ ያለው አምራቹ ብቻ ነው። ስለዚህ እነዚህን አካላት በማገናኘት የገበያ ትስስር መፍጠር ከማህበሩ የሚጠበቅ ሥራ በመሆኑ ማህበሩ ይህንኑ እየሠራ ይገኛል። በተለይም የውጭ ባለሃብቶችን ወደ አገር ውስጥ በመሳብ ረገድ ማህበሩ ሰፊ ሥራ እየሠራ ነው።

ኢትዮጵያ ከሌሎች አገራት በበለጠ በሆርቲካልቸር ዘርፍ ተመራጭ መሆን ችላለች ያሉት ፕሬዝዳንቱ፣ ለዚህም መንግሥት ለኢንቨስትመንቱ እያደረገ ያለው ማበረታቻ፣ የመልክአ ምድር አቀማመጧ፣ ለአውሮፓና ለመካከለኛው ምስራቅ ያላት ቀረቤታ እንዲሁም ፈጣን እና አስተማማኝ አገልግሎት የሚሰጠው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለአበባ ኢንቨስትመንት ልማት ማደግ በዋናነት ተጠቃሽ መሆናቸውን አመልክተዋል። የእነዚህ ድምር ውጤትም ኢንዱስትሪው በአገሪቱ እንዲስፋፋና በስኬት መስመር ውስጥ እንዲገባ አስተዋጽኦ የጎላ ነው ብለዋል።

በአገሪቱ ምጣኔ ሃብታዊ ዕድገት ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እያበረከተ የሚገኘው የሆርቲካልቸር ዘርፍ በተለይ አበባ አንድ ሺ ስድስት መቶ የሚጠጋ ሄክታር መሬት ላይ እየለማ እንደሆነ የጠቀሱት ፕሬዝዳንቱ፤ ከዚህ በበለጠ ስፋት ባለው መሬት ላይ መልማት ቢችል ዘርፉ የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆንም ነው ያስገነዘቡት። ለዚህም ማህበሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት እየሠራ እንደሆነ ገልጸዋል።

የውጭ ምንዛሪን በማምጣት፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠርና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ረገድ የጎላ አበርክቶ ያለውና በዕድሜ ትንሹ የሆነው የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ከቡና ቀጥሎ ተሰፋ የተጣለበት ዘርፍ ስለመሆኑም በውጭ ምንዛሬ ግኝት በኩል እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ይጠቀሳል። በሥራ ዕድል ፈጠራም ተጠቃሽ መሆን ችሏል፤ በአበባው ዘርፍ ብቻ ከሁለት መቶ ሺ በላይ ለሚደርሱ ዜጎች በቋሚነት የሥራ ዕድል መፍጠር አስችሏል።

የኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማህበር 120 የሚደርሱ አምራች ላኪዎችን በስሩ ያቀፈ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል 80 በመቶ የሚሆኑት በአበባ ምርት የተሰማሩ ናቸው። ቀሪዎቹ 20 በመቶዎቹ ደግሞ በአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በእጸጣዕም ምርት የተሰማሩ ስለመሆናቸው ከማህበሩ የተገኘው መረጃ ያመላክታል። ማህበሩ የዛሬ 20 ዓመት ሲመሰረት አምስት የአበባ አምራቾችን ብቻ ይዞ ሲሆን፤ በወቅቱ አበባን ብቻ አምርቶ ወደ ውጭ ገበያ ያቀርብ ነበር።

ፕሬዝዳንቱ እንዳሉት፤ ማህበሩ ሥራውን በአበባ ምርት ብቻ የጀመረ በመሆኑ በስፋት አምርቶ ወደ ውጭ ገበያ የሚልከውም ይህንኑ የአበባ ነው። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእጸጣዕም ምርቶችን በማምረት ወደ ውጭ ገበያ መላክ ውስጥ ገብቷል። በዚህም አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል። በዘርፉ ተሳታፊ የሆኑትም 24 የሚደርሱ የማህበሩ አባላት ናቸው።

ከአጠቃላይ ሆርቲካልቸር ዘርፍ የአበባ ምርት ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ ይናገራሉ። አሁን አሁን የአትክልትና ፍራፍሬ ገበያም ተወዳዳሪ እየሆነ መምጣቱን ፕሬዝዳንቱ አስረድተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከአትክልትና ፍራፍሬ መካከል በተለይም የስትሮብሪ ምርት በአገሪቱ በስፋት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እየቀረበ ይገኛል። አቦካዶ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በስፋት እየተመረተ ያለ ሲሆን፣ ሶስት አልሚዎችም ወደ ሥራው ገብተው ማምረት ጀምረዋል። ይህም በቀጣይ እንደ አበባው ሁሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፉ የተሻለ ውጤት በማስመዝገብ ውጤታማ መሆን እንደሚችል አመላካች ነው።

አገሪቷ በአየር ንብረት፣ ውሃ ሀብት፣ ለም አፈር የታደለች በመሆኗ በዘርፉ በስፋት መሥራት እንደሚገባ ያስገነዘቡት ፕሬዝዳንቱ፤ በተለይም አነስተኛ በሆነ ቦታ ላይ በማምረት ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል ዘርፍ መሆኑም ከሌሎች የግብርና ዘርፎች ለየት ያደርገዋል ብለዋል። ስለዚህ አገሪቷ ለዘርፉ ያላትን እምቅ አቅምና ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነቷን ይበልጥ ማረጋገጥ የሚጠበቅባት ጊዜ አሁን ነው ሲሉም ያስገነዝባሉ።

በተለይም የአበባው ዘርፍ ከቡናና ከሌሎች የግብርና ምርቶች አንጻር ሲታይ ትልቁን ድርሻ በመያዝ ከቡና ቀጥሎ ሁለተኛው የውጭ ምንዛሪ የሚገኝበት ዘርፍ መሆኑን ይገልጻሉ፤ አትክልትና ፍራፍሬም እንዲሁ እየተነቃቃ መሆኑን አመልክተው፣ ይህም የበለጠ ውጤታማ መሆን እንዲችልም ስራውን አጠናክሮ ማስቀጠል ይጠይቃል ብለዋል።

መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት ውጤታማ መሆን እንደተቻለ ያመለከቱት ፕሬዚዳንቱ፤ በተለይም በአሁኑ ወቅት ለዘርፉ ማነቆ የሆኑ የአሰራር ችግሮችን እየፈታ፤ በአዲስ ፖሊሲና በአዳዲስ እሳቤዎች ወደ ተግባር እየገባ ነው ይላሉ። ይህም ኢትዮጵያ ያሏትን በርካታ እምቅ አቅሞች መጠቀም እንድትችል ዕድል እንደሚፈጥርላት ተናግረው፣ መንግሥት ለዘርፉ እያበረከተ ካለው አስተዋጽኦ ጎን ለጎንም ማህበሩ ዘርፉን ለማነቃቃት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ማህበሩ የተለያዩ ኤክስፖዎችን በማዘጋጀት አገሪቷ ለኢንቨስትመንት ምቹ እንደሆነች በማስተዋወቅ እንዲሁም የገበያ ትስስር በመፍጠር ረገድ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ነው። ለአብነትም ከየካቲት 29 እስከ መጋቢት 1 ቀን 2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራቾችና ላኪዎች ማህበር አዘጋጅነት በሚሊኒየም አዳራሽ የተካሄደውን ስምንተኛውን የሆልቲካልቸር ዓለም አቀፍ ኤክስፖ ይጠቀሳል።

ኤክስፖውም ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ዘርፍ ያላትን እምቅ አቅም የማስተዋወቅና ዓለም አቀፍ የገበያ ትስስርን የመፍጠር፣ የአቅርቦት ሰንሰለትን የማሳደግ እንዲሁም የተወዳዳሪነት አቅምን የማጎልበት ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑ ተገልጿል።

በኤክስፖ መክፈቻ ላይ የተገኙት የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ፤ የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ በአሁኑ ወቅት በግብርናው ዘርፍ ከቡና ቀጥሎ ትልቁ የውጭ ምንዛሬ ግኝት መሠረት መሆኑን ተናግረዋል። መንግሥት ዘርፉን ለማሳደግ አዲስ እያዘጋጀ ባለው የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲም ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከቡናና ሌሎች ኤክስፖርት ከሚደረጉ ምርቶች አንጻር የአበባ ዘርፍ ሁለት አስርት ዓመታት ያህል ዕድሜ ያለው ቢሆንም፤ ባጠረ ጊዜ ውስጥ በአነስተኛ ቦታ ላይ ጥሩ ውጤት እያሳየ መጥቷል። የአገሪቱ የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ከቡና ቀጥሎ ሁለተኛው ትልቁ የውጭ ምንዛሬ የሚገኝበት ሆኗል። ዘርፉ ከውጭ ምንዛሬ ግኝቱና ከሥራ ዕድል ፈጠራ አኳያ ሲታይ በእርሻ ኢንቨስትመንት በውስን ቦታዎች ሰፊ የሥራ ዕድል እየተፈጠረ እንደሆነም አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ካላት አግሮ ኢኮሎጂና የአየር ንብረት አንጻር የአትክልትና ፍራፍሬ ዓይነቶች ከየትኛውም አገር የተሻለ እምቅ ሀብት ያላት መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፉ፤ የግብርና አምዶች በሆኑት በምግብ ዋስትና ራስን መቻል፣ ወጪ ምርትን መጨመር፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ እያሳየ ያለው ሂደት አበረታች እንደሆነም አመላክተዋል።

የተዘጋጀው ኤክስፖም ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ያላትን እምቅ አቅም ለማስተዋወቅና ዓለም አቀፍ የገበያ ትስስርን ለመፍጠር፣ የአቅርቦት ሰንሰለትን ለማሳደግ እንዲሁም የተወዳዳሪነት አቅምን ለማጎልበት ትልቅ ፋይዳ እንዳለውም ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ በአበባ ኤክስፖርት ከአፍሪካ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ስትሆን ከዓለም በአራተኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ከኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ላኪዎች ማህበር የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ሀገሪቱ በተያዘው 2015 በጀት አመት ከ770 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት መታቀዱን መረጃዎች ያመለክታሉ። ባለፉት ሰባት ወራት 414 ሚሊየን ዶላር ተገኝቷል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# ‹‹የጀሎ ደቀዬ›› የሕዝብ መዝናኛ ፓርክ - ቀጣዩ የሆሳዕና ከተማ ፈርጥ



መሳኩ ኤርሴ

‹‹የጀሎ ደቀዬ›› (ጎፈር ሜዳ) በሆሳዕና ከተማ የሚገኝ ሰፊ የወል መሬት ነው።ይህ መሬት ለበርካታ አሥርት ዓመታት ከተማዋ የውሃ ጥሟን ለማርካት ስትጠቀምበት የነበረው ሰው ሰራሽ ሀይቅ መገኛም ነው።አካባቢው የሀይቁ መገኛ በመሆኑ የውሃ ልማት አካባቢ ተብሎ ለዘመናት ተከልሎ ኖሯል።

የሆሳዕና ከተማ ነዋሪዎች በዚህ ሜዳ ብዙ ትዝታ አላቸው።በሀይቁ ዙሪያ ያለው ሰፊ ሜዳ ለከተማው ነዋሪ እና ለመላው የሀዲያ ዞን ሕዝብ አገልግሎት ሲሰጥ ኖሯል። የሕዝብ መሰባሰቢያ፣ የሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክዋኔዎች ማካሄጃ፣ የልጆች መቦረቂያ፣ የእግር ኳስ ሜዳ፣ የመኪና ማለማመጃ እንዲሁም የእንስሳት ማሰማሪያ ሆኖ አገልግሏል።

በየዓመቱ ለሚከበረው የሀዲያ የዘመን መለወጫ (ያሆዴ) በዓል ለማክበር የሚውል ‹‹ ሆዲይ ነፈራ ››ፕሮጀክት የተገነባውም ከዚሁ የወል መሬት ተቆርሶ ነው።‹‹ጀሎ ደቀዬ›› በከተማዋ ውስጥ የሚገኝ ለጥ ያለ ሰፊ ሜዳ እንደመሆኑ የብዙዎችን ቀልብ ስቧል።መቀራመት የሚሹ አካላት አይንም አርፎበታል።በተለያዩ ወቅቶች ከዚህ ሜዳ ተቆርሶ ለተለያዩ አካላት ተላልፏል።ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየጨመረ የመጣው ሜዳውን የመቀራመት አባዜም በከተማዋ ነዋሪዎች እና በመላው የሀዲያ ሕዝብ ዘንድ ስጋትን ፈጥሮም ነበር።

የከተማዋ ነዋሪዎች እና መላው የሀዲያ ሕዝብ መሬቱ ለግለሰቦች እና ለቡድኖች ተላልፎ ሊሰጥ አይገባም በማለት አስቁመዋል።ባለፉት ዓመታትም እንዲሁ ለተለያዩ አካላት ለማከፋፈል እንቅስቃሴዎች መደረጋቸውን ተከትሎ የሀዲያ ከቤራዎች (ለውጥ ፈላጊ የሀዲያ ወጣቶች) ባደረጉት ትግል ይህንን የወል መሬት ከተቀራማቾች እጅ ማስጣል ተችሏል።

ይህ የወል መሬት በአሁኑ ወቅት በውስጡ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ያቀፈ በሕዝብ መዝናኛ ፓርክነት እንዲለማ እየተደረገ ነው።የሆሳዕና ከተማ ከንቲባ አቶ ሊሬ ጀማል እንደሚሉት፤ በፓርኩ ውስጥ የስፖርት ማዘውተሪያ፣ የወጣቶች ስብዕና ግንባታ ማዕከል፣ መዋኛ ገንዳዎች እንዲሁም ሄሊኮፕተር ማረፊያ ይገነባል።‹‹በጀሎ ደቀዬ›› ላለፉት በርካታ አሥርት ዓመታት አገልግሎት ሲሰጥ የቆየውን ሰው ሰራሽ ሀይቅ ለማስፋት እና ዓሳ በስፋት ለማልማትም ታቅዷል።የዓሳ ልማቱ ለበርካታ ወጣቶች የሥራ እድል እንደሚፈጥርም ታምኖበታል፡፡

እስከ አሁን በከተማው ውስጥ ሁለገብ መዝናኛ እና የወጣቶች የስብዕና ግንባታ ማዕከላት እምብዛም የሉም ያሉት አቶ ሊሬ፣ የፓርኩ ግንባታ የመዝናኛና የስብዕና ማዕከላት እጥረት ችግርን ከመቅረፍ አኳያ ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።ፓርኩ ሲጠናቀቅ የከተማውን ማህበረሰብ አኗኗር ዘይቤ ከመቀየር ባሻገር ለወጣቶች ሥራ እድል እንደሚፈጥር ጠቅሰው፣ ፓርኩ በከተማዋ ትልቁ የሕዝብ መዝናኛ እንደሚሆንም ነው ያመለከቱት።ፓርኩ የከተማዋን ገቢ ማሳደግ እንደሚያስችልና ለከተማዋ ተጨማሪ ውበት በመሆን እንደሚያገለግልም ጠቁመዋል፡፡

የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች በስፋት አለመኖር ወጣቶች አልባሌ ቦታ እንዲውሉ እና ለተለያዩ ሱሶች እንዲጋለጡ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የተናገሩት አቶ ሊሬ፤ ግንባታው እየተፋጠነ ያለው የሆሳዕና የሕዝብ መዝናኛ ፓርክ ወጣቶች አልባሌ ቦታዎች እንዳይውሉ፤ ሱስ ውስጥ እንዳይገቡ ሚናው የላቀ ነው ብለዋል።ጤናማ ትውልድን ለመፍጠር ከፍተኛ ሚና እንደሚያበረክት ጠቅሰው፣ ለነገ አገር የሚጠቅም ብቁ ዜጋ ለመፍጠር ለሚደረገው ጥረት አገዛው ከፍ ያለ መሆኑን ጠቁመዋል።

ፓርኩ በ105 ሄክታር መሬት ላይ የተንጣለለ ሲሆን፣ የፓርኩ ግንባታ ፕሮጀክት የተጀመረው በ2013 ዓ.ም በሰኔ ወር ነው ።ፓርኩ እየተገነባ ያለው በ700 ሚሊዮን ብር ካፒታል በጀት ነው።የፓርኩ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራ በሁለት ሎት ተከፍሎ እየተካሄደ ሲሆን፤ የመጀመሪያው ምዕራፍ ሥራ እየተጠናቀቀ ይገኛል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ የፓርኩን ዙሪያ አጥር መከለል፣ የመግቢያና የጥበቃ በር፣ የእግረኛ መንገድ፣ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች፣ የመቀመጫ ወንበሮች፣ የመኪና ማቆሚያ ተገንብተዋል። የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራ ላይ 75 ሚሊዮን ብር ፈጅቷል።የፕሮጀክቱን ግንባታ በሰባት ዓመት ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነው ሥራው የተጀመረው።

እንደ አቶ ሊሬ ማብራሪያ፤ ፓርኩ ለከተማዋ እድገት መሰረት ነውና ሀይቁን በማስፋት ዓሳን በማምረት የምግብ ምንጭ ከመሆኑም ባሻገር የአየር ንብረትን ሚዛን በማስጠበቅ ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚኖረውም ተስፋ ተጥሎበታል።

የዚህ የወል መሬት ጉዳይ ለብዙ ዘመናት የከተማዋ ወጣቶች ጥያቄ ሆኖ መቆየቱን የጠቀሱት አቶ ሊሬ፤ አሁን እየተገነባ ያለው ፓርክ የከተማዋን ወጣት የዘመናት ጥያቄ የመለሰ መሆኑን ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱን በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ ፕሮጀክቱን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የፋይናንስ እጥረት ተግዳሮት መሆኑን ገልጸዋል።የፋይናንስ እጥረቱን ለመቅረፍ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከዓለም ባንክ ፕሮግራም በተገኘ ገንዘብ እና በከተማ አስተዳደሩ በተበጀተ ገንዘብ ግንባታው እየተካሄደ መሆኑን አስታውቀዋል።

የምዕራፍ አንድ ሥራ በጥሩ ፍጥነት መከናወኑን የጠቆሙት የሆሳዕና ከተማ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ተቋማዊ የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም አስተባባሪ አቶ ዘነበ ዳኘቸው፣ በምዕራፍ ሁለት ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚዎች የሚውሉ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ጨምሮ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ ፋውንቴን እና የህዝብ ቤተመጻህፍት እየተገነቡ መሆናቸውን ገልጸዋል። የፕሮጀክቱ ሂደት በየጊዜው እየተገመገመ በቀጣይ ደረጃቸውን የጠበቁ የማህበራዊ አገልግሎቶች መከወኛ ስፍራዎች ለማድረግ እንደሚሰራም አመላክተዋል።

በቀጣይ ምዕራፍ የህጻናት መጫዎቻዎችን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎት መስጫዎች በፓርኩ ውስጥ እንደሚገነቡ የጠቆሙት አቶ ዘነበ፣ ወደፊት ፓርኩ በአካባቢው ተመራጭ ቦታ እና የተለያዩ ማህበራዊ ክዋኔዎች የሚከናወኑበት እንዲሆን በትኩረት እንደሚሰራም አስታውቀዋል።

የሀዲያ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ አብርሃም መጫ በበኩላቸው ፓርኩ ካለው ስፋት እና ሁሉንም የመዝናኛ አይነቶች በአንድ ስፍራ አካቶ የያዘ በመሆኑ በአገር አቀፍ



ፓርኩ እየተገነባ ያለው በአንድ መቶ አምስት ሄክታር መሬት ላይ ነው

ደረጃ ከምናውቃቸው ፓርኮች ለየት ያደርገዋል። ይህም ለሆሳዕና ከተማ ገጽታ ግንባታ እንደ ዕድል ይወሰዳል። ፓርኩን ገንብቶ ለማጠናቀቅ የሚጠይቀው የግንባታ ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ የዓለም ባንክ ፕሮጀክት አካል ተደርጎ እየተሰራ ነው።

ግንባታውን በሰባት ዓመታት ውስጥ ለማጠናቀቅ የየዓመቱ እቀድ ወጥቶ እየተሰራ መሆኑን የጠቆሙት ዋና አስተዳዳሪው፤ የሁለት ዓመት ሥራው መጠናቀቁንና የሦስተኛውን ዓመት ሥራ እስከ ሰኔ 30 ለማጠናቀቅ እንደሚሰራም ገልጸዋል።

ይህን ጨምሮ የቀጣይ ዓመት ሥራ ሲጠናቀቅ ፓርኩ አሁን ካለው ገጽታ በበለጠ ሳቢ እንደሚሆን ጠቅሰው፣ ሀብት ለማመንጨትና ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል አደረጃጀት ተፈጥሮ እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

የከተማው ነዋሪዎች በበኩላቸው ከጥቂት ዓመታት በፊት ‹‹ጀሎ ደቀዬ›› (ጎፈር ሜዳ) ለተለያዩ አካላት ሊከፋፈል ነው የሚል መረጃ ሰምተው አዝነው እንደነበር አስታውሰው፣ ሜዳው ከቅርምት ተርፎ ወደ ፓርክነት በመቀየሩ ወጣቶቹ ደስታ እንደተሰማቸው ይናገራሉ።ፓርኩ በከተማዋ ውስጥ የሚስተዋለውን የመዝናኛ ቦታ እጥረት የሚቀርፍ ይሆናል ብለዋል፡፡

አቶ ታገሰ ላምቤ በሆሳዕና ከተማ የረጅም ዘመን ነዋሪ ናቸው።ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ ቦታው ሜዳ እንደነበር ያስታወሳሉ።በልጅነት ዘመናቸው በሜዳው ላይ ቦርቀዋል፤ ከብቶችም አግደውበታል።በወጣትነት እድሜያቸው ደግሞ በዚህ ሜዳ ብዙ ትዝታ አላቸው።ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን የሜዳው አጠቃቀም ወደ አስቸጋሪ አቅጣጫ ሲያመራ እንደነበር ጠቅሰው፣ ሁሉም ሜዳው ላይ ዓይኑን ጥሎ እንደነበር ያስታውሳሉ።

ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ የዞኑ መንግሥት እና ከተማ አስተዳደሩ በመተባበር ቦታውን ፓርክ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን የተናገሩት አቶ ታገሰ፤ ቦታው ከቅርምት ተርፎ በማየታቸው ደስተኛ መሆናቸውን ነው የገለጹት።ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ከተማዋ ሰዎች ራሳቸውን የሚያዝናኑበትም ሆነ ነፋሻማ አየር የሚወስዱበት፣ ለሰዎች አዕምሮ ማደሻ ስፍራዎች ሊኖራት የተገባ መሆኑን የከተማዋ ወጣቶች በመጥቀስ፣ በከተማዋ በሚፈለገው ልክ መሰል አገልግሎት የሚሰጡ ፓርኮች ባለመኖራቸው ምክንያት ወጣቶች አልባሌ ቦታዎች ለመዋል ይገደዱ እንደነበር ይናገራሉ።አዲሱ ፓርክ በተለይም ወጣቶች ራሳቸውን የሚያዳምጡበት ቦታ እንዲሆን እንደሚፈልጉም ይጠቁማሉ።በሌሎች አካባቢዎች የሚመለከቱትን አይነት መዝናኛ በከተማዋ ለማየት በመቃረባቸው ተደስተዋል።

ፓርኩ መገንባቱ ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው። ፓርኩ መገንባቱ ብቻውን ግን በከተማዋ ውስጥ ያለውን የመዝናኛ እጥረት አይፈታውም።በአገሪቱ አንዳንድ ፓርኮች ከአጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚታዩ ችግሮች በዚህ ፓርክም እንዳያጋጥም ጥንቃቄ ሊደርግም ይገባል።ፓርኩ ሕገ ወጥ ለሆኑ ተግባራት ማከናወኛ እንዳይሆን ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግበት ያስፈልጋል።በተለይም አደንዛዥ እጽ መጠቀም፣ ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ የመሳሰሉ ተግባራት በፓርኩ ውስጥና አካባቢ እንዳይለመዱ ጥንቃቄ ማድረግ ይሻል።

ሕዝቡ ከዚህ ቀደም ‹‹ጀሎ ደቀዬን›› ከቅርምት ለመከላከል ያሳየው አይነት ቁርጠኝነት ፓርኩን በባለቤትነት ስሜት በመጠበቅና በመንከባከብ ላይም ሊደግም ይገባል።በፓርኩ አጠቃቀምና አያያዝ ዙሪያ ሕገ መንግሥቱን፣ የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲን፣ የኢትዮጵያ የከተማ ልማት ፖሊሲን እንዲሁም የከተማ ፕላን አዋጅን እንደ መነሻ በመውሰድ ግልጽ ሕጎች እና መመሪያዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኑሮ ውድነቱ ልጓም ሊበጅለት ይገባል!

ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁንም የሚተዳደረው በግብርና ነው፡፡ ኢትዮጵያም ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት በሚታረስ የእርሻ መሬትና በግብርና ምርት ቀዳሚ ሀገር ናት፡፡ ሆኖም በተቃራኒው የግብርና ምርቶችና ሌሎች መሰረታዊ አቅርቦቶች እጥረት ካለባቸውና ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ከሚታይባቸው ሀገራትም አንዷ ናት፡፡ በአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣምና በተለያዩ ብልሹ አሰራሮች ምክንያት በየቀኑ እየጨመረ የሚሄደውም የሸቀጦች ዋጋ መናር በዜጎች ላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነትን በመፍጠር ሕዝቡን ለምሬት እየዳረገ ነው፡፡

በተለይም ሕብረተሰቡ በዕለት ተዕለት በሚጠቀምባቸው መሰረታዊ ፍጆታዎች ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ንረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዜጎችን ሕይወት እጅግ እየተፈታተነው ይገኛል። በእህል፣ በጥራጥሬ ፤ በአትክልት ምርቶች፤ በግንባታ ዕቃዎች እና በቤት ኪራይ ላይ የዋጋ ጭማሪው አሳሳቢ ሆኗል፡፡ ነገሩን ይበልጥ ከባድ የሚያደርገው ደግሞ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እየተመዘገበ ያለው የምግብ ነክ ሸቀጦች ላይ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ላይ ትራንስፖርት፣ የትምህርት ቤት ክፍያና የመሳሰሉት ሲጨመሩበት የሕዝቡን ኑሮ ችግሩን ከድጡ ወደ ማጡ እያደረገው ነው፡፡

በየቀኑና በየሰዓቱ የሚጨምረው የሸቀጦች ዋጋ በተለይም ዝቅተኛው የኀብረተሰብ ክፍል ኑሮ በጣም እንዲከብደው ምክንያት ሆኗል፡፡ መሸቶ በነጋ ቁጥር «ከገበያ ጠፍተዋል»፤ «ዋጋ ጨምሯል» የሚሉት አገላለጾች ኀብረተሰቡን በችግር ውስጥ እንዲኖር እያደረጉት ነው፡፡

የኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብት ከፍተኛ ፈተና እየገጠመው ያለው ከዋጋ ግሽበት በተያያዘ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገለጽ ቢሰማም ችግሩን ለመቅረፍ የተኬደበት ርቀት አናሳ መሆኑን በየሰዓቱ የሚጨምረው የሸቀጦች ዋጋ መናር በቂ ማሳያ ነው፡፡ ምግብ ነክ የሆኑና መሠረታዊነታቸው የታመነባቸው የፍጆታ ዕቃዎች በፍራንኮ ቫሉታ አሠራር ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ እና የመድኃኒት፣ ነዳጅ ፣ ማዳበሪያ፣ ዘይት እና ሌሎችም መሠረታዊ ሸቀጦች ግዢ አቅርቦት እንዲቀላጠፍ የማስተካከያ ርምጃ የተወሰደ ቢሆንም የኑሮ ውድነቱን ወደ ላይ ከመገስገስ ያቆመው አንዳች ምድራዊ ኃይል አልተገኘም፡፡

በኢትዮጵያ ባለፉት አራት ዓመታት በተሰሩ የግብርናውን የማዘመን ስራዎች በሀገሪቱ ምርታማነት እንደጨመረ ቢታመንም በተለያዩ ሕገወጥ አሰራሮችና የቁጥጥር መላላት ምክንያት ምርቱ ሸማቹ ህብረተሰብ ጋር በቀላሉ ለመድረስ ካለመቻሉም በሻገር የዋጋ ንረትም እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል፡፡ በተለይም በሕገወጥ ኬላዎች አካባቢ የሚታየው ሥርዓት አልበኝነት የሰብል ምርቶች ዋጋ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሊያሻቅብ ችሏል፡፡ በየኬላው የሚፈጸመው ሕገወጥ ቀረጥና ብልሹ አሰራሮች የግብርና ምርቶች ወደ ተጠቃሚው በቀላሉ እንዳይደርስ እንቅፋት ከመሆኑም ባሻገር በተለይ በከተሞች አካባቢ የዋጋ ንረት እንዲባባስ ምክንያት እየሆኑ መጥተዋል፡፡

ከታህሳስ እስከ የካቲት ባሉት ወራት በኢትዮጵያ ምርት ወደ ገተራ የሚገባበትና በገበያው ውስጥም ምርት በስፋት የሚታይበት ቢሆንም ባለፉት ወራት የታየው የዋጋ ግሽበት ከዚህ እውነታ የተለየ ነው፡፡ በመሳለሚያና በመርካቶ አካባቢ ያሉ ነጋዴዎች እንደሚናገሩትም በየካቲት ወር ብቻ በጤፍ፤ በዱቄት፤ በፓስታና መኮረኒ ላይ የታየው የዋጋ ጭማሪ አስደንጋጭ ነው፡፡ ጤፍ በአንድ ወር ብቻ በኩንታል እስከ ሁለት ሺህ ብር ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ፓስታና መኮረኒ ላይ በአንድ ወር ብቻ በኪሎ እስከ 30 ብር ጭማሪ ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ በአሳሳቢ ሁኔታ የኀብረተሰቡን ጫንቃ እያጎበጠ ያለውን የኑሮ ውድነት አሳስቦት ተገቢ የሆነ መፍትሄ ለማፈላለግ የሚደረገው ጥረት ከችግሩ መጠንና ፍጥነት ጋር የሚመጣጠን አልሆነም፡፡ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶችም የችግሩን አሳሳቢነት ከመቀበል ይልቅ አንዱ ወደ አንዱ እየወረወረ ችግሩ መፍትሄ አልባ ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ በየቀኑ እንደ ሸምጥ ፈረስ የሚወረወረው የኑሮ ውድነት የአብዛኛውን ድሃ ኀብረተሰብ ወገብ እያጎበጠና ከባድም የኑሮ ፈተና እየሆነ መምጣቱን አምኖ ለችግሩ ትኩረት መስጠት የመፍትሄው አንድ እርምጃ ሊሆን ይገባል፡፡ መንግሥትን ጨምሮ ነጋዴዎችና ሌሎችም የዘርፉ ተዋንያን በተጨባጭም ለኑሮ ውድነቱ ተገቢውን ትኩረት መስጠቱን የሚያረጋግጡ ርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ የአቅርቦት ሥርዓቱን ማስተካከልና ምርታማነት ማሳደግ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል፡፡


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከሁሉም በላይ መስከን ይጠበቅብናል

ዶክተር ጀኔኑስ

በአገራችን ሰሞነኛ የተለያዩ ከበስተጀርባቸው ጥፋቶችን ያነገቡ ክስተቶች ተከስተዋል፤ ያስከፈሉንም፣ ዋጋ ቀላል ነው ተብሎ የሚጠቀስ አይደለም በእኔ እምነት ነገሮችን በሰከነ መንገድ ማየት ቢቻል እነዚህ ነገሮች ባልተከሰቱ ነበር ብዬ አምናለሁ። የችግሮች ዋነኛ ችግር መስከን አለመቻላችን ነው። መስከን ለበርካታ ነገሮች መፍትሄ ነው። በሰከነ አዕምሮ ውስጥ መፍትሄ አለ። በሰከነ አዕምሮ ውስጥ የተረጋጋ ሥዕብና አለ። በሰከነ መንደር ውስጥ በጥባጮች ቦታ የላቸውም።

«ሠላምን በጉልበት ማስጠበቅ አይቻልም። ሠላምን ማሳካት የሚቻለው በመግባባት ብቻ ነው» ይላሉ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን። እንግዲህ ችግሮች ሲከሰቱ መቋጫው ሠላም ማምጣት ነው። ነገር ግን ነገሮች መፍትሄ አላቸው በሚል እሳቤ ብቻ ችግር መፍጠር ተገቢ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ «ካልደፈረሰ አይጠራም» የሚለው አገርኛ አባባል ሳይጠናወተን አልቀረም ብዩ ለማሰብ እገደዳለሁ ።

> **ሠላም፤ አንድነትና የብሄራዊ መግባባት የአንድ አገር የጀርባ አጥንት ናቸው። በዚህ ላይ ፖለቲከኞች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ምዕምናን፣ ምሁራን እና ሌሎች አካላትም የተለያዩ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ቢሆንም በአገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት ይጠበቅባቸዋል**

ለመጥራት የግድ መደፍረስ የለበትም። ሳይደፈርስ ገና በጅምሩ መሰረት ማስያዝ ይቻላል። ሰሞኑን የገጠመን ነገር ይህ ነው። ጥቂቶች ሐሳባቸው ነገሩ ይደፍርስ የሚል ይመስላል። የለም! የለም! መደፍረስ ያለበትንና የሌበትን ማወቅ ይገባል። ቀይ መስመሮችን እንዳሻን ከተረማመድንባቸው ውጤታቸው አደገኛ ነው።

ከሁሉም በላይ በሃይማኖት እና በፖለቲካው ጎራ የታየው መደበላለቅ የከፋ እንደነበር ይሰማኛል። «ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል» እንደተባለው ሁሉም በራሱ አውድ ሲመከርበትና ሲዘከርበት ፍሬያማ ይሆናል። አንዱን ከሌላው እያጋጩና እየበጠበጡ ጥሩ መመኘት ህልም ነው የሚሆነው።

በዚችህ አገር አንድ የበላይ ሌላው የበታች የሚሆንበት አካሄድ መኖር የለበትም። ለአንዱ ህግ የሚከበርለት ለሌላው መብቱ የሚገረሰስበት አግባብም መፈጠር የለበትም። ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ብቻ በአገሪቱ አውድና ህግ መሠረት ሁኔታዎችና ህጎች ሊከበሩና ሊተገበሩ ይገባል።

በመገፋፋት ላይ የተመሰረተች አገር መሆን የለባትም- ኢትዮጵያ። አንዳችን ሌላኛችንን አቅፈን ደግፈን ወደ ተሻለ ምዕራፍ የምንሸጋገርበት፤ ተከባብረን ተቻችለን የምንጓጓዝበት የጋራ ሃዲድ ነው መሆን ያለባት፤ መሆንም ያለበት ይኸው ነው።

ለዚህ ሃሳብ ማጥኛ ይሆን ዘንድም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በበዓለ ሲመታቸው ወቅት ለህዝብ እንደራሴዎች ያደረጉትን ንግግር ማስታወስ ይበጃል። «ማንነታችንን እንዳይለያይ ሆኖ የተሰናሰለ፣ እንዳትነጣጠል ሆኖ የተገመደ፣ የተዋደደ እና የተዋሀደ ነው። አማራው በካራ-ማራ ለአገሩ ሉዓላዊነት ተሰውቶ የካራ-ማራ አፈር ሆኖ ቀርቷል። ትግራዋይ በመተማ ከአገሬ በፊት አንገቴን ውሰዱ ብሎ የመተማ አፈር ሆኗል።

"ኦሮሞው በአድዋ ተራሮች ላይ ስለአገሩ ደረቱን ሰጥቶ የአገሩን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ከአድዋ አፈር ተቀላቅሏል። ሱማሌው፣ ሲዳማው፣ ቤኒሻንጉል፣ ወላይታ፣ ጋምቤላው፣ ጉራጌው፣ አፋሩ፣ ስልጤው፣ ከምባታው፣ ሀዲያው እና ሌሎቹም የኢትዮጵያ ህዝቦች ሁሉ በባድመ ከአገሬ በፊት እኔን ብለው እንደወደቁ ከባድመ አፈር ጋር ተዋህደዋል።

"አንድ ኢትዮጵያዊ አባት እንዳሉት እኛ ስንኖር ሰዎች፣ ስናልፍ አፈር፣ ስናልፍ አገር እንሆናለን። የየትኛውንም ኢትዮጵያዊ ከቡር ስጋና ደም በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ አፈር ሆኖ ታገኙታላችሁ። ኢትዮጵያውያን ስንኖር ኢትዮጵያ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ እንሆናለን» ሲሉ ነበር በርካቶቻችን ማንነታችን፣ እምነታችን፣ እሴታችን አንዳችን ከሌላችን ጋር ተሳሰረ ስለመሆኑ አበክረው የተናገሩት።

ኢትዮጵያ ማለት ውሃዊ ስሪት ነው። በውሃ ውስጥ ሃይድሮጂን እና ኦክሲጅን የተሰፉ ንጥረ ነገሮች ስሪት ነው። ነገር ግን ሃይድሮጅን ከኦክስጂን እንለይና ውሃ እናገኛለን ብለን ብንነሳ አስቸጋሪ ነው። ድምዳሜያችንም ሆነ አካሄዳችን ሌላ ውጤት ላይ ይወስደናል።

ይህ ማለት ኢትዮጵያዊ የሆነን አንድ ዜጋ በሃይማኖቱ፣ በብሄሩ ወይንም ደግሞ አንዱ መገለጫው ወስደን ከሌላው አካሉ ከሆነ ኢትዮጵያዊ ለመለየት ብንሞክር ኦክስጂን እና ሃይድሮጂንን ለየብቻ በመለየት ውሃ ለማግኘት እንደመመኘት ነው፤ አይሆንም፤ አይሳካም።

ኢትዮጵያዊነት ማለትም ልክ እንዲሁ ነው። አጋጣሚዎችን በመጠቀምና ሁኔታዎችን በመታከክ ኢትዮጵያዊነት ለመሸርሸር የሚደረጉ ሙከራዎችም ለጊዜያዊ ሆህታ ላይ አዋኪ ድምፅ ይሆናሉ እንጂ ውሃ የሚቋጥር አይሆንም።

የዛሬ ሃሳቤን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአንድ ወቅት የተናገሩትን በማስታወስ ለማቆም እገደዳለሁ። «ኢትዮጵያ የሁላችን አገር፤ የሁላችን ቤት ናት። በአንድ አገር ውስጥ የሀሳብ ልዩነቶች ይኖራሉ። የሀሳብ ልዩነት እርግማን አይደለም። ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ መደማመጥና በመርህ ላይ ተመስርተን መግባባት ስንችል የሀሳብ ልዩነት በረከት ይዞልን ይመጣል። በሀሳብ ፍጭት ውስጥ መፍትሄ ይገኛል።

"በመተባበር ውስጥ ኃይል አለ። ስንደመር እንጠነክራለን። አንድነት የማይፈታው ችግር አይኖርም... አገር ይገነባል። የኔ ሐሳብ ካላሸነፈ ሞቼ እገኛለሁ ማለት ግን እንኳን አገርን ሊያቆም ቤተሰብን ያፈርሳል። ያለችን ኢትዮጵያ ነች፤ ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት በላይ አገራዊ አንድነት ይበልጣል። አንድነት ማለት ግን አንድ ዓይነትነት ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። አንድነታችን ልዩነቶቻችንን ያቀፈ ብዝሃነታችንን በህብረ-ብሔራዊነት ያደመደቀ መሆን አለበት»

ሲጠቃለል የሰው ልጆች ነንና በአስተሳሰባችን፣ በአስተዳደጋችን፣ በመጣንበት ማህበረሰብ፣ የቀሰምነው እውቀት ብሎም በአነጋገራቻን እና በመሳሰሉት ነገሮች ልንለያይ እንችላለን። ግን ዋና መሠረቱና የሚያመሳስሉንና የሚያስተሳስሩን ነገሮች ላይ በችግሮችም ውስጥ ብንሆንም ኢትዮጵያ ማለት በቃ ኢትዮጵያ ናት። በማንም እና በምንም የማንተካት አገራችን መጠበቅ አለብን። ነገሮችን በተረጋጋ መንገድ መመልከት ይገባል።

እንደ አገር የምንግባባቸው ጉዳዮች የጋራ ጉዳይ ሲሆኑ ህዝባችን የተረጋጋ አገር እንዲኖረው ይፈልጋል። መብቱ እንዲከበር፤ ሉዓላዊነት ተከብሮ አገር ከፍ እንድትል፤ ዕድገት እንዲኖር፣ ፍትህ ማስፈን እና ልማት እንዲፋጠን ብሎም አገርን ተጠቃሚ ለማድረግ ሰላም እና ስክነት ያስፈልጋል።

በአገር ጉዳይ መተማመንና መተባበር ግዴታ ነው። ሠላም፤ አንድነትና የብሄራዊ መግባባት የአንድ አገር የጀርባ አጥንት ናቸው። በዚህ ላይ ፖለቲከኞች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ምዕምናን፣ ምሁራን እና ሌሎች አካላትም የተለያዩ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ቢሆንም በአገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት ይጠበቅባቸዋል። ሠላምን መስበክ፤ መስከን ለነገ ጉዞ መሰረት መጣል ነው። እንስከን።

ስክነት ያስፈልጋል። ስክነት ብስለት ነው፤ ብስለት ደግሞ የነገሮች መቋጫ ወይንም መፍትሄ ማማጫ ነው። ለመፍትሄው በደንብ ማማጥ አለብን። ምጡ የረዘመ ቢሆንም ለበጎ ከሆነ ዋጋ መክፈል ተገቢ ነው። በመሆኑም ነገሮችን በብስለትና ስክነት ማየት እንዲሁም ነገን አሻግሮ መመልከት ይገባል።

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ከሚሊየነርነት ወደ ጎዳና ሕይወት

**ማህሌት አብዱል**

አቶ ኢያሱ ሻንቅሎ ይባላሉ። ትውልድና እድገታቸው ወላይታ ሶዶ ሲሆን ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ ግን ኑሯቸውን ባቱ (ዝዋይ) ከተማ ላይ አድርገዋል። በ14 ዓመታቸው ለስራ ወደ ባቱ የሄዱት እኚህ ሰው አደም በተባለ ሻይ ቤት በ30 ብር የወር ደመወዝ ተቀጥረው ነው የስራን ዓለም የተዋወቁት፤ በዚያ ለጋ እድሜያቸው ኑሯቸውን ለማሸነፍ ሲሉ ጋሪ በመግፋት፤ ሊስትሮ በመጥረግ፤ እንዲሁም በብስክሌት ጥገና ስራ ላይ ተሰማርተው ለዓመታት ደፋ ቀና ብለዋል።

ነገር ግን ሰው ከሰራ ያገኛልና አቶ እያሱም በሚሰሯቸው ስራዎች የገቢ አቅማቸው ከፍ ሲል ትዳር መስርተው አራት ልጆችንም አከታትለው በመውለድ ለስራ በመጡባት ባቱ ከተማ ላይ ደስተኛ ሕይወትን መምራት ቀጠሉ።

አቶ እያሱ የስራ ሰው ናቸውና በተለይም ልጆች ከወለዱ በኋላ አቅማቸውን በማጠናከር ገቢያቸውን ለማሳደግ ልጆቻቸውንም በጥሩ ሁኔታ ለማኖር በርካታ ስራዎችን መስራት ቀጠሉ። እንደ እድልም ሆኖ ያሰቡት የሚሳካላቸው የነኩት ሁሉ ፍሬ የሚያፈራላቸው ነበሩና ቀስ በቀስ የገቢ አቅማቸው እያደገ ኪሳቸው ላይም ጥሩ ገንዘብ እየገባ መጣ።

አቶ እያሱ የያዙትን ገንዘብ ቋጥረው ለልጆቻቸው ማረፊያ ይሆን ዘንድ መሬት ገዝተው ቤት ገነቡ፤ ከዚያም ባሻገር ተጨማሪ ለኪራይ የሚሆኑ ቤቶች በመገንባት ተጨማሪ ገቢን ማግኘት ጀመሩ። በዚህ ብቻ አልተወሰኑም፤ ሌሎች አራት ተጨማሪ መሬቶችን ገዝተው የሚያከራዩትን ቤት ቁጥር 58 አደረሱ። ይህ ከፍ ያለ ሞራልን የጨመረላቸው አቶ እያሱ፤ ዕለት ዕለት ሳይታክቱ ይሰራሉ፤ ለሌሎችም የስራ እድል ፈጥረው ሥራቸውን ያሰፋሉ። ደግሞ ሌላ የገቢ አቅማቸውን የሚያሳድግላቸው የስራ ሃሳብ ለማግኘት ይጥራሉ።

የአካባቢው ማህበረሰብም በአቶ ኢያሱ ስራ ወዳድነትና ታታሪነት ይደነቃል። በተለይ ከሊስትሮነት ጀምሮ ባለሃብት እስኪሆኑ ድረስ ያሳለፉትን ውጣውረድ የሚያውቁ ሰዎች እንደ አቶ ኢያሱ ለመሆን ይመኛሉ። አንዳንዶቹም ተሞክሯቸውን በመውሰድ ወደ ንግድ ዓለም የተቀላቀሉም አሉ። አቶ ኢያሱ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያላቸውን ጥብቅ ቁርኝት ሲገልፁ ‹‹እኔ ደቡብ ልወለድ እንጂ እድገቴም ሆነ አብዛኛውን ህይወቴ ያሳለፍኩት ኦሮሚያ ውስጥ ነው፤ ሃብት ያካበትኩት፤ ቤተሰብ መስርቼ ልጆችም ያፈራሁት እዚሁ ነው። እትብቴ ከተቀበረበት ከወላይታ ሶዶ በላይ የኦሮሞን ባህልና ወግ ነው የማውቀው። ከከተማው ሕዝብ ጋርም እንደ ቤተሰብ የጠነከረ ግንኙነት ነው ያለኝ›› ይላሉ።

አቶ እያሱ ሥራቸው እየሰፋ ሲመጣም ለባለቤታቸው አነስተኛ ሻይ ቤት ከፍተው መተጋገዝ ጀመሩ እሳቸውም 75 ሺ ብር ከኮንስትራክሽን ባንክ ተበድረው ስራቸውን አስፋፉ። ተጨማሪ መሬት ገዙና ቤቶች በመገንባት እያከራዩ ገንዘባቸውን አጠራቀሙ። ከሚያከራይዋቸው ቤቶች በተጨማሪ የሸቀጣ ሸቀጥ ማከፋፈያ፤ የሞተር፣ ባጃጅና ብስክሌት መለዋወጫ እንዲሁም መሸጫ ከፈቱ።

የንግድ ተቋሞቻቸውን ለማስፋትና የገንዘብ አቅማቸውን ለማሳደግ ሲሉም ያሏቸውን አስር መሬቶች 13 ሚሊዮን ብር አስገምተው ከባንክ ሶስት ሚሊዮን ብር ብድር ወሰዱ። እንዳሰቡትም እቅዳቸውን ለማሳካት ሲሉ ደፋ ቀናቸውን ቀጠሉ።

ሰው ሲሰራ ችግር ማጋጠሙ አይቀርምና አቶ እያሱም አገር አማን ብለው ስራቸውን እየሰሩ ባሉበት ሁኔታ ያላሰቡት ነገር አጋጠማቸው። ይኸውም በከተማ በሚገኝ አንድ መጠጥ ቤት ውስጥ በሁለት ሰዎች መካከል የተፈጠረው ፀብ አንደኛው ሰው ይጎዳና ሆስፒታል ይገባል፤ ጉዳዩም በህግ ጥላ ስር እንዲታይ ይደረጋል። ሆኖም ፀቡ በሁለቱ ሰዎች ላይ ብቻ ተወስኖ አልቀረም፤ የተጎጂ ሕይወት ማለፉን



አቶ ኢያሱ ሻንቅሉ

ተከትሎ በቅፅበት ችግሩ ሰፋ።

ባላሰቡትና በማያውቁት ነገር ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው ነዋሪዎች መካከል ደግሞ አቶ ኢያሱ አንዱ ሆኑ። በዕለቱ ስለተፈፀመው ነገር ሲያስረዱም ‹‹ኅዳር 3 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ላይ ሀገር ሰላም ነው ብዬ ቤቴ በተቀመጥኩበት የድንጋይ ናዳ ወረደብኝ፤ ይህ ግን እኔ ላይ ብቻ የሆነ አልነበረም» ይላሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ታዲያ ስለተፈጠረው ጉዳይ ምንም ፍንጭ የሌላቸው አቶ እያሱ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከጥቃት ከመከላከል ውጭ ምንም ማድረግ አልቻሉም ነበር። ግን ደግሞ ቤታቸው ተከራይተው ይኖሩ የነበሩ ሁለት ፖሊሶች ቤት ስለነበሩ ግጭቱን ለማስቆም የበኩላቸውን ጥረት ሲያደርጉ እንደነበር አልሸሸጉም።

ሁኔታው ግን ከአቅማቸው በላይ በመሆኑ ለከተማዋ ፖሊስ ደወሉ ንብረቴ ከመውደሙ በፊት ደረሱ። ይሁንና የደረሱት ፖሊሶች መከላከል ሳይችሉ በመቅረታቸው ለፌደራል ፖሊስ መደወላቸውን የተናገሩት አቶ ኢያሱ የፌደራል ፖሊሶች ባቱ እስከ ደረሱበት 10 ሰዓት ድረስ ተኩሱ አለማቆሙን ያስረዳሉ።

‹‹....... ቤታችን ከህንፃነት ወደ አመድነት እስኪቀየር ድረስ ሁከቱ አልቆመም ነበር። በመደብሮቹ ላይም ከፍተኛ ውድመት ደረሰ። በዚህም ከአስር ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት አጣሁ›› ይላሉ። አደጋው በደረሰበት ወቅትም የቤተሰባቸውንና የራሳቸውን ነፍስ ለማትረፍ ሲሉ ምንም አይነት ገንዘብም ሆነ ንብረት ሳይዙ በለበሱት ልብስ ብቻ መውጣታቸውን ያስታውሳሉ።

‹‹.....ለ29 ዓመት ባቱ ከተማ ስኖር አንድ ቀን በወንጀል ስሜ ተነስቶ አያውቅም፤ ወህኒ ቤት ገብቼ አላውቅም። ከስራ በስተቀር የማውቀው ነገር የለም። ሆኖም ግለሰቦች በፈጠሩት ጸብ ንብረቴን አጣሁ›› ሲሉ ያብራራሉ። በግላቸውም ከተቃጠሉባቸው ቤቶች በተጨማሪ በርካታ ሞተሮችና ብስክሌቶች እንዲሁም የሸቀጣሸቀጥ ማከፋፈያና የሞተር ብስክሌት መለዋወጫ መደብር በሙሉ የወደመባቸው መሆኑንም አቶ እያሱ ከፍ ባለ ቁጭት ይናገራሉ።

አደጋው ሲከሰት ያልጠበቅነው በመሆኑ ራሳችንን ለማትረፍ በለበስነው ልብስ ነው የወጣነው። በዚያ ጊዜ ውስጥ ግን ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆነው ንብረቴ ወድሟል።

በሁለት ግለሰቦች ፀብ በተስፋፋው ግጭት ምክንያት ለ29 ዓመታት ለፍተው ያፈሩት ንብረት በሙሉ በአንድ ጀምበር ማጣታቸው ከፍተኛ የሆነ የልብ ስብራት አድርሶባቸዋል።

አቶ እያሱ የባንክ ሶስት ሚሊዮን ብር ተበዳሪ ናቸው፤ ለዚህ ብድር ዋስትና ደግሞ ያስያዙት ቤታቸውን ነበር፤ ነገር ግን በደረሰባቸው ችግር ምክንያት የክፍያ ጊዜያቸው እንዲራዘም ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት እንዲሁም ሰላም ሚኒስቴርና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የትብብር ደብዳቤ ለባንኩ የጻፉላቸው ቢሆንም ባንኩ ችግራቸውን መረዳት ባለመፈለጉ ብቻ ቤታቸውን በዝግ ጨረታ እንደሸጠባቸው ይገልጽሉ። ‹‹...... መክፈል ባለመቻሌ ባንኩ የራሱን እርምጃ ወሰደ ቤቴም በግፍ እንዲሸጥ ሆነ ›› በማለት በሐዘን ተውጠው ይናገራሉ።

በሌላ በኩል ከእሳት ከተረፉት ቤቶቻቸው የተገኘውን አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ የቤት ኪራይ ባንኩ ገቢ አድርጎታል ‹‹ ቤቴ ሲሸጥም ጨረታው የወጣው ደግሞ የእኔ ፊርማ በሌለበት ሲሆን አራት ሚሊዮን ብር ሊሸጥ ሲገባው በአንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ብር ነው የተሸጠው። ሁለት ሚሊዮን የሚሸጠው ቦታ ደግሞ በ980 ሺ ብር ተሸጠ››። ይህ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ግን ሊመለስላቸው የሚገባ ቀሪ ገንዘብ እንዳልተሰጣቸው ይናገራሉ።

‹‹አሁን ላይ ምንም አይነት የገቢ ምንጭ የለኝም፤ አንዳንድ ጓደኞቼን እየለመንኩ ነው 18 ቤተሰቤን እያስተዳደርኩ ያለሁት። አሁን ባለው የኑሮ ውድነት አይደለም 18 ሰው አንድ ሰው እንኳን ራሱን አስችሎ ማኖር ከባድ ነው፤ ሌላው ይቅርና በፍርድ ቤትና አንዳንድ የፌደራል ተቋማት ጠርተውኝ አዲስ አበባ የምሄድበት ገንዘብ አጥቼ ጉዳዬ የተስተጓጎለበት አጋጣሚ ብዙ ነው›› ሲሉም የችግራቸውን መጠን ከፍ ባለ ሀዘን ውስጥ ሆነው ይናገራሉ።

‹‹....... ትናንት ብዙዎችን ስደግፍ እንዳልኖርኩኝ ዛሬ የሰው እጅ እያዩ መኖር በጣም ከብዶኛል። አሁን ላይ እኔም ሆንኩ ቤተሰቦቼ ጎዳና ወጥተናል። አዲስ አበባም ለጉዳዬ ስሄድ ለሆቴል መክፈል ስለማልችል መገናኛ የሚገኝ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው የማድረው››። አሁን ላይ እጅግ ተስፋ በመቁረጣቸው ምክንያት በተደጋጋሚ ራሳቸውን ለማጥፋት የሞከሩበት አጋጣሚ እንዳለ አቶ እያሱ እንባ እየተናነቃቸው ይናገራሉ።

በተለይም የእሳቸው ባልሆነ ጥፋት ለዘመናት ያፈሩት ሃብትና ንብረት በሰዓታት ልዩነት አመድ ሆኗል። ከልጅነታቸው ጀምሮ ለፍተው ያካባቱት ሁሉ ዛሬ በእጃቸው የለም። ለብዙዎች ይተርፉ የነበሩት ባለሃብትም ዛሬ ሜዳ ላይ ወድቀዋል።

‹‹......ትናንት 58 ቤት ሳከራይ ኖሬ ዛሬ አንዲት ደሳሳ ጎጆ አጥቼ ከባድ ችግር ውስጥ ነው ያለሁት፤ ሰርቶ ያወቀ ሰው አግኝቶ ማጣት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ይረዳል። ለአቅም አዳም ያልደረሱ ልጆቼን የማበላው አጥቼ ግራ ገብቶኛል። ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር አንድ ሃዋሳ የማውቃቸው ሰው በነፃ ቤታቸው አኑረውኛል። አሁን ላይ ግን ከነቤተሰቤ ጎዳና ወጥቻለሁ›› ይላሉ። በዚህ ችግር ምክንያትም በተለይ የመጀመሪያ ልጃቸውና ባለቤታቸው ለበሽታ መዳረጋቸውን እነሱን ለማሳከም ባለመቻላቸው ተጨማሪ ጭንቀት ፈጥሮባቸዋል። ስለዚህ ‹‹መንግስት የደረሰብኝን ተገንዝቦ መፍትሔ እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ›› ሲሉ ነው አቶ እያሱ የጠየቁት።

ሀገርም ሆነ ግለሰብ የሚጠቀሙት ከሰላም ብቻ ነው። ሰላም ሲሆን ሀገር ትበለጽጋለች፤ ዜጎች ሰርተው ሃብት ያፈራሉ፤ ያፈሩትንም ሃብት በአግባቡ መጠቀም ይችላሉ። ሰላም ከሌለ ግን በሃብትም ሆነ በንብረት መመካት ከንቱ ነው። ለዚህም ነው ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው የሚባለው። አቶ ኢያሱ ሻንቅሎ አሳዛኝ አጋጣሚም የሚያስተምረን ይህንኑ ነው። ስለዚህም በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሁሉ ለሰላም ትኩረት እንስጥ።

# ስፖርት





## ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ 5 ዓለም አቀፍ የውሃ ዋና ስፖርት ዳኞች አስመረጠች

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በውሃ ዋና ስፖርት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚዳኙ አምስት ዳኞችን አስመረጠች። ዓለም አቀፉ ውሃ ስፖርቶች ማህበር (ዎርልድ አኳቲክስ) በዓለም አቀፍ ደረጃ በፈረንጆቹ ከ2023 እስከ 2026 ድረስ ውሃ ዋና ውድድርን የሚዳኙ ዳኞችን ስም ዝርዝር ይፋ ሲያደርግ አምስት ኢትዮጵያውያን የውሃ ዋና ዳኞችን ማካተቱን የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ገልጿል። ይህም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በውሃ ዋና ስፖርት ውድድሮችን የሚዳኙ ዳኞችን ስታስመርጥ በታሪክ የመጀመሪያው መሆኑ ፌዴሬሽኑ አስታውቋል።

በቀጣዮቹ አራት ዓመታት ዓለም አቀፍ ውድድሮችን እንዲመሩ የተመረጡት አምስት ዳኞች በእውቀት አሳዬ፣ ጌታነህ ገብረስላሴ፣ በላቸው መላክ፣ ልደታ ገብረስላሴና አደባባይ ዘውዱ መሆናቸውን የዓለም አቀፉ ውሃ ስፖርቶች ማህበር ይፋ ካደረገው ዝርዝር መረዳት ተችሏል።

የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሠረት ደምሱ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፣ ዳኞቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ ውድድሮችን እንዲዳኙ ያገኙት እድል ዓለም አቀፉ የውሃ ስፖርቶች ማህበር ለአባል አገሮቹ የተሰጠውን እድል በመጠቀም ነው።

ይህም "የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ ከመገንባት ባለፈ ኢትዮጵያውያን ጠንክረን ከሰራን እና የሚገኙ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ከተጠቀምን በየትኛውም ደረጃ መስራት እንደምንችልና ብቁ ባለሙያዎች እንዳሉን ማሳያ ከመሆኑ ባሻገር በውሃ ዋና ስፖርቶች ጠንክረን እንድንሰራም የሚያደርግ ነው" በማለት ፕሬዘዳንቷ ተናግረዋል።

ፌዴሬሽኑ በውሃ ስፖርት የሀገራቸውን ስም የሚያስጠሩ ስፖርተኞችን እና ባለሙያዎችን ለማፍራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እንደሚሰራና የጀመራቸውን አበረታች ስራዎችም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ወይዘሮ መሰረት አክለዋል።

ፌዴሬሽኑ ባለሙያዎችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቁ እንዲሆኑ ከማገዝ ባሻገር የውሃ ስፖርቶችን ለማሳደግ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን፣ ባለፈው ዓመት የጀመረውን ከዓለም አቀፉ ውሃ ስፖርቶች ማህበር ጋር በቅርበት በመስራት ፕሮጀክት ቀርፆ የሚያገኘውን የገንዘብ ድጋፍ በየክልሉ የሚገኙ የውሃ ዋና የታዳጊ ፕሮጀክቶችን በሥልጠና ቁሳቁስ የማጠናከር ስራ አጠናክሮ መቀጠሉን ገልጿል።

በዚህም በዘንድሮ በጀት ዓመት ለክልሎችና ከተማ አስተዳደር የሚያደርገውን የቁሳቁስ ስርጭት ድጋፍ መጀመሩን ወይዘሮ መሰረት ጠቁመዋል።

ፌዴሬሽኑ ከቀናት በፊት ለአዲስ አበባ ከተማ ውሃ ዋና ፌዴሬሽን የስፖርት ቁሳቁሶችን ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፣ ከሃያ ዘጠኝ ሺህ ብር በላይ የሚያወጡ የፑል ቦይ እና የኪክ ቦርድ የስፖርት ቁሳቁሶችን ድጋፍ አድርጓል።

ወይዘሮ መሰረት ድጋፉን ባስረከቡበት ወቅት እንደተናገሩት፣ የአዲስ አበባ ከተማ ውሃ ዋና ፌዴሬሽን በተለይ በታዳጊና ወጣቶች ላይ እየሰራ የሚገኘው ስራ የሚያበረታታና ወደፊትም ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት በመሆኑ የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽንም የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላል።

በድጋፍ እርክክቡ ወቅት የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሃላፊ አቶ በላይ ደጀን በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ላደረገው ድጋፍ አመስግነው "ለከተማችን ብሎም ለሀገራችን የውሃ ዋና ስፖርት ሁለንተናዊ እድገት ከፌዴሬሽኑ ጋር በጋራ እንሰራለን" ብለዋል።

የስፖርት ቁሳቁሶችን የተረከቡት የአዲስ አበባ ከተማ ውሃ ዋና ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኢንጅነር ዳዊት እምሩ እንደተናገሩትም፣ በኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን የተደረገላቸው ድጋፍ ታዳጊ ወጣቶችን ለማሰልጠን የሚረዳና ተተኪዎችን ለማፍራት ፌዴሬሽኑ እያደረገ ላለው ጥረት አጋዥ ይሆናል። የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ትናንትናና ከትናንት በስቲያም ለክልሎች የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ ለመቀጠል ወደ ጋምቤላ ማቅናቱ ታውቋል።

ፌዴሬሽኑ በውሃ ዋና ስፖርት ተተኪና ውጤታማ ስፖርተኞችን ለማፍራት በታዳጊዎች ላይ መስራት የትኩረት አቅጣጫው አድርጎ በተግባር እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ የገለጸ ሲሆን፣ በፈረንጆቹ ከህዳር 16 እስከ 20 ታንዛንያ ዳሬሰላም በተካሄደው የዞን 3 የምስራቅ አፍሪካ የውሃ ዋና ቻምፒዮና ላይ በሁለት ታዳጊ ዋናተኞች መሳተፉ ይታወሳል። በቀጣይም አውስትራሊያ በሚካሄደው የዓለም የውሃ ዋና ቻምፒዮና ላይ በታዳጊዎች ለመሳተፍ እየሰራ ነው።




**የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን የተለያዩ ድጋፎችን ለክልል ፌዴሬሽኖች እየሰጠ ነው፣**



## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

በአብክመ በምስራቅ ጎጃም ዞን የባሶ ሊበን ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት የግዥና ንብረት አስተዳደር ቡድን ለሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት የሚውል በመደበኛ በጀት አሸዋ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**ስለሆነም ተጫራቾች፡-**

1. ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸውና ፍቃዳቸውን ያሳደሱና የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣
2 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ያላቸውና ማቅረብ የሚችሉ፣
3. ግዥው ከብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) በላይ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ የተመዘገቡና ለመመዝገባቸው የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
4. ተጫራቾች ከላይ ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱ ማስረጃዎችን ፎቶ ኮፒ በማድረግ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዞ በታሸገ ፖስታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ 3,000 /ሶስት ሺህ ብር/ በመሂ-1፣ በC.P.O ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ማሲያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ባሶ ሊበን ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 3 በመምጣት የማይመለስ 50 ብር ከፍለው መግዛት ይችላሉ፡፡
7. ይህ ግልፅ ጨረታ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ ለ15 ቀን በአየር ላይ ውሎ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3:30 ላይ የጨረታ ሳጥን ታሽጎ በእዚሁ እለት ከጥዋቱ 4፡00 ላይ ተጫራቾች /ህጋዊ/ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግዥ ክፍል ቢሮ ቁጥር 3 በግልጽ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻው ቀን በዓል ከሆነ በቀጣዩ የስራ ቀናት የሚከፈት ይሆናል፡፡
8. ተጫራቾች በዋጋ መሙያ ሰነዱ ላይ የድርጅቱን ማህተም፣ ስም እና ፊርማ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
9. አሸናፊው አሸዋውን ባሶ ሊበን ወረዳ ውሃና ኢነርጂ ጽ/ቤት ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
10. ተጫራቾች ዋጋ መሞያው ላይ ምንም ዓይነት ስርዝ ድልዝ ማድረግ የለባቸውም፡፡ ስርዝ ድልዝ ካለው ፓራፍ መደረግ አለበት፡፡
11.የባ/ሊ/ወ/ገንዘብ ጽ/ቤት በጨረታው የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**12. ስበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 058-246-03-16/05-65 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡**

**በአብክመ የምስራቅ ጎጃም ዞን የባሶ ሊበን ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ
## ቁጥር 26/2015

የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር ዝርዝራቸው ከዚህ በታች የተገለፁትን የተለያዩ እቃዎች በዝግ ጨረታ መሰረት አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡

ክፍል 1. የተለያዩ መጠን ያላቸው የተጠናቀቁ የጨርቅ ተረፈ ምርቶች

ክፍል 2. የተለያዩ አይነት የጥጥ ቅሪቶችና ተረፈ ምርቶች

ክፍል 3. የተለያዩ አይነት ብረታ ብርት እና መለዋወጫ ዕቃዎች

ክፍል 4. የተለያዩ መጠን ያላቸው የተጋቡ የፕላስቲክ ጀሪካኖችና የብረት በርሜሎች እንዲሁም ሌሎች ልዩ ልዩ ዕቃዎች

ጨረታው ማንኛውም በዘርፉ የታደሱ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያለው ግለሰብ ወይም ድርጅት መሳተፍ የሚችል ሲሆን ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል ከአክሲዮን ማህበሩ ቅ/ጽ/ቤት አዲስ አበባ ወይም ከዋና መስሪያ ቤት /ኮምቦልቻ/ መግዛት ይችላሉ፡፡

ዕቃዎቹን ዘወትር በሥራ ሰዓት (ከሰኞ-አርብ ከ2፡00-10፡00 እና ቅዳሜ ከ2፡00-6፡00) ዋና መስሪያ ቤት ኮምቦልቻ እንዲሁም የተወሰኑትን ዕቃዎች ደግሞ በአዲስ አበበ የድርጅት መጋዘን ላይ በመመልከት የሚገዙበትን ነጠላ ዋጋ አ/ማህበሩ ባዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ ላይ በትክክል በመሙላት በሰም በታሸገ ፖስታ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጨረታ መመሪያው ላይ በመገኘት ዋጋ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃን፡፡

ጨረታው ማታወቂያው በተዘጋ በ 3ኛው ቀን ከምቦልቻ /ወሎ/ በሚገኘው በዋናው መ/ቤት ከጠዋቱ በ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ይህ ቀን የህዝብ በዓል ከሆነ በሚቀጥለው ቀን ይከፈታል፡፡

አክሲየን ማህበሩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለተጨማሪ ማብራሪያ፡-**

**ስልክ ቁጥር፡- 033-551-06-27/551-02-11 (ኮምቦልቻ)**

**ስልክ ቁጥር፡- 011-551-18-05/553-01-24 (አዲስ አበባ)**

**ራስ ደስታ ደምጠው ጎዳና ፓፓሲኖስ ህንፃ አንደኛ ፎቅ**

**ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር**